“ዳንዲ ኦነግ”
የኦነግ

በታምራት መርጊያ

የለውጥ ጉዞው
“የልምዣት ሆነ
እንዴ?”

መ/ር አሸብር ውርጌሳ

ብሔር
ባይኖረንስ?

ተስፋ አሏታሰብ

ተስፋና ስጋትን
ያዘለው የጥላቻ
ንግግርን ከአሜሪካ

ጃፈር ሰዩም


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 63 ሐምሌ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99




አዲሱ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን
ዶ/ር ዳንኤል ማን ናቸው?



“አገሪቱን የሚጠላ መንግስት
ገዢ ሲሆን ውጤቱ አስከፊ ነው”

ኘ/ር ጌታቸው በጋሻው



# ዶክተር ዐቢይ
# ኮሎኔል ሆነው
# ሊመጡ ይሆን?

ተስፋና ስጋትን ያዘለው ከአሜሪካ የጥላቻ ንግግርን የሚያሰራጩ ኢትዮጵያውያን የክስ ጉዳይ
ጃፈር ሰዩም
2

ጠ/ሚ/ሩን ወደ ኃይል ዕርምጃ ያንደረደራቸው የሕዝብ ግፊትና አሳዛኝ ክስተቶች!
4

የይድረስ ይድረስ
ፍቅርተ ተሾመ
8

"ዳንዲ ኦነግ" የኦነግ መንገድ
በታምራት መርጊያ
9

ቅምሻ
11

ብሔር ባይኖረንስ?
ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
12



ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ኮሎኔል ሆነው ሊመጡ ይሆን?
መሳክ ቢ.
5




ቁጥር 62 ዕትም

# ግዮን

**ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ**
**ሐምሌ 6**
**ይጠብቁን!**



"አገሪቱን የሚጠላ መንግስት ገዢ ሲሆን ውጤቱ አስከፊ ነው"
ፕ/ር ጌታቸው በጋሻው
14


በጠ/ሚ/ር ዐቢይ ቸልተኝነት የብር የመግዛ አቅም እየወረደ ነው
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት
19

6ቱ የሆቴል ሸው አፍሪካ ምርጥ ተሸላሚዎች
20

"ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል"
አፈወርቅ በቀለ
22

የአገረገዢነት ማዕረግ ያገኘው፤ "ሩሲያዊው ደጃዝማች" ኒኮላይ ስቴፋቪች ሊዎንቴቭ
ብሩክ መኮንን
23

የለውጥ ጉዞው "የልምዣት ሆነ እንዴ?"
መምሕር አሸብር ውርጌሳ
25



ዶክተር ዳንኤል በቀለ በሰብኣዊ መብት ጥሰቶች ዙሪያ፤ አንባገነኖችን ሲታገል የኖረ ታላቅ ሰው!
ብሩክ መኮንን
3


ጃፌር ስዩም

# ተስፋና ስጋትን ያዘለው ከአሜሪካ የጥላቻ ንግግርን የሚያሰራጩ ኢትዮጵያውያን የክስ ጉዳይ

ባለፈው ሳምንት “ያሸለቡት የአዴፓ ጀግኖችና የማህበራዊ ሚድያው መዘጋት” በሚል ርዕስ በጻፍኩት ጽሁፍ፣ የማህበራዊ ሚዲያውን መዘጋትና መጠነኛ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ ሞክሬ ነበር፡፡ ከነዚህም ውስጥ መንግስት ኢንተርኔትን በፍጥነት መክፈቱ የሚበረታታ ተግባር ነው፡፡ ከአመታት በፊት አንድ ግለሰብ ስለ ኢንተርኔት ሲናገር “ኢንተርኔት በውስጡ 98 በመቶ ጠቃሚ 2 በመቶ ደግሞ ጎጂ ነገሮችን ይዟል፡፡ ሆኖም 98 በመቶ የሚሆነው የዓለማችን ህዝብ ኢንተርኔት ከያዛቸው ነገሮች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 2 በመቶ የሚሆነው መጥፎ ነገሮች ላይ ያተኮረ አጠቃቀምን ሲከተል የቀረው 2 በመቶ የሚሆነው የዓለማችን ህዝብ ደግሞ 98 በመቶ በሚደርሰው ጥሩ ነገሮች ላይ አተኩሮ ኢንተርኔትን ይጠቀማል” ብሎ ነበር(የተጠቀመውን ምንጭ አላስታውስም)፡፡

አልተገናኘቶም! በግርድፉ “ጥሩ” ተብለው የሚጠቀሱት ነገሮች መረጃን፣ እውቀትን፣ ግንዛቤን፣ መጽሐፍትና የንባብ ባህልን የሚያዳብሩ ነገሮች ፣ ንግድን፣ አዳዲስ ሰዎች መተዋወቅን፣ የባህልና የልምድ ልውውጥን እና የመሳሰሉት ነገሮችን ሲሆን፤ መጥፎ ተብለው የተቀመጡት ነገሮች የጥላቻ ንግግሮች፣ ዘርና ሀይማኖት ላይ የሚሰነዘሩ ስብከቶች፣ ከሞራልና ባህል ያፈነገጡ አጸያፊ ምስሎችና ቪዲዮዎች፣ በኢንተርኔት የሚፈጸሙ ማጭበርበሮች ወዘተ ብለን ሌሎች ነገሮችንም ጨምረን ልንመድባቸው እንችላለን፡፡

## ተስፋ

ሀላፊነት የማይሰማቸው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጉዳይን አስመልክቼ በህግ ሊጠየቁ እንደሚገባ፣ በኢንተርፖልም ጭምር ተይዘው መቅረብ እንዳለባቸው ሀሳቤን አካፍዬ ነበር፡፡ በማህበራዊ ሚዲያ የሚደረጉ ቅስቀሳዎች ብዙዎቻችንን ያሳዘነ ከመሆን በላይም እነዚህን የጥላቻ ነጋዴዎች ማቆም ያለመቻሉ ጉዳይ ግራ የሚያጋባ ሆኖ ሰንብቷል፡፡ አንዳንዶቹ በግልጽ በቀጥታ ቪዲዮ እየተቀረጹ ህግና ተጠያቂነት ያለበት አገር አሜሪካ ቁጭ ብለው “የአዴፓ አመራሮችን በጥይት ግንባራቸውን በሏቸው” እያሉ ሲቀሰቅሱ ተመልክተናል፡፡

ሆኖም በሳምንቱ አጋማሽ በፌስቡክ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰማነው ብስራት ውስጥን በተስፋ ይሞላል፡፡ ርዕሱ ብቻ ልብን ያሞቃል፦ “የጥላቻ ንግግር የሚያሰራጩ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀመረ” ይላል፡፡ በማብራሪያውም እነዚህ የጥላቻ አርበኞችን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ እንቅስቃሴ የጀመረው የኢትዮጵያ አሜሪካውያን የዜጎች ምክር ቤት መሆኑን ገልጾ፣ ይህ ምክርቤት በሕወሓት ዘመን HR 128 የተሰኘውን የውሳኔ ሀሳብ በአሜሪካ ኮንግረስ እንዲጸድቅ መስራቱን ያስረዳል፡፡ የተደላደለ ሕይወት ላይ ሆነው ድሃውን ህዝብ እርስ በርስ በማጋጨት የሙሉ ስራ እየሰሩ ያሉ ግለሰቦች፣ በህግ ተጠያቂ ለማድረግ ስራዎቹ እየተጠናቀቁ መሆኑን መስማታችን በርግጥም ተስፋን የሚያለመልም ዜና ነው፡፡

ከነዚህ የጥላቻ አራማጆች ውስጥ የተወሰኑት በተለያዩ ምክንያቶች ከተወዳጁ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ተባረውና በገዛ ፍቃዳቸው ለቀው ከወጡ በኋላ አገርን ለማመስ የጥላቻ ጅራፍ እያጮሁ ነው፡፡ ከነርሱ ውስጥ የተወሰኑት በዩቲዩብ የምትገኘን ሞኒታይዜሽን(ክፍያ) ተማምነው የጥላቻ ጅራፋቸውን ለማጮህ ይረዳቸው ዘንድ ሀሰተኛ መረጃ(Fake News)፣ መሰረት አልባ ክስ (Baseless accusation) እና የወረደ ትንተና(poor analysis) ተጠቅመው በርካታ የትምህርትና የስራ አማራጮች ባሉበት አሜሪካን ሀገር ተቀምጠው፣ ራሳቸውን ከማሻሻል ይልቅ ያደጉበትን ያረጀ የሕወሓት የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ በማራመድ ላይ ተጠምደዋል፡፡

ይህንኑ አገርን የሚጎዳ ተግባር፣ ስራዬ ብለው በየዕለቱ “ክራቫትና ሸሚዝ” ለብሰው እየተሰየሙበት የገቢ ምንጭ አድርገው ይዘውታል፡፡ አገርን በሚጠቅም እንኳን ባይሆን በማይጎዳ መልኩ በማህበራዊ ሚዲያም በሚሰሩ ስራዎችም ቢሆን ኑሯቸውን መምራት ሲችሉ፣ ሕዝብ መንግስት ላይ እምነቱን እንዲያጣ እያንዳንዷን ቀዳዳ በመፈለግና በማጉላት በተለይም ዘር ላይ ባነጣጠሩ ቅስቀሳዎች የአንድ ብሔር የበላይነት እንዳለ ሰፊ ቅስቀሳ በማድረግ በዘር ፍቅርና በዘር ጥላቻ ያበደውን ትውልድ “በመንጋ እናንጋጋዋለን” ብለው የጥፋት ስራቸው ላይ ተሰማርተዋል፡፡

የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀታቸው በጣም አሳፋሪና የወረደ መሆኑን በተደጋጋሚ በድፍረት በሚገልጿቸው ንግግሮቻቸው ውስጥ ታዝበናል፡፡ ለምሳሌ ያህል የበረከት ስምዖን ምክትል ሆኖ የኮሚኒኬሽን ሚኒስትር ደኤታ የነበረው ግለሰብ ከኢሳት ከመልቀቁ ጥቂት ወራት በፊት አዲስ አበባን አስመልክቶ በዋሽንግተን ዲሲ በተደረገ ውይይት ላይ ጽሁፍ አቅራቢ ሆኖ ቀርቦ “ዕለታዊ” የተሰኘው የኢሳት ፕሮግራም ተወዳጅ እንደሆነና ሀሳባቸውን በነጻነት እንደሚያንሸራሽሩበት ገልጾ ከ1 የዕለታዊ ፕሮግራም እስከ 2000 የአሜሪካን ዶላር ዩቲዩብ እንደሚከፍላቸው በድፍረት ሲናገር ተመልክቼው አፈርኩበት፡፡

ግለሰቡ ስለ ‘YouTube Monetization’ ያለው እውቀት ማንኛውም ሰው በቀላሉ ከጎግል ከሚያገኘው ተራ እውቀት እንኳ ያነሰ፣ በጣም የቀጨጨ መሆኑን የተረዳሁበት አጋጣሚ ነበር፡፡ እውነታው ግን 1000 ሰዎች አንድን የዩቲዩብ ቪዲዮ ሲመለከቱት እንደሚመለከቱበት ሀገርና ሲዝን(ለምሳሌ በገና በአል ሰሞን ክፍያው ከፍ ይላል) ከ1 እስከ 5 የአሜሪካን ዶላር ይገኝበታል፡፡ እርሱ እንደገለጸው በወቅቱ እስከ 100,000 የሚደርሱ ሰዎች አንድን የዕለታዊ ቪዲዮ ቢመለከቱትና 1000 ሰዎች ሲመለከቱ ኢሳት 3 ዶላር እንዲያገኝ አማካኝ ዋጋ ብናስቀምጥለት 100ሺ ሰዎች በተመለከቱት ቪዲዮ 3X100=$300 ለኢሳት ያስገባል፡፡ ይህም በካልኩሌሽን ችግር የተፈጠረ ሳይሆን ካለማወቅና ከነባራዊ ሁኔታ በመራቅ የተፈጠረ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ሌላኛው አጋሩ ሰሞኑን የዲጂታልና አናሎግን ምንነት ለይቶ ማወቅ በማይችልበት ሁኔታ ትንታኔ ሲሰጥ ስመለከተው የጥላቻ ሰባኪዎች አብዛኞቹ የመሀይም ስብስቦች መሆናቸውን ያጋለጠበት ሆኖ አልፏል፡፡

በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በጀርመን አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ውስጥ በድፍረት ዘር ላይ ያነጣጠረ ጥቃትን የምትቀሰቅስን ግለሰብ መንግስት ትኩረት አድርጎ በሕግ ሊጠይቃት ይገባል፡፡ ግለሰቧ ፈጽሞ ከአንዲት ሴት ያውም እናት በማይጠበቅ ሁኔታ በግልጽ “ይህንን ብሄር አጥቁት፣ አጥፉት” እያለች በናዚው የአዶልፍ ሂትለር አገር ተቀምጣ በድፍረት ትቀሰቅሳለች፡፡ ይህንን የጥላቻ ዘመቻዋን የሚያሳዩ በርካታ ቪዲዮዎች በፌስቡክና በዩቲዩብ ለምስክርነት ተቀምጠዋል፡፡ መንግስት በዚህች ሴትና መሰሎቿ ላይም ህጋዊ ዕርምጃ ለመውሰድ ዳተኝነትን ካሳየ እንቅስቃሴውን ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይከተዋል፡፡

## ስጋት || የጥላቻ ንግግርን እንደ ማጥቂያ?!

### የጥላቻ ንግግር ግን ምንድነው?

በመላው ዓለም የጥላቻ ንግግርና የመናገር ነጻነት በተምታታ መልኩ በስራ ላይ ሲውሉ እየተመለከትን ነው፡፡ ብዙሃንን የሚያስማማው የጥላቻ ንግግር ትርጉም በግለሰብ ወይም በቡድኖች ላይ ያተኮረ በንግግር የሚደረግ ጥቃት ነው፡፡ እነዚህ ቡድኖች የተወለዱበት ዘር፣ የሚከተሉት እምነት፣ የተወለዱበት አካባቢ/ሀገር፣ ጾታ እንዲሁም የአካል ጉዳት ላይ የተማከለ ሊሆን ይችላል፡፡ በአገራችንም እንደ መላው ዓለም ሁሉ ሰዎችን በብሄራቸው፣ ሀይማኖታቸው፣ ቋንቋቸው፣ ጾታቸው(በተለይ ሴት እህቶችን) እንዲሁም የአካል ጉዳትን ያማከለ የጥላቻ ንግግሮችን ተመልክተናል፤ እየተመለከትንም ነው፡፡

ፈረንሳያዊው ጸሀፊ፣ የታሪክ አዋቂና፣ ፈላስፋ የሆነው ቮልቴር ከ20ሺ በላይ ደብዳቤዎችንና ከ2ሺ በላይ መጽሃፍትና

ቀሪውን በገጽ 27 ይመልከቱ

# ዶክተር ዳንኤል በቀለ

## በሰብኣዊ መብት ጥሰቶች ዙሪያ፤ አንባገነኖችን ሲታገል የኖረ ታላቅ ሰው!

ብሩክ መኮንን



የሰብኣዊ መብት ተከራካሪ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰብኣዊ መብት ተከራካሪነታቸው በ2009 የኤልቪን ዲሲ ፎርጂስ የላቀ አክቲቪትነት ሽልማት ተሸላሚ፣ በ2010 የታዋቂው የ"ማርቲን ኤናልስ" የሰብኣዊ መብት ተከራካሪዎች ሀሳብን በነፃነት ለመግለጽ የሚደረጉ ትግሎች ውስጥ ከፍተኛ ሚና ላበረከቱ ተከራካሪዎች የሚሰጠው የሚሰጠውን ክብርና ሽልማት በመቀዳጀት በዓለምአቀፍ ደረጃ በሰብኣዊ መብት ተከራካሪዎች ተርታ ስማቸው በደማቁ ተጽፏል፤ አዲሱ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ ሙሉጌታ።

ማክሰኞ ሰኔ 25 ቀን 2011 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባካሄደው ስብሰባና በምክር ቤቱ አፈጉባኤ በተመራው የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ አማካይነት በዕጩነት ቀርበው ከነበሩት 88 ግለሰቦች መካከል፣ ዶ/ር ዳንኤል በቀለ ባላቸው የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ሲመዘኑ፣ ብቁና የተሻሉ ሆነው በመገኘታቸው አንድ የተቃውሞ ድምፅና በከፍተኛ ድጋፍ ተመራጭ ሆነዋል።ዶ/ር ዳንኤል በቀለም "የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር" ኃላፊነታቸውን በታማኝነት ለመወጣት፣ በምክር ቤቱ ፊት ቃለ መሃላ ፈጽመዋል።

ዶ/ር ዳንኤል በቀለ ሙሉጌታ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩሊቲ ካገኙ በኋላ በታዋቂው "አበበ ወርቁና ሸሪኮቹ የህግ ባለሙያዎች ኩባኒያ" ውስጥ ተቀጥረው ለዓመታት አገልግለዋል፡ ፡ በመቀጠልም በሕብረት ኢንሹራንስ ኩባኒያ የሕግ ዲፓርትመንት፣ የኢንሹራንስ ኩባኒያው የቦርድ ጸሐፊ በመሆን ሰርተዋል።

በመቀጠልም በ"አክሽን ኤድ ኢትዮጵያ" የፖሊሲ ምርምርና የአድቮካሲ ዲፓርትመንት ማኔጀር በመሆን የሲቪል ማህበረሰቡ በሀገራ ሶሺዮ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል።

ዳንኤል በቀለ ከአክሽን ኤድ ኢትዮጵያ በተጨማሪ ኦክስፋም፣ አርቲክል 19፣ ፊርደም ሐውስና፣ ፖክት የተሰኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ከዓለም ባንክ ጋር በተለያዩ የአማካሪነት ኃላፊነቶችም ሰርተዋል። በበርካታ የሲቪል ሶሳይቲ ተቋማት ውስጥም በተለያዩ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድበው ሙያዊ ግልጋሎት ሰጥተዋል።

በነዚህ ከፍተኛ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሲሰሩ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የፀረ ድህነት እንቅስቃሴዎችን ወደ ዓለም አቀፍ መድረኮች በማቅረብ ፤የፀረ ድህነት ዘመቻዎችን በበላይነት መርተዋል። በተጨማሪም በአፍሪካ ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት፣ በሰብኣዊ መብት እና በመልካም አስተዳደር መሰረታቸውን ያደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ወሳኝ ሚና እንደተጫወቱ ይነገርላቸዋል።

በ1997 ዓ.ም በኢትዮጵያ በተካሄደው አገራዊ ምርጫ ወቅት ሕብረተሰቡ በነፃና ገለልተኛ ምርጫ ንቁ ተሳታፊ በመሆን መሪዎቹን እንዲመርጥ በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ያስቻሉ ተግባራትን በማከናወን ረገድ የሕግ ባለሙያው ዳንኤል በቀለ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ወገኖች አንዱ ነበሩ።

ከሲቪል ማኅበረሰቡና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎች በሁሉም የአገሪቱ የምርጫ ጣቢያዎች ተሰማርተው ምርጫውን እንዲታዘቡ በማድረጉ ረገድ፣ እንዲሁም ምርጫውን ተከትሎ በአገሪቱ የተከሰተው ግጭት ሰላማዊ ዕልባት እንዲያገኝ በተካሄዱ እንቅስቃሴዎች ዶ/ር ዳንኤል በቀለና ባልደረባቸው ነፃነት ደምሴ የነበራቸው ከፍተኛ ሚና እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም።

ይህ እንቅስቃሴያቸውን ያልወደደው ገዢው ፓርቲ ለወራት የዘለቀውን ሕዝባዊ ተቃውሞና ውዝግብ በኃይል ለመጨፍለቅ በወሰደው ዕርምጃ፣ በአገሪቱ ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችንና አባላትን፣ ጋዜጠኞችን በሙሉ ሰብስቦ ወደ ወሕኒ በወረወረበት አሳፋሪ ዕርም ጃው፣ዳንኤል በቀለና ባለደረባቸው ነፃነት ደም ሴንም "ሕገ መንግስቱን በኃይል ለመናድ ተን ቀሳቀስዋል" በሚል ክስ ወሕኒ ወረወራቸው።

ዳንኤልና ነፃነት ደምሴ በወሕኒ በቆዩባቸው አንድ ዓመት ከአስር ወር በሚደርስ ጊዜ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸው ተቋማት፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የተለያዩ አህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፤ ሁለቱ ግለሰቦች ለሰብኣዊ መብት መከበር፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት እውን መሆን በመስራታቸው፣ ያለፍርሃት በመታገላቸው አድናቆታቸውን በመግለጽ ፣ የመለስ ዜናዊ መንግስት ዳንኤል በቀለና ነፃነት ደምሴን በአስቸኳይ ከዕስር እንዲፈታ ከፍተኛ የሆነ ዴፕሎማሲያዊ ዘመቻዎችን አካሂደዋል።

ከአንድ ዓመት ከአስር ወር ዕስር በኋላ የኢትዮጵያ መንግስት የሚሊኒየሙን በዓል ምክንያት በማድረግ በዕስር ላይ የሚገኙት የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን በምህረት ሲፈታ፣ እነ ዳንኤልም ነጻ የመሆን ዕድልን አግኝተው ከጠባቡ እስር ቤት ወጡ።

የሕግ ባለሙያ፣ የሰብኣዊ መብት ተከራካሪው ዳንኤል በቀለ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በሪጅናል ዴቨሎፕመንት ስተዲ ያገኙ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀሳብን ለመግለፅ በሚያደርጉት ጥረት ሳቢያ ለዕስር ከተዳረጉ የዓለማችን እውቅ የሀሳብን መግለፅ ነፃነት ታጋዮች ስም ዝርዝር ውስጥ ስማቸው ሊካተት ችሏል።

ዶ/ር ዳንኤል በቀለ ሙሉጌታ ከዕስርና ከመከራ በኋላ ወደውጭ አገር በማምራት በአሜሪካ ኒዮርክ በሚገኘው የሂዩማን ራይትዎች ዋና መስሪያ ቤት "ከፍተኛ የአፍሪካ አድቮኮሲ ዲፓርትመንት ዳይሬክተር"፣ ከ2011 እስከ 2016 በተቋሙ የአፍሪካ ጉዳዮችን የሚመራው ዲፓርትመንት ዋና ዳይሬክተርም በመሆን ሰርተዋል። ከዚህም በተጨማሪ "አምንስቲ ኢንተርናሽናል" በተባለው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ተቋም ውስጥ በከፍተኛ አማካሪነት ሰርተዋል።

በኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ የሕግ ፋኩሊቲ ሁለተኛ ዲግሪ በሕግ ትምህርት ከማግኘታቸው በተጨማሪ፣ በዚያው በኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ በዓለም አቀፍ ሕግ ትምህርት የዶክተሬት ዲግሪያቸውን በቅርቡ የወሰዱት ዶ/ር ዳንኤል በአገራችን ኢትዮጵያ የተከሰተውን ለውጥ ተከትሎ ስልጣኑን የወጡትና ሕወሓት መራሹ መንግስት በዜጎች ላይ ያደረሰውን አስከፊ የሰብኣዊ መብት ጥሰት ከማጋለጥ ባሻገር ጥፋቶቹ እንዳይገደሙ ለማድረግ በቁርጠኝነት እየሰሩ የሚገኙት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ የሕግ ባለሙያና የሰብኣዊ መብት ተከራካሪው ዶክተር ዳንኤል በቀለ ሙሉጌታን የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር አድርጎ ሾመውታል።

የዶ/ር ዳንኤል በቀለ በሀገራችን በኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብቶች ተከብረው፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እውን ሆኖ፣ ሕዝብ ነጻነቱ እንዲከበር ሲሉ ብዙዎች ሕይወታቸውን፣ አካላቸውን የገበሩበት ትግል ፍሬ ለማፍራት የተንደረደረበት፣ የብዙዎች ተስፋና ምኞት እውን የሚሆንባት ኢትዮጵያን የምናይባት ጊዜ መቅረቡን የሚያመለክት ብርሃን መፈንጠቁን የሚያሳይ ነው ብለው የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው።

የኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ከተቋቋመ ጀምሮ ጥርስ የሌለው አንበሳ ሆኖ፣ የተሰጠውን ሕዝባዊ ኃላፊነትና ስልጣን በአግባቡ ሳይጠቀም፣ አለ እንዲባልና ለሚዲያ ፍጆታ ብቻ ይውል የነበረው ሚናው ተቀይሮ፣ በመላው አገሪቱ እየታዩ ያሉ ፋታ የማይሰጡ የሰብኣዊ መብት ጉዳዮች ላይ ተቋሙ ሊጫወተው የሚገባውን ድርሻ እንዲወጣ ትክክለኛው ሰው በትክክለኛው የኃላፊነት ቦታ ተመርጧል ብለው እንደሚያምኑ በሹመቱ ላይ አስተያየታቸውን ለግዮን የሰጡ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ይናገራሉ።

የግዮን መጽሔ ዝግጅት ክፍል ለዶክተር ዳንኤል በቀለ ሙልጌታ ለተሰጣቸው ከፍተኛ ኃላፊነት አደራ በብቃት ይወጡ ዘንድ መልካሙን እየተመኘን በቅርቡ ከእኚሁ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር ጋራ ቃለምልልስ አድርገን እናቀርባለን።

# ጠ/ሚ/ሩን ወደ ኃይል ዕርምጃ ያንደረደራቸው የሕዝብ ግፊትና አሳዛኝ ክስተቶች!

ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀረቡት ሪፖርት የብዙዎችን ትኩረት ስቧል። ከቀናት በፊት ሶስት የአማራ ክልል ባለስልጣናት (ርዕሰ መስተዳሩን ጨምሮ) እና ሁለት ጀነራሎች የተሰውበት ሂደት እጅግ አሳዛኝ ነበር ማለት ይቻላል። የሀሳብ ልዩነትን፣ በሀሳብ ብልጫ መቀልበስ፤ አልያም "ገሸሽ" ማለት ሲቻል ያን ማድረግ ያልፈለገ አካል የወሰደው ግብታዊ ዕርምጃ ከተማሪ እስከ አገር መሪ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል በሀዘን አንገት አስደፍቷል።

በዚህን መሰሉ አስከፊ ስሜት ውስጥ ሆነው፣ በፓርላማው ፊት ንግግር ያደረጉት የለውጡ አጋፋሪ፤ "አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር" ሆነው ታይተዋል። ከአስራ ሁለት ወራት በላይ የተሻገረው ተለማማጭነትና ፍቅር ሰበካ ድራሹ ጠፍቶ፣ ትዕግስታቸው ተሟጦ ሌላ ሰው ይመስሉም ነበር። አምባገነኑን ስርዓት አሽቀንጥሮ የጣለው የለውጡ ቡድን የተከተለው ሆደ ሰፊነትና አስተዋይነት፣ ከየቦታው የሚነሱ ሁከትና ግጭቶችን ለመቆጣጠር የሄደበት መንገድ፤ ከዚህ ቀደም በነበሩ መንግስታት (በተለይም ባለፉት አርባ ዓመታት) ያልታየ መሆኑ፣ ስልጣኑን በያዙት አካላት ላይ የተለያዩ ትችቶችን ሲያስነዝር ቆይቷል።

ከሰኔ 16ቱ የመስቀል አደባባይ የመግደል ሙከራ፣ ከሶማሌው ከአብዲ ዒሌ ዘግናኝ ጥፋት፣ ከ"ኦነግ ሸኔ" ተደጋጋሚ ዝርፊያዎችና አላስፈላጊ ጦርነቶች በመነሳት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ በአጥፊዎቹና በለውጡ አደናቃፊዎች ላይ ጠንከር ያለ ዕርምጃ አለመውሰዳቸው፣ በይቅርታና በምሕረት አዋጁ ተጠቅመው ከዕስር የወጡት ጀነራል አሳምነው ፅጌ፣ "ከመንግስታዊ ኃላፊነት ወደ ግል ጦር አዛዥነት" በግልፅ እንዲሸጋገሩ፣ በመንግስት በጀትም የአክራሪ ብሔርተኝነትና የበቀለኝነት ተግባርን የሚፈፅም ታጣቂ ኃይል ያለ ምንም እንከን እንዲያደራጁ፣ ዘግየት ብለውም የሰዎችን ሕይወት ባልተፈለገ መንገድ እንዲቀጥፉ በር ከፍቷል የሚሉ በርካቶች ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ዘርፈ ብዙ የግጭት ችግሮች በአገሪቱ ሲከሰቱ ቆፍጠን ብለው ዕርምጃ በመውሰድ ወንጀለኞችን ለሕግ ከማቅረብ ይልቅ፤ በተደጋጋሚ ነገሮችን በለዘብተኝነት ሲያስተውሉ ቆይተዋል ተብለው፣ በሕዝባቸው የሚከሰሱት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሁን ግን የቆረጡ ይመስላሉ። ከብሔርተኝነት ስሜት ወጥተው፣ ኢትዮጵያዊነታቸውን በማስቀደም በለውጡ ቡድን ውስጥ ትግል ሲያካሄዱ የቆዩት የትግል አጋሮቻቸው፤ በዚህ መንገድ መሰዋታቸው ቁጭትና ንዴት ውስጥ ከቷቸዋል። ሂደቱ ከዚህ ከፍ ብሎ ከመንበረ ስልጣናቸው ዳግም ላይደርስ ላለመቻሉም እርግጠኛ አይመስሉም።

"የእኔ ጠባቂ አያንቀላፋም" ያሉት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከእንግዲህ በኋላ የትኛውንም ስልጣንን በሕገ ወጥ መንገድ ለመቆጣጠር የሚደረግ እንቅስቃሴን፣ በኃይልና በተገቢው ዕርምጃ ለማኮላሸት፤ ብሎም ለመቅጣት ፈፅሞ እንደማያንቀላፉ ነው የነገሩን። በም/ቤቱ ላይ ጉዳዩን አስመልክቶ ያቀረቧቸው ሪፖርቶች ፣መንግስት የመረጠውን የፍቅርና የሰላም መንገድ ትቶ ማንኛውንም ዓይነት የኃይል መንገዶችን እንደሚጠቀም አረጋግጠዋል።

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ወደ ጉልበተኝነት የገፋቸው፤ የደረሰው ጥፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ መብዛትና ጓደኞቻቸውን በሞት ማጣት ብቻ አይደለም። ከዚህ ቀደም ሕዝብ በተለያየ አቅጣጫ "ለምን የኃይል ዕርምጃ አይወስዱም?" እያለ ሲያቀርበው የነበረውን ጥያቄ ምላሽም ይመስላል፡ ፡ ቅጥ እያጣ በመጣው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ችግር እየፈጠሩ ያሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ፣ ከዚህ በኋላ የተባለው ጠንከር ያለ ዕርምጃ ሲወስድ "ዐቢይ አምባገነን ሆነ" የሚል ጉምጉምታና ተቃውሞ፣ ከተለያየ አቅጣጫ መሰማቱም አይቀርም። አሁን አሁን "የእኔ ብሔር ተነካ" ባዩ፣ ከአገር ጥቅም ይልቅ ዘረኝነቱ የሚቀድምበት ሕዝብ በስፋት እየተስተዋለ ነውና።

የሆነ ሆኖ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፤ "ወታደራዊ" ስብዕናቸውን ተላብሰው፣ አገራዊ ኃላፊነታቸውን በቅጡ ተገንዝበው "እወስደዋለሁ" ያሉት ዕርምጃ እንደ ከዚህ ቀደሙ በፉከራ እንዳይቀር፤ በምክርና በተግሳፅ ብቻ እንዳይገለበጥ አደራ ለማለት እንወዳለን።የምንወዳት ኢትዮጵያን ከመንደርና ከጎጠኝነት ፖለቲካ አውጥቶ፣ አንድነቷን የሚያቆይ አማራጭ ሆኖ እስከቀረበ ድረስ።

**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2
የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
ፍቅርተ ተሾመ
ሙሉጌታ አክሊሉ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ (ከሲውዘርላንድ)
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
አሸናፊ ዘደቡብ
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661 +251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል:
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506

በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ኮሎኔል ሆነው ሊመጡ ይሆን?




**መላክ ቢ.**

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስትን የአንድ ዓመት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ሊያደምጥ ቀጠሮ የያዘው፣ መገናኛ ብዙሃንም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሪፖርት ለማስተላለፍ ዝግጅት ያደረጉት ባለፈው ሳምንት ሰኞ ሰኔ 17 ቀን 2011 ዓ.ም ነበር። ነገር ግን ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን ማምሻውን በመላው ኢትዮጵያ አስደንጋጭ የነበረው ክስተት ተፈጠረ። የአማራ ክልል ሶስት ባለስልጣናት እና የጦርሃይሎች ጠቅላይ ኤታማጆር ሹምን ጨምሮ ሁለት የጦር ጄኔራሎች በሰዓታት ልዩነት ውስጥ ተገደሉ።ይህ ያልተጠበቀ ክስተት በአገር አቀፍ ደረጃ የተያዙ ፕሮግራሞች በሙሉ እንዲቀየሩ አድርጓል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ይሰማበታል የተባለበት ሰኞ ዕለት፣ በመላው አገሪቱ የአንድ ቀን ብሄራዊ ሃዘን የታወጀበት ዕለት ሆነ። በዚሁ ዕለት የጄኔራሎቹ አስከሬንም ወደቀብር ስፍራው በክብር የተሸኘበት ስነስርዓት ተካሄደ ።የታቀደው የፓርላማ ስብሰባም በዚህ ምክንያት ተሰረዘ።

በሳምንቱ ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም ሰኞ ዕለት ፓርላማው በሃዘኑ ምክንያት ያስተላለፈውን ፕሮግራም አካሄደ። በዚህ ዕለት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ በጥቁር ክራቫት ነው ወደመድረክ የወጡት። ከምክር ቤቱ አባላት አብዛኞቹ ለሃዘን መግለጫ ጥቁር ለብሰው ነው ስብሰባውን የታደሙት። ሪፖርት አቅራቢው ጠቅላይ ሚኒስትር በጨገገ ፣ በደከመው እና ፈገግታ በራቀው ፊት የመንግስታቸውን የስራ አፈጻጸም ለህዝብ እንደራሴዎች ሲያቀርቡ ድምጻቸው ለሆሳስ ሆኖ ቢቆይም በአገሪቱ የተከሰተውን ድንገተኛ የባለስልጣናት ግድያ በተለይም መፈንቅለ መንግስት የተባለውን የአማራ ክልል ክስተት ጉዳይ መናገር ሲጀምሩ ግን ከፍተኛ ብስጭት ይታይባቸው ነበር። ከዚህ ቀደም ብዙም ባልታየባቸው "ኮምጫጫ" ስሜት ውስጥ ሆነው የሰነዘሯቸው ቃላቶች "ምሬታቸውን" የሚያመላክቱ ብቻ ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስትሩን Enough is Enough "በቃ ማለት በቃ ነው!" የሚል አቋምም በግልጽ ያንጸባረቁ ነበሩ ማለት ይቻላል። በተለይም "ከዚህ በኋላ…" በማለት የሰጧቸው ማስጠንቀቂያዎች ጠቅለል ያለ ይዘት ሲፈተሽ፣ ከዚህ በፊትም በተለያዩ መድረኮች ላይ ያደረጓቸው ንግግሮች ተደምረው ሲጤኑ "ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኮሎኔል ሆነው ሊመጡ ይሆን ?" የሚል ጥያቄ ያስነሳል።

## "ኮሎኔል- ከጠቅላይ ሚኒስትርነቱም በፊት"

ጠ/ሚ/ር ዐቢይ የኦህዴድ አባል ከሆኑ በኋላ ቀዳሚ ሙያቸው ወታደርነት ነው። እሳቸው የፓርቲው አመራር ከመሆናቸውም በፊት፣ ዳይሬክተርም ከመሆናቸው በፊት፣ ሚኒስትር ሆነው ከመሾማቸውም በፊት፣ከዚያም የኦህዴድ ሊቀመንበር ከመሆናቸውም በፊት፣ ቀጥሎም የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ከመመረጣቸውም በፊት ኮሎኔል ነበሩ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ከስማቸው በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር የሚል የማዕረግ ቃል ከመግባቱም በፊት ሆነ በግጭት አፈታት ዶክተር ኦፍ ፊሎሶፊ (PHD) የሚለው የትምህርት ማዕረግ ከስማቸው ኋላ ከመከተሉ በፊት ኮሎኔል ነበሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በስለላ እና ግንኙነት ጠለፋ ሙያ ላይ በትግራይ የተለያዩ አካባቢዎች ከሻዕቢያ ጋር በተደረገው ጦርነት ወቅት አገልግለዋል። በተለይም በባድመ ውጊያ በኢንተሊጀንስ ኮሙኒኬሽን ቡድን መሪነት የጦርነት ውሎዎችን ኖረውባቸዋል። ሩዋንዳ ውስጥም የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ሃይል አባል ሆነው በዚሁ ወታደራዊ ሙያቸው ሰርተዋል። በተለይም በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ላይ የሻዕቢያ ሰራዊት አቅጣጫ እና እንቅስቃሴን የመቆጣጠር ሃላፊነት በያዘው ኢንተሊጀንስ እና ኮሙኒኬሽን መኪና ሙሉ ከነበሩ የቡድናቸው አባላት ጋር ሆነው ግዳጅ ላይ ሳሉ በአጋጣሚ ስልክ ለማውራት ዘወር ባሉበት ቅጽበት ከጠላት በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ መኪና ሙሉ የቡድን አባሎቻቸው ሲያልቁ እሳቸው ለታሪክ የተረፉ "ሞት የቀረባቸው" ወታደርም ነበሩ።

ዐቢይ አህመድ እንዲህ ያሉ ወታደር ናቸው። ኮሎኔልነታቸው፣ ከባህሪያቸው ጋር የተዛመደ እና አስፈላጊ በሆነ ጊዜም ከተቀመጠበት ስፍራ የሚወጣ የሰብዕናቸው ዋነኛ መገለጫም እንደሆነ በተለያዩ ንግግሮቻቸው ውስጥ ብቅ በሚሉ ቃላቶቻቸው እያሳዩን ነው።ለዚህም ብዙ ማረጋገጫ ፍለጋ ሳይኬድ ከራሳቸው ንግግሮች▶

ውስጥ ቆምጫጫ ወታደራዊ ባህሪያቸውን ማሳየት አይከብድም።

## ቀዳሚውን እንደማስታወሻ

የለውጡን አንደኛ አመት ምክንያት በማድረግ በኢትዮጵያ የተከናወኑትን የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት የሚገመግም አንድ ውይይት መጋቢት 13 እና 14 ቀን 2011 ዓ.ም በሸራተን አዲስ ሆቴል ተካሂዶ ነበር። አዲስ ወግ በሚል ርዕስ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት መዘጋጀት የጀመረው የዚህ ፕሮግራም የመጀመሪያ ክፍል በአገሪቱ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የሰላ ትችት እና ውይይት የተደረገበት ነበር። በዚህ የውይይት መድረክ ማጠቃለያ ቀን ታዲያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ በድንገት ወደአዳራሹ መጡ። ከዚያም በመድረክ መሪው ተጋብዘው ንግግር አደረጉ።

በዚህ ዝግጅት ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ስለውይይቱ መጀመር እና ከአደባባይ ወደአዳራሽ የዞረ የውይይት ባህል እንዲዳብር ሃሳብ ለመስጠት ነው ብሎ ያልተገመተ የለም። ንግግራቸው ግን በዚያን ሰሞን በአገሪቱ ፖለቲካ ላይ እየተካሄደ ያለ አዲስ ነገር አስቆጥቷቸው የመጡ ነው ያስመሰላቸው። በጊዜው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የአዲስ አበባን ጉዳይ አጀንዳ በማድረግ በባልደራስ አዳራሽ ከህዝብ ጋር ባደረገው ምክክር የባለአደራ ምክር ቤት ማቋቋሙ ወሬ በስፋት ናኝቶና መንግስትንም አስቆጥቶት የነበረበት ጊዜ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ታዲያ በዚያን ዕለት ባደረጉት ንግግር ከተለመደው ወጣ ባለ ጠንካራ ድምጽ፣ ቁጣ እና ቅሬታ በሚነበብበት ስሜት፣ ሃይለቃል ተጠቅመው ሃሳባቸውን ገልጸዋል።

## “ጦርነትን” እንደቀላል ቃል

በዚያን ወቅት በድንገት በውይይቱ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው ውስጥ በአብዛኛው የቁጣ፣ የማስፈራራት፣ የማስጠንቀቅ ፣ የቅሬታ እና የተስፋ መቁረጥ ድምጸቶች ነበሩ የተንጸባረቁባቸው። በንግግራቸውም “በዚያች አገር ላይ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር እሳቸው ብቻ መሆናቸው ለአፍታም ቢሆን እንዳይዘነጋ” ማስጠንቀቂያ ሰጡ።ከህግ አግባብ ውጪ ሰልጣን ለመያዝ ማንም ቢሆን እንዳያስብም አስጠነቀቁ። ልክ ናቸው። ነገር ግን የባለአደራውን ጉዳይ በመጥቀስ “ግልጽ ጦርነት ውስጥ እንገባለን” የሚል ከበድ ያለ ቃል ተጠቀሙ። እዚህ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደታች ወርደው ከእስክንድር ጋር “ግልጽ ጦርነት ውስጥ” የመግባት ፍላጎታቸውን አዝማሚያ ማሳየታቸው ለብዙዎች እሳቸው ነገሮችን ምን ያህል መታገስ እንዳቃታቸው አመልካች ነበር። በጊዜው አሜሪካ የሚኖሩ አንድ ግለሰብ በዩቱብ በለቀቁት ቪዲዮ ላይ እንደተናገሩት፣ “በብዙ የዓለም ክፍሎች በተለይም በአንደኛው አለም ያሉ የአገር መሪዎች “ጦርነት” የሚል ቃል ከአፋቸው ለማውጣት ብዙ ማሰብ የሚጠብቃቸው ነው ይላሉ። ከመገናኛ ብዙሃንም ሆነ ከተፎካካሪ ፖለቲከኞች የሚያስከትልባቸው ትችት የላቀ ነውና። በነዚያ አገራት ጦርነትን የሚያህል ቃል ያለአግባብ መጠቀም የማይገባ ባህሪ ተደርጎ ይታሰባልና” ይላሉ አስተያየት ሰጪው ። “ጦርነት ቀላል ቃል ሆኖ ከአንድ ጠቅላይ ሚኒስትር አፍ መግባቱ የሚጠበቅ ቢሆንም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ግን ወታደር ነበሩና ውጊያ እና ጦርነትን ሲጠቀሙባቸው በቀን ከቀን መግባቢያ ቃላት አረዳድ ነው። ለዚህም ነው ቀለል ብሏቸው ቃሉን ከአፋቸው ያወጡት” ብለዋል።

“ጠቅላይ ሚኒስትር ፍቅር እና ሰላምን እንደሚሰብኩ፣ አንድ የተለዩ የአገራችን መሪ ሆነው ሲታዩ ጦርነትን አማራጭ አድርገው መውሰዳቸው፤ ራሳቸው ወታደር መሆናቸውን በጎን ለህዝብ እያሳወቁና በተፈለገ ጊዜም ይህንን ወታደርነት እንደሚጠቀሙበት ማሳያ ሊያደርጉት ሽተው ነው” ብለው በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተከራከሩም በርካታ ናቸው።

## “የወታደር መንግስትነት” ፍላጎት

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ “ጦርነት እንገጥማለን” ከሚለው ቃላቸው ባሻገር “ማሰር እና መግደል” ከሚል ቃል ጋር አያይዘው የተናገሩት ቃልም በተመሳሳይ ነበር። የርሳቸውን ጠንካራ ግለሰባዊ ሰብዕና ያሳዩበት ነው የተባለው። “ማሰር እና መግደል አይቀርም” የሚል ቃል ባወጡበት በዚያ ንግግራቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዕስር እና ግድያ “ሰለቸን” በማለት ነው የጠንካራ መንግስትነታቸው ባህሪ መምጣት እንደማይቀር ምልክት የሰጡት። “አንዳንድ ችግሮችን እያዩ ትንሽ መሸከም ሳይሻል አይቀርም። ካልሆነ እሱም [እስር እና ግድያ ] አይቀርም” በማለት መንግስታቸው አማራጭ ካጣ አምባገነን መንግስት ወደመሆን ደረጃ ሊሸጋገር ይችላል የሚል እሳቤ እንዲሰርጽ አድርገዋል። አምባገነን መንግስት ደግሞ በኢትዮጵያ ደርግን የመሰለ ቅልቅል የሌለበት የ ወታደሮች ስብስብ ቀድሞ አሳይቶናል። ኋላም ብረት አንግበው፣ በጥይት ታግለው ኋላ ሲያሸንፉ ከታጋይ ዩኒፎርም ወደሲቪል ክራቫት የተቀየሩ “ውስጠ ወታደር” ኢህአዴጎች ኢትዮጵያን በጻፉት ዶክመንት ሳይሆን በታጠቁት ጠመንጃ እያሰቡ ሲመሯትም አምባገነንነትን ኖረንበታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አምባገነን ለመሆን ጫፍ ላይ ነው ያሉት፤ መንግስታቸው የደርግ ቢቀር የሁለተኛው ባለጠመንጃ ትውልድ ውጤት ነው። እሳቸው ባላቸው የተለየ አመራር ከለውጥ ሃይሉ ጋር የቀደመውን አምባገነን አገዛዝ ለውጠው ወደስልጣን መምጣታቸው በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያስገኘላቸው መሆኑን ዘንግተው ይመስላል ዳግም አምባገነን የሚሆን ባህሪ የተላበሰ መንግስት ዳር ላይ እንደቆመና ሊመጣ እንደሚችል መናገራቸው ለብዙዎች ቅቡል ሃሳብ ሆኖ አልተገኘም። ምክንያቱም ህዝብ በአምባገነንነት የተሰላቸ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ቃሉንም መስማት የማይፈልግ መሆኑ ነው። በዴሞክራሲ ማስፈን እና ግንባታ ሂደት የተቃውሞ ከመስመር መውጣት እና የቡድኖች ሂደትን ማደናቀፍ፣ ያለ ነገር ቢሆንም ይህንን የሚታገስ ባህሪ እንደሌላቸው እየነገሩን፤ በሌላ መንገድም አንድ ቀን ኮሎኔል ሆነው እንደሚመጡ እያሳዩን ነው የሚሉም አሉ።

እናም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀደመ በሸራተኑ ንግግራቸው መንግስት ‘ደክሞት’ የተወውን ዕስር እና ግድያ አማራጭ ካጣ ዳግም ሊጠቀምበት እንደሚችል በግልጽ ማመላከታቸው ከዚያ በቀደመ የማብራሪያ ንግግራቸው “የኢትዮጵያ መንግስት አምባገነን ሊሆን ጫፍ ላይ ያለ መንግስት ነው፣ አታስገድዱት ” ካሉት ጋር ተዳምሮ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሁለተኛ ሰብዕና (“ወታደራዊ” ባህሪ ) አመላካች ሆኗል የሚሉም አልጠፉም።

## ዶክተር አብይ

> ..“ይቺን ታላቅ ሃገር ሊበትኑ የሚያስቡ ሰዎች ከዚህ ሃሳባቸው ጥቃታቸውን የምንከላከል እንጂ በተፈጠረብን ትንኮሳ በከፈልነው አሳዛኝ መስዋዕትነት ሸብረክ የማንል መሆኑን ድጋሚ ለማሳሰብ እወዳለሁ... ጀግናው የመከላከያ ሰራዊት መክፈል የሚገባውን መስዋዕትነት ከፍሎ ሃገሩን ደህንነት ያስጠብቃል”

## በዳግም “ወታደራዊ ንግግር”

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ በተለይም ለውጡ ከመጣ በኋላ ከባድ የሆነው ክስተት በቅርቡ በአገራችን ያጋጠመው የከፍተኛ አመራሮች እና የጦር አዛዦች ግድያ ነው። ይህ ክስተት በአገሪቱ የፖለቲካ ለውጥ ሂደት ወቅት ከተከሰተው የ”ኦነግ ሸኔ” የባንክ ዝርፊያም፣ የምዕራብ ወለጋ ወረራም፣ በቡራዩ ከተከሰተው ማፈናቀልም በላይ፣ በጌዲዮ ከሆነው የህዝብ ስደትም በላይ፣ በሻሸመኔ ተዘቅዝቆ ከተሰቀለው ወጣትም በላይ፣ በሃዋሳ ወላይታ ወጣቶች እንደእባብ ተቀጥቅጠው ከመገደላቸውና ሳይሞቱ ሲቃጠሉ ካየነውም በላይ ፣ በአማራ ክልል የዘመተ ሃይል በቤኒሻንጉል ደቡብ ነዋሪዎችም ላይ ካደረሰው ግድያም በላይ፣ ኦነግ በደቡብ ወሎ ገብቶ ከፈጸመው ግድያ እና ቤተክርስቲያን ማቃጠልም በላይ፣ ከነዚህ እና ሌሎችም ብጥብጦች እና መፈናቀሎች፣ ስደቶች እና ጉዳቶችም በላይ አስደንጋጭ ክስተት

ሆኗል።ጠቅላይ ሚኒስትሩ “ይወጣለታል፣ ብጥብጡ የሚቀጥል ይሆናል፣ ከዚያ ወደስፍራው ይመለሳል፣ መረጋጋት ይኖራል” በማለት መንግስት እርምጃ ለመውሰድ ሆደ ሰፊ እና ታጋሽ መሆኑን ደጋግመው እየተናገሩ አሳልፈውታል።

ህዝብ “የህግ የበላይነት አልተገበረም፣ የጎበዝ አለቆች የራሳቸውን ትናንሽ መንግስታት ፈጥረዋል፣ መውጣት መግባት ብርቅ ሆኗል“ እያለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የያዙትን የተለሳለሰ አቋም ሲተች እና ብዙውም ለርሳቸው የነበረውን ድጋፍ በዚህ ሳቢያ ሲያነሳ ሁሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መራራ ንግግር ተናግረው አልታዩም።ህዝቡ “አገር በወሬ ሳይሆን አንዳንዴም በሃይል ትመራለች፣ ሰላም በልመና ሳይሆን በህግ ማስከበርም ይመጣል” እያለ ሲማረር ሁሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አልፎ አልፎ ቆጣ ከማለት በዘለለ የተናገሩት ነገር እምብዛም አልነበረም።

አሁን ግን እሳቸው እንደሚሉት “የመንግ ስታቸው ትዕግስት እና ቻይነት” እየተሟጠጠ መምጣቱንና እርምጃ እንደሚወስዱም አምርረው ይፋ አድርገዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሲቪል ማንነታቸውም በላይ በእንዲህ ያለ ቀን የክት የሆነው ወታደራዊ ማንነታቸው ጎልቶ እየወጣ ያለም ይመስላል። በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ አለመረጋጋት እና አገር አደጋ ላይ የምትወድቅበት ሂደት በዚህ ከቀጠለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገር በመምራት ደረጃ ወታደራዊ ማዕረጋቸውን ይጠቀሙበታል ማለት ሳይሆን በውስጠ አመራራቸው ጠንካራ እርምጃ ወሳጅ እና ወታደራዊ ስሜት የሚጠይቁ አመራሮችን ሰጪ እንደሚሆኑ የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ።

በነዶክተር አምባቸው እና ጄኔራል ሰዓረ ሞት እጅግ ስሜታቸው የተነካ መሆኑን በአስከሬን ሽኝት ስነስርዓት ወቅት አሳይተዋል። እልህ እና ቁጣም ተፈታትኗቸዋል። በተለይም የነዚህ አራት ከፍተኛ ባለስልጣናት በዚህ አይነት አሳዛኝ ክስተት መቀነስ ለውጡ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ እንዳለ ሆኖ፣ በዚህች አገር ማንም እየተነሳ እንዲህ ያለ እርምጃ የሚወስድ ከሆነ ነገም የራሳቸው ደህንነት አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ማሳያ ሆኗልና እሳቸውም በልዩ ሁኔታ አስተያየት ሰጥተውበታል።ከዚያ በፊት ግን ጥቃቱ ተፈጸመ በተባለበት ሰኔ 15 ቀን ሌሊት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወታደራዊ ዩኒፎርም መግለጫ የመስጠታቸውን አንደምታ እዚህ ላይ ማየት ግድ ይሆናል።

## “ዩኒፎርም ወዳጁ” ጠቅላይ ሚኒስትር

ወታደርነት ከመለዮ እና ዩኒፎርም ጋር የተቆራኘ ክብር አለው። ወታደር ሆኖ ያለፈ ሁሉ በየሰራዊቱ የሚጠቀምበትን ዩኒፎርም ያከብራል። ግርማ ሞገስ የሚያሰጠውን ፣ የሙያው መገለጫ የሆነውን እና አክብሮ ሊያስከብረው የተነሳለትን አላማ ማረጋገጫው የሆነውን ዩኒፎርም በልዩ ዐይን ያያል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ወታደርነታቸው ቀርቶ ሲቪል ቢሆኑም፣ በሲቪል ማዕረጋቸውም አገር ቢመሩም ከዚያ ሁሉ በላይ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትርነታቸው የሰጣቸው የጦር ሃይሎች ጠቅላይ አዛዥነት ማዕረግ የሲቪል ማዕረግ ቢሆንም በአንዳንድ ወሳኝ አጋጣሚዎች የወታደር ልበስ ለብሰው “ወታደር መሆኔን አትርሱ” አይነት ማስታወሻ ቢጤ እንዲፈጠር መንገድ መክፈታቸውም አልቀረም ። ለውጡን ገና ሲጀምሩ ጠበቅ ያለ ኦሬንቴሽን የሰጡት ለመከላከያ ሠራዊቱ ነው። የዛሬ አመት ክረምት ሲቃረብ ከሠራዊቱ አመራሮች ጋር በነበራቸው የስልጠና ቆይታ ወታደራዊ ሳይንስ አዋቂነታቸውን በሚገባ አስመስክረዋል። በወታደራዊ ቋንቋ ከአርሚያቸው ጋር መግባባት እንደሚችሉ እና ለማዘዝ የአውቀት ቸግር እንደሌላቸውም ለህዝቡ አሳይተውታል። መከላከያ ሰራዊትን መልሶ በማደራጀት ህብረብሄራዊ ተቋም እንዲሆን አቅጣጫ የቀየሱትና ሹመቶችንም የሰጡት በዚሁ እሳቤ ነው። እዚያ ያለውን ስራቸውን ሲከውኑ ታዲያ ወታደራዊ ዩኒፎርም መልበሳቸውን አያቋርጡም።በርግጥ የሚለብሱት ወታደራዊ ዩኒፎርም ለምዕራባውያን ወታደሮች የሚቀጠሙበት አይነት የሆነና የሃገር መከላከያ ሰራዊት የሚቀምበት አለመሆኑ ለብዙዎች ጥያቄ ቢሆንም በግምት ግን ይህንን ልብስ የሰራዊቱ ደንብ ልብስ ለማድረግ መምረጣቸውን ያሳያል የሚሉ አሉ።

በመጀመሪያ በዩኒፎርም የታዩት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት በተለቀቀ አንድ አራት ፎቶግራፋቸው ነው። መጽሃፍ ሲያነቡ፣ ቆመው እና ሲሄዱ ፎቶ የተነሱባቸው ወታደራዊ ዩኒፎርሞች በርግጥም ግርማ የቸሯቸው ነበሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ከሰኔ 16ቱ የመግደል ሙከራ በኋላ የነበራቸው ግልጽነት ተቋርጦ በከፍተኛ ወታደራዊ አጀብ ሲጓዙም የመረጡት እንደሌላው ጊዜ በሲቪል ሳይሆን ዩኒፎርም በለበሱ ሃይሎች እንዲታጀቡ ነው። የዚህ ምክንያት ደግሞ በወታደራዊ ሳይንስ ዩኒፎርሙ ከግማሽ በላይ እኩይ እቅድን ያስቀራል መባሉ ነው። ሃይልን ማሳየትና እኩይ ዕቅድን ማክሸፍ ወይም ዴተረንስ ይሉታል የሚሊተሪ ባለሙያዎች ።

**...በዚያች አገር ላይ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር እሳቸው ብቻ መሆናቸው ለአፍታም ቢሆን እንዳይዘነጋ” ማስጠንቀቂያ ሰጡ።ከህግ አግባብ ውጪ ሰልጣን ለመያዝ ማንም ቢሆን እንዳያስብም አስጠነቀቁ። ልክ ናቸው። ነገር ግን የባለአደራውን ጉዳይ በመጥቀስ “ግልጽ ጦርነት ውስጥ እንገባለን” የሚል ከበድ ያለ ቃል ተጠቀሙ...**

ከዚያ በኋላ ከኤርትራ የየብስ ድንበር ሲከፈት በስፍራው የተገኙት በወታደራዊ ዩኒፎርም ነው። ወታደር ባለበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን የሪፐብሊኩን ልዩ ዘብ ሲያስመርቁም በወታደራዊ ዩኒፎርም ታይተዋል። ብዙዎች እንደሚሉት ምዕራባውያን መሪዎችም ቢሆኑ ወታደር ሆነው አልፈዋል። ጆርጅ ቡሽ የአሜሪካ አየር ሃይል አብራሪ ነበሩ። ሌሎቹም በአሜሪካ ሚሊተሪ ውስጥ አገልግሎት ያበረከቱ ሰዎች ናቸው። ወታደራዊ ስልጠና እና ሰብዕና የመሪነት መኮትኮቻ መሆኑ በአለም ላይ ያለ ተግባር ነው። ነገር ግን በሲቪል አገር እንዲሾሙ የተሾሙ ጊዜ ይህንን ወታደርነታቸውን በዩኒፎርም ያሳዩ ማናቸውም የሉም። በአገራችን አባዱላ ገመዳ በመከላከያ አመራር ውስጥ የነበራቸው ማዕረግ ሙሉ ጄነራል ሆኖ ሳለ አቶ ተብለው ወደሲቪል ስልጣን ከመጡበት ወቅት ጀምሮ አንድም ቀን በዩኒፎርም ታይተው አያውቁም። ለዚህ ነው የጠ/ሚ/ር ዐቢይ ዩኒፎርም ማዘውተር ብዙ ጊዜ ወታደር ሆነው ሊመጡ ይፈልጉ ይሆን? የሚለውን ጥያቄ የሚያጭረው።

7 ደቂቃ በፈጀውና እንደተለመደው የማን እንደሆነ በማይታወቀው ሚሊተሪ ዩኒፎርም በሰጡት መግለጫ ላይ ምንም ቢታሰብ የሚወድቅ የለውጥ ሃይል እንደሌለ ተናግረዋል።

“ይቺን ታላቅ ሃገር ሊበትኑ የሚያስቡ ሰዎች ከዚህ ሃሳባቸው ጥቃታቸውን የምንከላከል እንጂ በተፈጠረብን ትንኮሳ በከፈልነው አሳዛኝ መስዋዕትነት ሸብረክ የማንል መሆኑን ድጋሚ ለማሳሰብ እወዳለሁ…ጀግናው የመከላከያ ሰራዊት መክፈል የሚገባውን መስዋዕትነት ከፍሎ ሃገሩን ደህንነት ያስጠብቃል” በማለት በቀጥታ ለመከላከያ ሰራዊቱ መልዕክት አስተላለፍዋል። በጊዜው ሃገሩ እንዲረጋጋም “በአዲስ አበባና አካባቢዋ በየትኛውም ስፍራ መሰል ጥቃት እንዳይፈጸም በኔ ስር ያለው ኮማንድ ፖስት ትዕዛዝ እየሰጠ ነው” ብለዋል። “ይህንን የፈጸሙ አካላት ን መሆናቸውን እየለየን እንሄዳለን” በማለትም እርምጃ እንደሚወሰድ ተናግረዋል።


## የፓርላማው ውሎ እና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማስጠንቀቂያ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ በፓርላማ የመንግስታቸውን የአንድ አመት ሪፖርት ሲያቀርቡ በዋናነት የህዝቡን ቀልብ የሳበው ነገር በወቅታዊው የሃገራችን ጉዳይ ላይ የሰጡት ማስጠንቀቂያ ነው። ማንም ቢሆን መንግስት ልገልብጥ ማለቱ የማያዋጣ ቅዠት አንደሆነ መናገራቸው ብቻ ሳይሆን የማይቻል ነገር መሆኑን ገልጸዋል።

“ማነው ማንን ፈንቅሎ መንግስት መሆን የሚችለው? አይቻልም እኮ ! ይሄ መተላለቅ ነው እንጂ.... በፌዴራል ደረጃም ቢሆን መፈንቅለ መንግስት የሚታሰብ አይደለም። በራሽናል ጭንቅላት ..አሁን ባለው ኢትዮጵያ ውስጥ መፈንቅለ መንግስት ማሰብ እብደት ነው። አይሆንም! በአንድ ጀምበር መቶ ሺህዎች የሚታረዱበት ትራጀዲ እንፈጥር ይሆናል እንጂ መንግስት መሆን አንችልም

ቀሪውን ቃለ ምልልስ በገጽ 27 ይመልከቱ

# የይድረስ ይድረስ



ፍቅርተ ተሾመ

ከሰሞኑ በመንግስት ባለስልጣናት ላይ በተቃጣው ጥቃት ምክንያት ሁለቱ ከተሞች ካለባቸው ውጥረት የረገቡ አይመስልም፡፡ በዚህም ጥቃት ሳቢያ የሰዎች ሕይወት ከማለፉ ባሻገር የመንግስታዊ ሹመት አሰላለፉን ንጦታል፡፡ አዲስ ተሹዋሚዎችንም ጠይቋል፡፡ ጠ/ሚ/ሩ በፓርላማ ንግግራቸው እንዳነሱት አገሪቱ ከተጋረጡባት ችግሮች ውስጥ አንዱ አክራሪ ብሔርተኝነትና ግጭቶች እንደሚገኙበት ገልፀዋል፡፡ ይህ ችግር እንደአገር ለመቆም አገሪቷ ሊኖራት በሚገባው የሰላም ሁኔታ ላይ ትልቅ ተግዳሮትን ይፈጥራል፡፡ በመፍትሄ ደረጃ ዘላቂና ጊዜያዊ ምላሽን ይሻሉና፤ በተግባርም እየተሰራ ላለው የዘላቂ እና ጊዜያዊ መፍትሔ አሰጣጥ ላይ ማሳያ የሚሆነን አሁን ላይ በመንግስት እየተሰራ ያለው አንዱ መፍትሔ ሹመትን በብሔር ስብጥር ማድረግ ነው፡፡ ይህ ለሌሎች ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ላይ የሚያመጣው የራሱ ተግዳሮቶች ሳይዘነጉ ማለት ነው፡፡ የሰኔ 21ዱ የደህንነት እና የመከላከያ ኃላፊዎች ሹመት፤ የብሔር ስብጥርን ለማስማማት በሚመስል ሁኔታ የሹመት ጨዋታው ከክበቡ ሳይወጣ በዛቢያው ላይ እየተሽከረከረ መሄዱን መርጧል፡፡ አንድ መሪ በዙሪያው የሚሾማቸው አካላት እራሱን መሳይ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በአንድም በሌላም መልኩ የአገሪቱ ፖሊቲካ የ"ሴራ" መሆኑን ማሳያው የተሹዋሚው እና የሹዋሚው መመሳሰል ብቻም ሳይሆን፣ የሴራው ውጤት የሆነው ጆከሩ ብሔር የሚመዘዝበት አጋጣሚ መብዛቱ ነው፡፡

እንዲህ ባሉ አጋጣሚዎች በብሔር ንክኪ ብቻ ወደ ኃላፊነት ማምጣቱ የታችኛው መዋቅር አመሰራረት ላይ ችግርን ማስከተሉ አይቀሬ ነው፡፡ እነዚህ ተሹዋሚዎች የብሔርን ስራ ከታች አይከውኑም ብሎ የሚከራከር መኖሩ ያጠራጥራል፡፡ ይህ እውነት በተግባርም ከስር ባሉት ተቋማት የስራ መዋቅሮች ሁሉ እየተነበበ ይገኛል፡፡ እንደቀድሞው የኢህአዴግ ስርዓት ሹመት አይነት የፈጠጠ ደረጃ አለመድረሱ የሚካድ ባይሆንም መንገዱን በዛ መልክ እየጠረገ እንደማይቀር መገመት ይቻላል፡፡ ከላይ የስብጥሩ ሂደት ባላንሱን የጠበቀ ቢመስልም፣ ይህ ግን በመዋቅር ደረጃ በታችኛው አመራር ላይ አይታይም፡፡ ጠ/ሚ/ሩ ከላይ ስብጥሩን ሲጨነቁበት፣ ስብጥር የመስራቱን አስፈላጊነት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የአንድነት ሃሳብ ጋር ሊቃረን እና በተመሳሳይም ሊጣጣም የሚችልባቸው መንገዶች እንዳሉ ማየት ተገቢ ነው፡፡ ጠቅላዩ ካቀዱት የኢትዮጵያዊነት ዝማሬ ጋር ብሔር ተኮር የስልጣን ስብጥር ከነባራዊው ድርጊታቸው ጋር መቃረኛው ምክንያት ሲሆን፣ ከአጭሩ እና ጊዜያዊው የሰላም ማስፈን ስራ ጋር ደግሞ ስምሙ የሆነ ይመስላል፡፡ ስብጥሩ እንደማስጨነቁ ሁሉ ከሆነም በኃላ የሚያስከፍለውን ዋጋ ማየትም ተገቢ ይሆናል፡፡ ለአንዳንድ ቦታዎች በትክክል ለቦታው የሚገጥሙ ግለሰቦችን፣ በዘራቸው አንድ አይነት ሆነው ለተለያዩ ቦታዎች በተመሳሳይ ጊዜ ብቁ ሆነው ቢገኙ የዘርስብጥር መኖር አለበት በሚል የማሚያ ክራይቴሪያ ምክንያት፣ ከጥራት ብዛት ላይ ያለስህተት መስራት ይሆናል፡፡ ይህ የስብጥር ጉዳይ በከፍተኛ አመራር ላይ የሚነሳ ይሁን እንጂ የታች መዋቅሩ የስብጥሩም ነገር ህልም ሆኖበታል፡፡ በተለያዩ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች እየታየ ያለውም ይህ ስብጥር አልባ የአንድ ወገን የበላይነት ነው፡፡ የተያዘው የቀድሞውን ብልሹ አሰራር መለወጥ ከሆነ እንዴት? ለሚለው "መተካካት መልስ የሆነ ይመስላል"፣ መልሰው ለለውጥ ካልዘመቱበት በቀር፡፡

የይድረስ የይድረስ ስራ ውሃ የሚቋጥር ፍሬ ሲያፈራ አይታወቅም፡፡ በፓርላማ ውሎአቸው ከአክራሪ ብሔርተኝነት ጋር አያይዘው የማንነትና የአደረጃጀት ጥያቄዎችን፣ የዜጎችን መፈናቀል፣ ሕገ ወጥ የመሣሪያ ዝውውር፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሁለንተናዊ (ዩኒቨርሳል) እሴቶችን ከማቀንቀን ይልቅ ወርደው ወደ እርስ በርስ ግጭቶች ውስጥ መግባት፣ የሚዲያ ጽንፈኝነትና በከተማ ውስጥ የተደራጁ ወንጀሎችና የኢኮኖሚ አሻጥሮችን እንደችግር አቅርበዋል፡፡ በመሆኑም ያሳኩዋቸውን የመፍትሔ ሃሳቦችም፤ አመራሮችን በማንሳት አሠራሮችን በማስተካከል፣ ተቋማዊ መዋቅሮችን በፍጥነትና በስፋት በመገንባት የማደስ ዕርምጃዎች መውሰዳቸውን በማብራራት አምነዋል፡፡ እነዚህ ስራዎች ቀድመው የተበከሉ እና አሁን ላይም እየተፈጠሩ የቀጠሉ መሆናቸው ይታወቃል፤ በሌላ በኩል ጊዜያዊ መፍትሄ የሚያሻቸው እና ዘላቂ መፍትሄው ላይ አተኩሮ መስራትን የሚሹ ጉዳዮች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ አክራሪ ብሔርተኝነት የፖለቲካ መነገጃ መሆኑን ግንዛቤው ያልተፈጠረላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ባሉበት ሁኔታ የአንድነትን ጉዳይ ማውራት ለእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ሃሳቡን በግድ እንደመጫን ይቆጠራል፤ ይሄ ደግሞ የዴሞክራሲን ጉዳይ ገደል ይከተዋል፡፡ የማንነት እና የአደረጃጀት፣ የመፈናቀል እና የመሳሪያ ዝውውር እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፍሬ ቢስነት የዚህ ሁሉ ችግሮች ስረ መሰረት ይህ የብሔርተኝነት ፖለቲካ ንግድ ነው፡፡ ንግዱ ደግሞ የእጁ ርዝመት ህገ መንግስቱ ላይ ፊጥ እንዲል አድርጎታል፡፡ ስለዚህ ሃያ ስድስት አመት የተበከለን አስተሳሰብ የአሁኑ አሰራር ላይ ቀጥተኛ እክል መፍጠሩ እየታየ፣ ዘላቂ ለውጡ ላይ ከማተኮር ይልቅ ጊዜያዊው ላይ ማተኮር አቅም የሚጠይቅ ሁኖ ሳለ፣ ከምንም በላይ ትኩረትን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ ላይ ብዙ ሲባልበት ቆይቷል፡፡ ችግሩ ከተግባሩ ላይ ነው፡፡ እንግዲህ ስለአንድነት ሲወራ በአንድነት ማሰብና የጋራ እሴትን ማጉላት ይጠይቃል፡፡

**... የስብጥሩ ሂደት ባላንሱንየጠበቀ ቢመስልም ይህ ግን በመዋቅር ደረጃ በታችኛው አመራር ላይ እየታየ አይደለም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከላይ ስብጥሩን ሲጨነቁበት ስብጥር የመስራቱን አስፈላጊነት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የአንድነት ሃሳብ ጋር ሊቃረን እና በተመሳሳይም ሊጣጣም የሚችልባቸው መንገዶች እንዳሉ ማየት ተገቢ ነው...**

አሁን ላይ ህዝብ እያስተናገደ ያለው ‹‹የህልውና ጥያቄ›› በተለያየ መንገድ ጥያቄ ውስጥ መውደቁ መንግስትም ይሁን የፖለቲካው ነጋዴዎች በተለያየ አውድ የሚያነሱት ጥያቄ ነው፡፡ ህዝብ መፍትሔ ይፈልጋል፣ ለመፍትሔው መልስም በተግባር ይፈልጋል፡፡ መልስ ስንል የዘላቂ መፍትሔ ሂደትንም አካቶ ማለት ነው፤ ይሄ ግን በነጋዴዎች ሲጠለፍ ትውልድ ያከስራል፡፡

የአገር ባለቤትነት የአደራ ነው፡፡ ያለፈው በኃላፊነት ያስረክባል፤ የሚመጣው በኃላፊነት ኖሮ ያስቀምጣል፤ ለቀጣይ ትውልድም በኃላፊነት ያስረክባል፡፡ በዚህች አገር መልካም አስተዳደር እና የህልውና ጉዳይ ዘላቂነቱ እና መሰረትያለው መሆኑ ኃላፊነትን የመወጣት ጉዳይ ነው፡፡

# “ዳንዲ ኦነግ” የኦነግ መንገድ



በታምራት መርጊያ

በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ በበጎም ይሁን በአሉታዊ መልኩ ስማቸው ጎልቶ ከሚነሱና አወዛጋቢ ከሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል “የኦሮሞ ነጻነት ግንባር” (ኦነግ) አንዱና ግንባር ቀደሙ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም:: ለመሆኑ “ኦነግ” ማነው? የድርጅቱ የኋላ ታሪክስ ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ለዛሬ የድርጅቱን (የኦነግን) ከአርባ ዓመታት በላይ የዘለቀ የትግል ጉዞ ሂደትና ታሪክ፣ ከብዙ በጥቂቱ ለአፍታ በመፈተሽ የድርጅቱን አሁናዊ ሁኔታ ለመገምገም እንሞክር:: መልካም ንባብ::

የኦሮሞ ህዝብ ትግል በ19ኛው ክፍለ ዘመን የዘመነ መሳፍንት እና የተስፋፊነት ወቅት የአጼ ምንሊክን ጦር ወደ ደቡብ አቅጣጫ የመስፋፋት አካሄድ ተከትሎ የተጀመረ እንደነበር የታሪክ አጥኚዎች ይገልፃሉ:: የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚገልጹት ከሆነም የኦሮሞ ማህበረሰብ የትግል መነሻና ማጠንጠኛ የሆነው ”የሰፋሪዎች ቅኝ ግዛት” ወይም በእንግሊዝኛ አጠራር “settler colonialism” የተሰኘ የቅዋሜ ሀሳብ ነበር::

> ...የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚገልጹት ከሆነም የኦሮሞ ማህበረሰብ የትግል መነሻና ማጠንጠኛ የሆነው ”የሰፋሪዎች ቅኝ ግዛት” ወይም በእንግሊዝኛ አጠራር ”settler colonialism” የተሰኘ የቅዋሜ ሀሳብ ነበር...

የዚህ የተቃውሞ ሀሳብ ጭብጥ ሲተነተን፤ ነባር ማህበረሰቦችን ከቀዬአቸው በማስነሳት፣ በምትካቸው በሌሎች የተሰፋፊዎቹ ወገኖች በሆኑ ማህበረሰቦች የመተካትና፤ የራሱ የሆነ አይነተኛ መለያ ያለው የወረራና የቅኝ ግዛት ተግባር መሆኑን ምሁራን ያስረዳሉ::

በ1960 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ንጉሳዊ አገዛዝ የኦሮሞ እራስ አገዝ ማህበር የነበረውን “ሜጫ እና ቱለማ” የተሰኘ ማህበር ህገወጥ ማህበር ነው ሲል ፈረጀው:: ይህንንም ተከትሎ ንጉሳዊ ስርዓቱ በርካታ የኦሮሞ ተወላጅ ወጣቶችን የሜጫና ቱለማ አባል ናችሁ በሚል ሰበብ የዘፈቀደ የጅምላ ዕስርና የግድያ እርምጃዎችን መውሰድ ጀመረ::

ከዚህ ባሻገርም ከፍተኛ የሚሊተሪ እንዲሁም የሜጫና ቱለማ ራስ አገዝ አመራርና አባላትን ወህኒ እንዲወርዱ አደረገ:: ከነዚህ የወቅቱ ታሳሪዎች መካከል ታዋቂው ጀነራል ታደሰ ብሩ አንዱ ነበሩ:: ይህ የመንግስት ግብታዊ እርምጃ ሜጫና ቱለማ የተባለውን የኦሮሞ ተወላጆች እራስ አገዝ ድርጅት በሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ያለውን ታዋቂነትና ህዝባዊ ተቀባይነት በእጅጉ አናረው:: ይህም በፊናው ጀነራል ዋቆ ጉቱ ይመሩት ለነበረው የባሌ ገበሬዎች አመጽ እንዲቀሰቀስ ምክንያት ሆነ::

በ1667 ዓ.ም የፈነዳው የኢትዮጵያ አብዮት የንጉሳዊ አገዛዙን ግብዐተ መሬት በመፈጸም በምትኩ የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ወታደራዊ አገዛዝ ደርግ ወደ አገሪቱ የስልጣን ማማ ላይ በማውጣት፣ በጓሮ በር አራት ኪሎ ቤተ መንግስት እንዲገባ አደረገው:: ይህ አጋጣሚ በሜጫና ቱለማ ራስ አገዝ ማህበር ውስጥ አመራር የነበሩና በኋላም በንጉሳዊው ስርዓት ተይዘው ወህኒ ወርደው ለቆዩ ታሳሪዎች ከእስር ለማምለጥ መልካም አጋጣሚን ፈጠረላቸው:: እነኚ የታሰሩበትን እግረ ሙቅ መበጣጠስ የቻሉ ከፍተኛ የሜጫና ቱለማ የአመራር አባላት ከዕስር መልስ የትግላቸውን ስልት “ከራስ አገዝ ማህበር” ወደ “ፖለቲካዊ መስመር” ቀየሩ:: በአገር ውስጥ በህቡዕ የተሟጋችነት ወይም “Activism” እንቅስቃሴዎችን በማካሄድ እንደነ “ቄና በከታ” እና “The Oromo Voice Against Tyranny” የተሰኙ ጋዜጣዎችን እያሳተሙ ለህብረተሰቡ በስፋት እንዲሰራጩ በማድረግ፣ በስውር የኦሮሞን ማህበረሰብ ለትግል የማንቃት፣የማደራጀት ስራን አጥብቀው ተያያዙት:: ከዚህ እንቅስቃሴ በተጓዳኝም እንደነ ሁሴን ሶራ፣ ኢሊሞ ቂሊጡ እና ሌሎች የኦሮሞ እንቅስቃሴ ጉምቱ መሪዎች የተሳተፉባቸው ስብሰባዎችን በህቡዕ ለማካሄድ ቻሉ::

የኦነግ (ኦሮሞ ነጻነት ግንባር) ኦፊሴላዊ ዉልደት የሆነውና የድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራም ጽሁፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰነድ ተጽፎ እንዲዘጋጅ ማድረግ የቻለውም በነዚሁ ስብሰባዎች አማካኝነት እንደነበር የድርጅቱ የኋላ ታሪክ ያመላክታል:: ከዚህ በተጓዳኝነትም የድርጅቱ ታጣቂ ቡድን በ”ጨርጨር ተራራ” ላይ የድርጅቱ አንድ ክንፍ ሆኖ (Waraanna Bilisummaa Oromo/ WBO) በሚል ስያሜ ወይም The Oromo Liberation Army/ OLA በመባል ተመሰረተ::

ይህ የድርጅቱ ተዋጊ ክንፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢሊሞ ቂልጡ ወይም በሌላ ስሙ ሁሴን ኢብራሂም እየተባለ በሚጠራው የድርጅቱ መስራችና ነባር ታጋይ ይመራ እንደነበር ይነገራል::

በ1969 ዓ.ም ደግሞ ከንጉሳዊው ስርዓት ዕስር አምልጠው የነበሩት፣ በኦሮሞ ህዝብ የትግል ታሪክ ውስጥ እንደ ነጻነት ታጋይ በተምሳሌትነት በጉልህ የሚጠቀሱትና የድርጅቱ ቀኝ እጅ የነበሩት፤ እውቁ ጀነራል ታደሰ ብሩ ፣ከነ ኦቦ ሃይሉ ረጋሳ ጋር በመሆን ከኦነግ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በድጋሚ በደርግ የወታደራዊ አስተዳደር በቁጥጥር ስር ውለው ግድያ ተፈጸመባቸው::

ምንም እንኳን የነጀነራል ታደሰ ብሩ መያዝና መገደል በኦሮሞ ነጻነት ግንባር ላይ ከፍተኛ የሞራል ጉዳትና ፖለቲካዊ ኪሳራን አስከትሎ የድርጅቱን እንቅስቃሴ ሊያዳክመው ይችላል የሚል እምነት በወታደራዊ አገዛዙ ዘንድ ቢያሳድርም፤ ኦነግ ከመዳከም ይልቅ የተደራጀ ፖለቲካዊ ቅርጽና መዋቅር እየያዘ ትግሉን ይበልጡኑ አጠናክሮ ለመቀጠል ቻለ::

በአጠቃላይ ኦነግ ከ1960 እስከ 1970ዎቹ በዘለቁት ዓመታት ራሱን እንደገና በማጠናከር፣ በማደራጀት 41 (አርባ አንድ) አባላትን ያካተተ የድርጅቱን ማዕከላዊ ኮሚቴ በመምረጥና “ሸኔ” በመባል የሚታወቅ 5 (አምስት) ያህል የድርጅቱን ፖለቲካና ታጣቂ ኃይሉን የሚመሩ ከፍተኛ አመራሮችን በመሰየም፤ ይበልጡኑ ተጠናክሮ ቀረበ:: አምስቱ የድርጅቱ ከፍተኛ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ (ሸኔ) አባላት፤ የዛሬው የኦዴግ (የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር) ሊቀመንበር አቶ ሌንጮ ለታን ጨምሮ ሙሄ አብዶ፤ ባሮ ቶምሳ፤ መገርሳ ባሪ እና ገዳ ገመዳ የተካተቱበት ነበር::

ይህንንም ተከትሎ ድርጅቱ አያሌ የኦሮሞ ተወላጆችና ተማሪዎችን ስለ “ኦሮሞ ብሔርተኝነት” (Oromo nationalism) በማስተማርና የኦሮሞን ማህበረሰብ በማንቃት የተሳካ ዘመቻ ለማድረግ መቻሉ ይነገራል::

በ1970ዎቹ ዓመታት ውስጥ የኦሮሞ ነጻነት ►

ግንባር ድርጅታዊ አድማሱን እያሰፋ ሄዶ ከኢትዮጵያ ውጭ ሱዳን ላይ የድርጅቱን ቢሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ ለመክፈት በቃ:: በዚህ የድርጅቱ ግስጋሴ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ የገባው ደርግ ኦነግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት፣ ህዝባዊ መሰረቱን ለማክሰም በማሰብ በበርካታ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ የጅምላ ግድያና የዘፈቀደ ዕስር በመፈጸም ያልተሳካ ሙከራ አደረገ:: ይህ የደርግ እርምጃ በወታደራዊው መንግሥት ላይ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ኪሳራን በማስከተል፣ በተቃራኒው ለኦነግ በበርካታ የኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍና ተቀባይነት በማስገኘት ያልታሰበ ፖለቲካዊ ትርፍን አስገኘለት::

አጋጣሚውን በሚገባ የተጠቀመበት ኦነግ፤ የኦሮሞ ወጣቶች ትግሉን እንዲቀላቀሉ ውጤታማ የፕሮፓጋንዳ ስራን በመስራት ተዋጊ ኃይሉን ከመቶዎች ወደ አስር ሺዎች ለማሳደግ ቻለ:: በዚህም ምክንያት ድርጅቱ በደቡብ ምዕራብ እና በምስራቅ ኦሮሚያ ያሉ ቦታዎችን ለመቆጣጠር የቻለበትን ድል ለማስመዝገብ በቃ:: በተጨማሪም እንደ ጅጅጋ፣ አሶሳ፣ ደምቢዶሎ እና መንዲ ባሉ ቀጠናዎች ላይም ተጨማሪ ቢሮዎችን ማቋቋምና የውጊያ ቀጠናዎችን ለማስፋት ቻለ::

ኦነግ በነዚህ ዓመታት ውስጥ የመስፋፋቱን ያክል ከመንግሥት ጋር ባካሄደው ውጊያ እንደነ ሙሄ አብዶ፣ ሳርቱ ዩሱፍ፣ ከበደ ደምሴ፣ ባሮ ቶምሳ እና ጁኪ ባሬንቱን የመሳሰሉ ጉምቱ አመራሮቹን ጨምሮ በርካታ የኦሮሞ ተወላጆችን ለሞት በመገበር በድርጅቱም ሆነ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሞትና ከፍተኛ የንብረት ኪሳራዎችን ያስከተለ፤ ድርጅቱንም ሆነ የኦሮሞን ህዝብ መስዋዕትነት ያስከፈለ ውድ ዋጋም ከፍሏል::

የ1980ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ደርግ መራሹ ወታደራዊ መንግስት ኦነግን ጨምሮ ከሻዕቢያ እና ሕወሓት በየአቅጣጫው የሚደርስበትን ጥቃት ለመቋቋም ክንዱ እየዛለ ለመውደቅ መንገዳገድ የጀመረባቸው ዓመታት ነበሩ:: በዚህ ግዜ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከተቀሩት አማጺ ኃይላት ጋር ህብረተሰብ በመፍጠር ከግራ ከቀኝ "ለጌሾ ወቀጣ ማንም ሰው አይመጣ" እያሉ የተዳከመውን የደርግ አገዛዝ ከዚህም ከዚያም ክፉኛ ይደቁሱት ያዙ::

በ1982 ዓ.ም ሕወሓት የደርግን መውደቅ አይቀሬነት አስቀድሞ በመገንዘብ በቀጣይ መላ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር በማሰብ በርካታ በብሔርተኝነት የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶችን ማቋቋም ጀመረ::

በዚህ ረገድ ሕወሓት በተለይም ኦሮሚያን ለመቆጣጠር እንዲረዳትና ምቹ መደላድል ከወዲሁ ለመፍጠር እንዲያስችላት ኦነግን ማጥፋት ወይም ሌላ ከኦነግ አንጻር በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና የሕወሓትን ተልዕኮ በእጅ አዙር ማስፈጸም የሚችል ታማኝና ተላላኪ የሆነ፣ በኦሮሞ ተወላጆች የተዋቀረ ተገዳዳሪ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅት በማቋቋም ኦነግን የማዳከም ስትራቴጂን የመከተል አስፈላጊነትን አመነችበት::

በዚሁ መሰረት በ1982 ዓ.ም ተከዜ ወንዝ ላይ "የኦሮሞ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት" ወይም "ኦ.ህ.ዴ.ድ" እየተባለ ይጠራ የነበረውን ድርጅት በራሷ አምሳል ቀርጻና፤ በራሷ ልክ ሰፍታ ስትንፋስ ዘራችበት::

በተጨማሪም ሕወሓት እስትንፋስ ዘርታ፥ በራሷ ቁመናና ልክ ሰፍታ ያቋቋማቸውን ሎሌች ድርጅቶች በአንድ ልጥ በማሰር ለመቆጣጠርና እንዳሻት ለመጋለብ ያመቻት ዘንድ ከኦሮሚያ ኦህዴድን፤ ከአማራ ብአዴንን፤ ከደቡብ ደህዴንን እንዲሁም እራሷን አባል በማድረግ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) በሚል ስያሜ ሁሉንም ሕወሓት ሰራሽ ድርጅቶች በአንድ የሚያስተሳስር የግንባር ድርጀት አቋቋመች:: በአናቱም አብዮታዊ ዴሞክራሲ የተሰኘ ውጥኗን ሊያሳካ የሚችል ጨው ነሰነሰችበት::

ይህንንም ተከትሎ ሕወሓት ሰራሹ ኢህአዴግ ትግሉ ሰምሮለት፣ ትግራይ እና አማራ ክልል ላይ የነበረውን የደርግ መንግስት ከደመሰሰ በኋላ ትግሉን ለማስፋት ፊቱን ወደ ኦሮሚያ ክልል አዙሮ ነቀምት ከተማን ለመቆጣጠር ፣ኦሮሚያን ነጻ ማውጣት የሚል እቅድ ነድፎ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመረ:: ይህ የኢህአዴግ ተግባር የኦነግን አመራሮች ክፉኛ አስቆጣ:: በምላሹም እ.ኤ.አ አፕሪል 15/1991 የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጀርመን አገር በሚገኝ "የኦሮሞ ነጻነት ድምጽ" ራዲዮ የኢህአዴግን እንቅስቃሴ በጽኑ እንደሚቃወም ድርጅታዊ መግለጫ እስከማውጣት ደርሶም ነበር::

በወርሃ ግንቦት 1983 ዓ.ም በአገረ እንግሊዝ ሎንዶን ከተማ በአሜሪካዊው ኸርማን ኮኸንና ዴቪድ ሺን አደራዳሪነት ኦነግ፣ ሻዕቢያ እና ሕወሓት ከደርግ ልዑካን ጋር ለድርድር ተቀመጡ:: ሆኖም የኢትዮጵያን መንግስት ወክለው የመጡት የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ተስፋዬ ዲንቃና አሻግሬ ይግለጡ የኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን አገር ጥሎ የመኮብለል ዜና እዚያው ሎንዶን ላይ ሆነው በመስማታቸው ድርድሩን ትተው እራሳቸውን የሚሸሽጉበትን ቦታ ይፈልጉ ያዙ::

በዚህም ምክንያት ድርድሩ በሦስቱ አማጺያን መካከል ብቻ እንዲካሄድ ሆኖ ሻዕቢያ በኤርትራ ሪፈረንደም እንዲያካሂድ ሲወሰንለት፤ ኦነግ ግን ሻዕቢያ በኤርትራ ያገኘውን አይነት እድል አግኝቶ ኦሮሚያን እንዳይገነጥል ሕወሓት እምቢኝ በማለት የኦነግን እቅድ አከሸፈች:: ባይሆን ኦነግን ጨምሮ ሌሎች ተቃዋሚ ሐይሎችን ያካተተ አዲስ የኢትዮጵያ መንግስት መመስረት እንደሚቻል በሕወሓት በኩል ሐሳብ ቀረበ::

> ...ኦነግ ከጅምሩ አንስቶ የኦህዴድን መቋቋም ፈጽሞ ቀልቡ አልውደደውም፤ ምቾትም አልሰጠውም ነበር። ከጅምሩም ቢሆን ሕወሓት ኦህዴድን ያቋቋመበት ዐቢይ ምክንያት ኦነግ በኦሮሚያ የገነባውን ቅቡልነት በመሸርሸር፣ የድርጅቱን ህዝባዊ ተቀባይነት ለማክሰምና ህልውናውን ለማሳጣት ነው የሚል እምነትም አድሮበት ነበር...

ይህ ሐሳብ ለኦነግ ባይጥመውም ቃር ቃር እያለውም ቢሆን ውጦት ከሕወሓት ጋር ሃይሉን በማስተባበር አዲስ አበባንና የተቀሩ ነጻ ያልወጡ የአገሪቱን ቦታዎች ከደርግ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነጻ ለማውጣት፣ በደርግ አስከሬን ሳጥን ላይ የመጨረሻውን 24 ቁጥር ሚስማር ለመምታት የጋራ እንቅስቀሴ ለማድረግ ተስማማ::

በዚህ መሰረትም ሐሳባቸው ተሳክቶና ውጥናቸው ሰምሮ አዲስ አበባ የገቡት ሕወሓት እና ኦነግ፥ ቀድመው ለንዶን ላይ በተስማሙት መሰረት ሌሎች የኢትዮጵያ ሐይሎችን አካትተው ብሔራዊ የውይይት መድረክ ለማካሄድ እና የሽግግር መንግስት ለማቋቋም ቻሉ:: በዚህ አግባብም በውላቸው መሰረት የኦሮሞ ነጻነት ግንባታ (ኦነግ) በሽግግር መንግሥቱ ውስጥ ከኢህአዴግ በመቀጠል በሽግግር መንግሥቱ ውስጥ የአገሪቱ ሁለተኛ ባለከፍተኛ ወንበር ፓርቲ ለመሆን በቃ::

ይሁን እንጂ ሕወሓትና ኦነግ ፈጽሞ ሰላማዊና የሰመረ ግንኙነት ሊኖራቸው አልቻለም::

የአለመግባባቱ ቀዳሚ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው ደግሞ፤ ሕወሓት በኦሮሞ ብሔርተኝነት ስም ያቋቋመችው የቀድሞው ኦህዴድ የዛሬው የነ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ኦ.ዴ.ፓ ነበር:: ኦነግ ከጅምሩ አንስቶ የኦህዴድን መቋቋም ፈጽሞ ቀልቡ አልውደደውም፤ ምቾትም አልሰጠውም ነበር:: ከጅምሩም ቢሆን ሕወሓት ኦህዴድን ያቋቋመበት ዐቢይ ምክንያት ኦነግ በኦሮሚያ የገነባውን ቅቡልነት በመሸርሸር፣ የድርጅቱን ህዝባዊ ተቀባይነት ለማክሰምና ህልውናውን ለማሳጣት ነው የሚል እምነትም አድሮበት ነበር:: እየቆየም በሁለቱ ድርጅቶች (በህወሃት እና ኦነግ) ታጣቂዎች መካከል ግጭት መቀስቀስ ጀመረ::

በዚህ ክፉኛ የተቆጣው ኦነግ በ1984 ዓ.ም ይፋዊ በሆነ መንገድ በአባላቱ ላይ ግድያና እንግልት እየደረሰ እንደሚገኝ ገልጾ እራሱን ከሽግግሩ መንግስት ማግለሉን አሳወቀ:: ይህንን ተከትሎ ሕወሃት መራሹ የኢህአዴግ መንግስት፣ ባልተዘጋጀበት ሁኔታ ካምፕ ገብቶ በነበረው የኦነግ ሰራዊት ላይ ድንገተኛና ቅጽበታዊ ጥቃት በመፈጸም ከፍተኛ ጉዳትና ኪሳራ ለማድረስ ቻለ:: በዚህም የኦ.ነ.ግን ተዋጊ ኃይል አቅም

ቀሪውን በገጽ 18 ይመልከቱ


## አንደበት

“ግብፅ ሊገባ የነበረው ፓልም ዘይት ለምግብነት ሳይሆን ለሳሙና ፋብሪካ ግብዓት እንዲሆን ነበር፣ ግን እኛ አገር ገብቶ ለምግብነት ዋለ። ያን ጊዜ በዚህ ጉዳይ ኢንቮልብ ያደረጉት የገንዘብ ሚኒስትሩ ነበሩ። እሳቸው ናቸው ይህ እንዲሆን ያደረጉት የግዢ ኤጀንሲና የገንዘብ ሚኒስቴር ሰዎች መጡ; ጅቡቲ ላይ ተደራድረው መርከቡ ወደ ጅቡቲ መጣ ዘይቱ ወደ ኢትዮጵያ ገባ ለምግብነት ዋለ ይሄው ነው። እንዴት ይሄ ምግብ ሆኖ ይገባል ብለን ተቃወምን አይ ምግብ ይሆናል ብለው አስገቡት። ይህንኑ ጉዳይ ለጠ/ሚኒስትሩ አሳውቂያቸዋለሁ እሳቸው ግን ይጣራል ብለው ዝም ነው ያሉት”



**ምባሳደር ሱሌይማን ደደፎ**
**ሸገር ታይምስ መጽሔት ሰኔ 2011 ዓ.ም**

“አዲስ አበባ የአዲስ አበባውያን ናት” የሚለው ለእኔ ትክክል ነው። የትም ሀገር ቢኬድ አንድ ከተማ የነዋሪው ነው። 98 ወይም 99 በመቶ አማርኛ ተናጋሪ ህዝብ እንደሚኖርበት እየታወቀ፣ ሌላ ማሰብ ተገቢ አይደለም። ዐማርኛ የማይሰማ በከተማዋ ውስጥ ካለ፣ ወይ ሆን ተብሎ ነው፣ ወይ ደግሞ ወደ ከተማዋ ከገባ ገና ጥቂት ጊዜው ነው፤ በአዲስ አበባ 6 ወር ከተኖረ ዐማርኛ ይለመዳል። ሱማሌዎች ቦሌ ሚካኤልና 24 ብትሄድ፣ ዐማርኛን ለምደው በዐማርኛ ነው የሚግባቡት። የአዲስ አበባ ህዝብ እራሱ በራሱ ማስተዳደር የሚችል ህዝብ ነው። ህዝቡ አዲስ አበባዊ ስነ ልቦና ያለው ኢትዮጵያዊ ነው።”



**አቶ ታዬ ቦጋለ /“የመራራ እውነት” መጽሐፍ ደራሲ/**
**ኢትዮጲስ ጋዜጣ ሰኔ 23 ቀን 2011 ዓ.ም**

“አንዴ እድሉ ደረጃ ሲናገር ሰምቻለሁ።... ከክፍሌ ጋር ለ ቢ ምርጫ ስንሄድ ወደ 2 ሺኅ ታዳጊ ይመዘገብ ነበር ሁሉም ስለሚችሉ መምረጥ ይከብደናል. አሁን ግን ታች ሄጄ ሳይ የመጡት 100 አይሞሉም አንዱም ግን አይችልም አለ.... ችግሩ ታዲያ የሜዳ ችግር ይሁን ትውልዱ ወይም ተስፋ መቁረጥ በዝቶ አሊያም ታች ያለው ስልጠና አልገባኝም... ያኔኮ ትውልዱ ወደ ኳስ ያዘነብላል ሜዳ እንደ ጉድ ነበር አሁን ግን ያ ሜዳ የለም ይሄ ትልቅ ችግር ነው... ሌላው ደግሞ ተጨዋቹ እስከ 13 ዓመቱ ድረስ በራሱ ሊጫወት ይገባል። ከዚያ በኋላ ቢሰለጥን ይሻላል ባይ ነኝ አለበሊዚያ በአሰልጣኙፍላጎት ይቀረፅና ያለውን ተሰጥኦ ያጣል ይሄ ነው”



**አሰልጣኝ ክፍሌ ቦተና (ሰበታ ከተማ)**
**ሀትሪክ ጋዜጣሰኔ 26 ቀን 2011 ዓ.ም**

“በየክልሉ የሚሊሻ ጦር፣ የፀጥታ ኃይል እየተባለ የሚጠራው የሕግ የበላይነትን ለማስከበር ነው ሲባል እሰማለሁ። አይደለም። በጦር የሕግ የበላይነት አይከበርም። የህግ የበላይነት የሚከበረው በሕግ ነው። ሕግን ደግሞ በግንባር ቀደምትነት የሚያስከብረው ፖሊስ ነው። በክልል ፕሮፌሽናል ፖሊስ ለማደራጀት ገንዘብ ብታወጣ ይስማማኛል። ፕሮፌሽናል ፖሊስ ብታደራጅ ልክ ነው እላለሁ። ነገር ግን ሚሊሻና ልዩ ኃይል እያልክ የምታደራጅ ከሆነ የተለየ ዓላማ አለህ ብዬ ነው የምጠረጥረው።”



**አቶ ሞላ ዘገየ /የሕግ አማካሪና ጠበቃ/**
**ሪፖርተር ጋዜጣ ሰኔ 23 ቀን 2011 ዓ.ም**

## ይህን ያውቃሉ?

# ‹‹ላቲን አሜሪካ›› እና ‹‹ደቡብ አሜሪካ››

ላቲን አሜሪካ እና ደቡብ አሜሪካ ልዩነት እንዳላቸው ያውቃሉ.....? ለብዙዎቻችን እንግዳ ይሁን እንጂ ላቲን አሜሪካ ሙሉ በሙሉ ከደቡብ አሜሪካ ጋር ተመሳሳይ አይደለም። ላቲን አሜሪካ የተሰኘው መጠሪያ ከጂኦግራፊ አቀማመጥ ይልቅ ባህልን የሚገልፅ ነው። ላቲን አሜሪካ ተብለው የሚጠሩት ከደቡብ አሜሪካ ሀገራት በተጨማሪ ሜክሲኮ፣ ማዕከላዊ አሜሪካና ካሪቢያንስ የመሳሰሉ በጂኦግራፊ የሰሜን አሜሪካ አካላት ሆነው የሚታወቁትን ጭምር ነው። አብዛኛዎቹ እነዚህ ሀገራት በስፓኒሽ፣ ፖርቹጊዝ እና ፈረንሳይ ቅኝ ገገርዎቹ የተያዙ ናቸው። የተጠቀሰው አካባቢ ኗሪዎቹ የሚበዙት ምንጩ ላቲን የሆነ ቋንቋን ስለሚጠቀሙ ነው ተጠቃለው ‹‹ ላቲን አሜሪካ ›› የሚባሉት። በላቲን አሜሪካ ከአራት ሰዎች ሶስቱ የከተማ ነዋሪዎች ናቸው። በ2009 የላቲን አሜሪካ ሕዝብ ቁጥር 568 ሚሊየን እንደሚደርስ ተገምቷል።

## አባባል

- ትልቁ ነገር ሕይወትን በመነፅር ውስጥ መመልከቱ ነው። በሌላ አነጋገር ህይወት ተሰነጣጥቆና ተተንትኖ ወደ ሰባቱ ቀለማት ወርዶ ቀለል ባለ መንገድ አዕምሯችን ውስጥ መቀመጥና እያንዳንዱ ንጥረ ነገር በጥንቃቄ ተነጣጥሎ መጠናት ይኖርበታል።
- አዲስና ንፁህ ህይወት ለመጀመር የሚቻለው አንድ ሰው በትክክለኛ መስመር ላይ ነኝ ብሎ በልበ ሙሉነት የራሱን ዕድል ፊት ለፊት በትክክል ለማየት ሲችል ነው። ይህ አዲስ ህይወት ዘግይቶም ሆነ ፈጥኖ መምጣቱ የማይቀር ነው።
- እያንዳንዱ ግላዊ ኑሮና ሕይወት በምስጢር ዙሪያ የሚሽከረከር በመሆኑ ነው ሁሉም ስልጡን ሰዎች ስለ ሰው ምስጢር መጠበቅና መከበር አጠንክረው የሚከራከሩት።
- የአንድ ሰው አይነተኛ መጥፎ ምግባሮቹ ቅናትና ትዕቢት ናቸው። ቅናት የሰው የተፈጥሮ ደካማነት ሲሆን፣ ትዕቢት ደግሞ ከልክ ያለፈ ኃይልና ከሰው በላይ የሆነ ፍጥረት ነኝ ብሎ ያታልላልና ነው።
- ንግግሮች ዋጋ ቢስ የሚሆንባቸውና የሰውም ንግግር በስራ ብቻ የሚገለፅባቸው ብዙ መንገዶች አሉ።

## ለጠቅላላ እውቀት

- የዋልታ ጫፍ ላይ ድቦች በሰዓት 40 ኪሎ ሜትር መሮጥና 1.8 ሜትር መዝለል ይችላሉ። እነዚህ ድቦች በኢንፍራሬድ ካሜራ ፈፅሞ ምስላቸው ሊነሳ አይችልም። ምክንያቱም ደግሞ በቆዳቸው ላይ የሚገኘው ፀጉር አንፀባራቂ በመሆኑ።
- ቢራቢሮዎች የሚያጣጥሙት በእግራቸው ጫፍ ነው። ይህ ስሜት ሕዋሳታቸው ያረፉበት ቅጠል የሚበላ አሊያም የማይበላ እንደሆነ ይገልፅላቸዋል።
- ‹‹ፊኒሽ ታይን›› የተሰኘ የዛፍ ዝርያ ስር በጠቅላላ ተደምሮ 30 ማይልስ (48.278 ኪሎ ሜትር) እንደሚደርሱ ታውቋል።
- በብስክሌት ከፍተኛውን ፍጥነት ያስመዘገበው ሬድ ፎምፐበርግ የተባለው ሰው ሲሆን፣ ፍጥነቱም 166.94 ሜት በሰዓት ነበር።



ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

# ብሔር ባይኖረንስ?

አሁን አሁን በሀገራችን ብሔር የሚለው ቃል ከሞት፣ ከስደት እና ከመፈናቀል ጋር ጥብቅ የሆነ ወዳጅነት እንዳለው በተደጋጋሚ እየተመለከትን ነው። የ"እንትን ብሔር ከእንትን ብሔር" ጋር ተጋጩ። እንትና ብሔር እንትና ብሔርን አፈናቀለ። እንትና ብሔር ከእንትን ብሔር ጋር በድንበር ይገባኛል ግጭት ፈጠረ። ....ወዘተ ለአገራችን ሚድያዎች ዕለታዊ ዜና ሆኗል። አሁን ምን ብዬ ማለም ጀመርኩ መሳላችሁ? ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከእንቅልፉ ሲነቃ ብሔሩን ረስቶ ቢነቃ ተመኘሁ። ከዚያ በኋላ እነዚያ የግጭት ፣የመፈናቀልና የመገዳደል ዜናዎች ይጠፉልን ነበር። ለመሆኑ የሀገራችን ብሔር ብሔረሰቦች የተፈጠሩት ዛሬ ነው እንዴ? አማራ፣ኦሮሞ ፣ትግሬ ፣ከንባታ ፣ሀዲያ፣ ሶማሌ፣ ኮንሶ፣ጉራጌ፣አፋር ፣ቤንሻንጉል፣ሐረሪ ..ወዘተ ዛሬ የተፈጠሩ ናቸው እንዴ? ለክ/ዘመናትና ለዘመናት አብረው ተጋብተውና ተዋልደው አልኖሩም እንዴ? ምነው ዛሬ ብሔር ብሔር እየተባለ ህዝቡ በብሔሩ ምክንያት ስቃዩ የበዛው? ዛሬ ለምን በተለየ ሁኔታ ብሔርን የጥላቻና፣የግጭት ምንጭ አደረግነው? እንደ እኔ እምነት የግጭቱ ምንጭ ብሔሩ ሳይሆን በብሔሩ ውስጥ ያሉ አንዳንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅም የተነካባቸው ጥቂት ግለሰቦች የሚያደርጉት እንጂ፣የትኛውም ብሔር ከሌላው ከሌላው ብሔር ጋር ዛሬም ተዛንቆ እየተጋባ እየተዋለደ እንደ ቀድሞ እየኖረ ያለ ነው።

በቅርቡ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አህመድ ከደሴ ነዋሪዎች ጋር በነበራቸው ውይይት ስለ ብሔር ጉዳይ ተነስቶ የሰጡት ምላሽ አስደስቶኛል። ከአብራካቸው የተፈጠረችውን ልጃቸውን ዲቦራ ዐቢይን ምሳሌ አድርገው ነበር። ዲቦራ ዐቢይ በብሔር ከተቀላቀሉት ሁለቱ ወላጆቿ የተፈጠረች አዲስ ትውልድ ናት። "ታዲያ ዲቦራ ዐቢይን የብሔር ታርጋ ለመለጠፍ ልንሰነጥቃት ነው ወይ? ሲሉ ነበር እውነታውን በግልጽ ያስቀመጡት። ታድያ በዚህ ዘመን እንደ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ ልጆች ፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን ዜጎች የብሔር ታርጋ በላያቸው ለመለጠፍ መሰንጠቅ አለባቸው? መሰንጠቅስ ይቻላል ወይ ነው ጉዳዩ?

በአንድ ወቅት አንድ ወጣት ስራ ለመቀጠር ከፈለገው መ/ቤት ፎርም እየሞላ ሳለ፣ብሔር የሚለው መጠይቅ ላይ ሲደርስ የራሱን ብሔር ለመሙላት ተቸግሮ፣ ለቢሮው አለቃው ብሔር የሚለው ላይ ምን ብዬ ልሙላ ሲል ጠየቀ? ብሔርህን አታውቀውም አለው? ልጁ በፍጥነት ኢትዮጵያዊ ብዬ ነው የምፅፈው? ሲል ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ። የቢሮ አለቃው ደግሞ እሱ ዜግነት ነው አለው፡ ፡ ልጁ ግራ ተጋባ። የልጁን ግራ መጋባት ያስተዋለው የቢሮ አለቃ፣ "የቤተሰቦችህ ብሔር ምንድነው ሲል ጠየቀው?" "እናቴ በእናትዋ ጉራጌ ናት። በአባትዋ ደግሞ ኦሮሞ ናት፡ ፡ አባቴ ደግሞ በአባቱ ሲዳማ ነው እናቱ ደግሞ ትግሬ ናት" አለ። በዚህ ሰአት የቢሮ ሀላፊው ጭምር በሁኔታው ግራ ተጋባ። ድብልቅልቅ ትውልድ ነህ ሲል በልቡ አሰበ፡ ፡ እንዲህ በል ብሎ ለማለት እንኳን ምርጫ ጠፋ። ከአራት የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ተቀላቅሎ የተወለደው አዲስ ትውልድ ምን ብሎ ፎርሙን ይሙላ? መሙላት ደግሞ ግዴታው ነው። ወጣቱ ብሔሩ ጠፍቶበት ወረቀቱን በእጁ ይዞ ማሰብ ጀመረ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ለቢሮ ሀላፊው "ፌደራል ብዬ ልሙላው ወይ?" ሲል ሀሳብ አቀረበ። የቢሮ ሀላፊው የጭንቀትና የሀዘን ሳቅ ሳቀና ፌደራል የሚባል ብሔር በኢትዮጵያ አለ ወይ? ብሎ መልሶ ጠየቀው። በልጁ ሁኔታ የተጨነቀው የቢሮ ሀላፊ "በቃ እሱን ተወዉ እና እለፈው" አለው። ብሔርን በተመለከተ የተዛባ ትርጉም ይዘን ፣እኛ ግራ ገብቶን ልጆቻችንን ግራ አጋባናቸው።

በዚህ ዘመን ከታሪክ ጋር የሚወዛገቡ ኃይሎች መንገድ ብቻ እየጠመዘዙ አንዱን ወገን ወይም ብሔር ብፁዕ፣ ሌላውን ወገን ብሔር እርኩስ አድርገው የሚስሉ የዘመናችን ቴአትረኞች እንደ አሸን ሞልተዋል። በታሪክ ማንኛውም ብሔር በማን ላይ ጭቆና እንዳደረሰ ማስረጃ አቅርቡ ቢባሉ ወገቤን የሚሉበት ተረት ተሸክመው የሚዞሩም ሞልተዋል። አባቶቻችን የሰሩትን አስደናቂ ታሪክ መሥራት የማይችሉ ታሪክ ለማበላሸት ግን እንቅልፍ የሚያጡ የተማሩ ማህይማን በየቦታው አሉን። እንዲህ ዓይነቱ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ውስጥ የተዘፈቁ ኃይሎች፣ በተለያዩ መንገዶች በብሄር ስም የአገር ሰላም እያደፈረሱ ነው። በብሄር አሳበው በሕዝብ መሀል መቃቃር እንዲፈጠርና ግጭት እንዲቀሰቀስ ተግተው እየሠሩ ነው። ይህ ድርጊት መቆም አለበት። የእልህና የብሽሽቅ ፖለቲካ ውጤቱ ታሪክ እያዛቡ አገር ማመስ በመሆኑ መንግስት ሃይ ማለት አለበት። ግጭት የሌላቸውን ፣ተዋልደው ተጋብተው የሚኖሩትን ጨዋ ህዝቦች በብሄር ግጭት እንዲገቡ ፣የሌለ የፈጠራ ታሪክ እየፃፉ አገርን ለማጥፋት መሯሯጥ ለማንም አይጠቅምም እንላለን።

> ...የቤተሰቦችህ ብሔር ምንድነው ሲል ጠየቀው?" "እናቴ በእናትዋ ጉራጌ ናት። በአባትዋ ደግሞ ኦሮሞ ናት። አባቴ ደግሞ በአባቱ ሲዳማ ነው እናቱ ደግሞ ትግሬ ናት" አለ፡ ፡ በዚህ ሰአት የቢሮ ሀላፊው ጭምር በሁኔታው ግራ ተጋባ። ድብልቅልቅ ትውልድ ነህ ሲል በልቡ አሰበ....

የአገሪቱንና የሕዝቡን ታሪክ ብሔርን ያለ ቦታው እየሰነቀሩ እና እያጣመሙ ለግጭት ምንጭ እንዲሆን አደረጉት። አንዱ ይነሳና የሌላውን ሕልውና በመካድ አገር አልባ ሊያደርገው ይፈልጋል። ሌላው ደግሞ በትውልድ ቅብብሎሽ ሕዝብ አንድ ላይ ሆኖ ብሔርን ሳይለይ አገሩን በጋራ ሲጠብቅ እንደነበረ ሊክድ ይዳዳዋል። የፖለቲካ ሥልጣን በተሳሳተ መንገድ ለመጨበጥ ብቻ፣ የጋራ አገር እንደሌለች ዓይናቸውን በጨው አጥበው ሐሰተኛ መረጃ የሚነግሩን "የተማሩ ማህይማን" ሞልተዋል። ታሪክን በሚፈልጉት ዛሬ አንዱ ብሄር ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር አብሮ እንዳይኖር በክፉ ድርጊት እንድንፈፅም የሚቀሰቅሱንን የብሔር ጠበቃ ተብዬዎች ሂዱ ወደዛ ዘረኞች ናችሁ በሉዋቸው፣ የኛ ብሔር ብቻ እዚህ ይኑር ሌላው ከዚህ ይውጣ ብሎ የሚነግረንን የብሔር ጠበቃ ተብዬን "ብሔርህ ገደል ይግባ" በሉት። "ከብሔር በላይ ኢትዮጵያዊነቴ ይቀድምብኛል" በሉት። "ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል ነው። አብሬ ተከባብሬ እንደ ቀድሞዬ እኖራለሁ" በሉት። ሙሰኛ አጭበርባሪ ሲታሰር በብሔር ጉያ ተሸጉጠው ጎጠኛና ዘረኛ አስተሳሰባቸውን ለማስረፅ የኛ ▶

**የአዲስ አበባ አስተዳደር ብሔር የሌለውን መታወቂያ እሰጣለሁ ሲል ብዙ ህዝብ ደስታውን ገልፆ ነበር። በርካታ ህዝብ ብሔር የሌለውን መታወቂያ ለመውሰድ ወደ ቀበሌ ነጉዶ ነበር። እነዚህ ብሔር አልቦ መታወቂያ የፈለጉት ዜጎች ከሁለት ከሶስት እንዲሁም ከአራት ብሄሮች የተፈጠሩና ብሄራቸውን መሰንጠቅ ያልቻሉ ነበሩ። በእንዲህ አይነት መልክ የተጋቡና የተዋለዱት ደግሞ ከብሄራቸው ይልቅ ስለ ኢትዮጵያዊነታቸው በጣም ይጨነቃሉ።**

▶ ብሔር ስለሆነ ታሰረ ቢሉዋችሁ፤ "ሌባ ከሆነ ይበለው" በሉት። "ህግ ይዳኘው" በሉት። እንዲህ አይነት የብሔር ጠበቃ ተብዬዎች በሁሉም ብሔሮች ውስጥ ሞልተዋል። ጥፋት ሳይኖረው በብሔሩ ብቻ ተመካኝቶ የታሰረ ዜጋና ያሰረ መንግስት ካለ ነገ ሁሉም የእጁን እንደሚያገኝ ከማንም የተሰወረ አይደለም። ምክንያቱም እውነት በጊዜ ብዛት ትቀጥነለች እንጂ ተበጥሳ አታውቅም።

ሚዛናዊነት አጥተን፣ በክፉ ዘረኝነት ተጠልፈን፣ ሌላውን ወገን ያለ ጥፋቱ የምንበድል ከሆነ ከኛ ጋር አብሮ ባልተፈጠረ፣ ስንኖር ባበጀነው ብሔር ሌላውን "መጤ ነው" ብለን ሰይፍ አንስተን ፤መሳሪያ ደቅነን፤ ቆንጨራ ስለን፤ ቀስት ወርውረን፤በእግር ብረት አስረን ጉዳት የምናደርስ ከሆነ፤ አብሮ የመኖር ትርጉም ያልግባን፣ ከእንስሳ ያልተሻልን መሆናችን አይደል? ለአገር ሰላምና ደህንነት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም አብሬ የማልቆም፤ይበልጥኑ በብሔር ምክንያት የአገር ሰላምና ደህንነት ስጋት ከሆንኩኝ የተማርኩ ማሀይም ነኝ ማለት ነው። ቀድሞ አባቶቻችን ሳይማሩ የተከበረች አገር ሲያቆዩልን ፤የተማርን መሀይሞች ደግሞ የፈረሰ አገር ለትውልድ ለማስረከብ ደፋ ቀና እንላለን።

የአንድ አገርን ሕዝብ በብሔር ወይም በተለያዩ ማንነቶች በመከፋፈል በስሙ መነገድ የዘመናችን ልሂቃን መለያ ከሆነ ዓመታት ነጉደዋል። እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ከልዩነቶቹ ይልቅ የጋራ እሴቶቹና መስተጋብሮቹ የሚያመዝኑት ይህ ሕዝብ፣ በተለያዩ መልክዓ ምድሮችና የአየር ፀባዮች ውስጥ ቢኖርም ዕጣ ፈንታው ግን አንድ ነው። ለዘመናት የተለያዩ ገዥዎች ቢፈራረቁበትም፣ የተለያዩ ባዕዳን ወራሪዎች ቢዘምቱበትም፣ ለማመን በሚያዳግት ሰቆቃ ድህነትና ኋላቀርነት መከራውን ቢያይም፣ የግፍና የበደል ዓይነቶች ቢፈራረቁበትም በእናት አገሩ ጉዳይ በብሔር ተለያይቶ ሲደራደር አይታወቅም። ይህ ከብሔሩ በላይ ለኢትዮጵያዊነት ያለው የማይበርድ ፍቅርና የጋለ ስሜት ከዘመን ወደ ዘመን፣ እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ እዚህ ደረጃ ደርሷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በብሔር ሳይለያይ እርስ በርሱ ሲተዛዘን፣ ሲደጋገፍና ያገኘውን እየተጎራረሰ መኖሩ መቼም ቢሆን አይታበልም።

ከበፊት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሕዝብን በብሔር ለማቃቃር፣ ለማጋጨትና ደም ለማፋሰስ የሚጥሩት ግን የአገር ህልውናን ከራሳቸው ርካሽ ጥቅም በታች የሚያዩ ከንቱዎችን ታሪክ በጥቁር መዝገብ መዝግቧቸዋል። አስተዋዩና ጨዋው የኢትዮጵያ ሕዝብ መታገል ያለበት እነዚህን በአፍቅሮተ ንዋይና በጭካኔ የሰከሩ እኩዮችን ነው።

በዚህ ዘመን ልዩነቶችን በሠለጠነ መንገድ በማስተናገድ ለሰላማዊና ለዴሞክራሲያዊ ፉክክር መዘጋጀት ሲቻል፣ በዘመናት ችግሮች ላይ ተጨማሪ ችግሮች እየደራረቡ አገርንና ሕዝብን በብሄር ማተራመስ የኋላቀርነት እና የድንቁርና አካሄድ ነው። ከዚህ በፊት ተሞክረው ተግባራዊ መሆን ያልቻሉ ስህተቶችን ለመድገም መሞከር ትርፉ ውድቀት ነው። በተለይ በነጋ በጠባ ከመንግሥት ጋር ንትርክ ውስጥ ያሉ የሀገራችን የብሔር ፖለቲከኞች ካለፈው ስህተታቸው መማር አለባቸው። ገና ለገና ሕዝብ ይደግፈናል በሚል አጉል ሥሌት ያልተገባ ድርጊት ውስጥ የሚገኙ የብሔር ፖለቲከኞች፣ ራሳቸውንም ድርጅታቸውንም መሳቂያ ባያደርጉ ይሻላቸዋል። ሕዝብ ውስጥ መሸሎ በብሔር አመካኝቶ ጦርነት መክፈት፣ ግጭትን የዓላማ ማስፈጸሚያ ማድረግና ከሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በማፈንገጥ ስህተት ውስጥ መነከር የጊዜ ጉዳይ ይሆናል እንጂ ለኪሳራ ይዳርጋል። ሰላማዊ የፖለቲካ ትግልን ወይም ፉክክርን ከጠመንጃ ጋር ለማቆራኘት መሞከር የማይወጡት አዘቅት ውስጥ ይከታል። ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የማይመጥን ጠመንጃ ነካሽነት በሕዝብ ያስንቃል። ያዋርዳልም።

በዚህ ዘመን ብሔርተኝነትን ሙጭጭ ብለው የያዙ ወገኖች አገርን የምታህል የጋራ ቤት ዘንግተው ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ተጥደዋል። ከእነሱ አመለካከት ውጪ ምንም ነገር ማዳመጥ ስለማይሹ፣ ተቃራኒ የሚሉትን በሙሉ በጠላትነት ይፈርጃሉ። የእነሱ ድርጊት በዚህ አያበቃም። ብሔርን በጎሳና በጎጥ እንዲሁም በመንደር እየከፋፈሉ ስለሚሻኮቱ እርስ በርስም አይግባቡም። ከዘመነ መሣፍንት ጋር ተቀራራቢ በሆነ አስተሳሰብ ላይ ተጥደው፣ ሐሳብን በሐሳብ ከመሞገት ይልቅ ልዩነትን በነፍጥ ለመፍታት ይጋበዛሉ። በሌላ በኩል ከዴሞክራሲያዊ መሠረታዊ ሕጎች በማፈንገጥ፣ ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ደንታ የላቸውም። ከዕውቀት ነፃ ስለሆኑ የሚቀናቸው ዘለፋና ስድብ ሲሆን፣ ለውይይትና ለድርድር በራቸው ዝግ ነው። በሕዝብ ስም ቢምሉም ዋናው ትኩረታቸው ዝና፣ ሥልጣንና ጥቅም ላይ ነው። በሕዝብ ስም እየነገዱ ዓላማቸውን ካሳኩ በኋላ የሚንደረደሩት አምባገነን ለመሆን ነው።

በአንድ ወቅት የአዲስ አበባ አስተዳደር ብሔር የሌለውን መታወቂያ እሰጣለሁ ሲል ብዙ ህዝብ ደስታውን ገልፆ ነበር። በርካታ ህዝብ ብሔር የሌለውን መታወቂያ ለመውሰድ ወደ ቀበሌ ነጉዶ ነበር። እነዚህ ብሔር አልቦ መታወቂያ የፈለጉት ዜጎች ከሁለት ከሶስት እንዲሁም ከአራት ብሄሮች የተፈጠሩና ብሄራቸውን መሰንጠቅ ያልቻሉ ነበሩ። በእንዲህ አይነት መልክ የተጋቡና የተዋለዱት ደግሞ ከብሄራቸው ይልቅ ስለ ኢትዮጵያዊነታቸው በጣም ይጨነቃሉ። ታዲያ አንድ ወዳጄ በመታወቂያው ላይ በግድ የተጫነበትን ብሔር ለማስነሳት ወደ ቀበሌ ሲሄድ ፤የቀበሌው ወሳኝ ኩነት ብሔር የሌለው መታወቂያ ገና ነው አልተጀመረም ብሎ መለሰው። ወዳጄ አዝኖ ተመለሰ።

በዚህ አጋጣሚ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ብሔር የሌለውን መታወቂያ ለመስጠት የተዘጋጀው እኛ በህይወት እያለን ነው ወይስ በመቃብራችን ላይ ነው ብሔር አልቦ መታወቂያችንን የሚያድለን? ስንኖር ኢትዮጵያ ፤ስንሞት ኢትዮጵያዊ መሆን የሚቻለው እኮ ማንነታችን ኢትዮጵያዊ ሲሆን ነው። ካልሆነ ስንኖር ብሄር ስንሞት ኢትዮጵያዊ ሊያደርገን ስለሚችል፤አሁን ባለው የአገራችን ሁኔታ ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ሰርቶ መኖርና እንደፈለገ መንቀሳቀስ የሚችለው ብሔር የሚለውን መለያ ከመታወቂያችን ላይ ማንሳት ሲቻል ብቻ ነው። ለዚህች 100 ለማትሞላ ትንሽ እድሜ ብሔር ባይኖረን ምን እንሆናለን?

***ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር***



በኢህአፓ ውስጥ ከአገራዊ ንቅናቄና የጦር ትግል እስከ ባህርማዶ አደረጃጀት ድረስ ጉልህ ድርሻ የነበራቸው ፕሮፌሰር ጌታቸው በጋሻው፤ ከመሰል አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጓደኞቻቸው ጋር በጥምረት "ቪዥን ኢትዮጵያ" የተሰኘ ድርጅት በምድረ አሜሪካ በማቋቋም፤ በአገሪቱ ጉዳዮች ዙሪያ ታላላቅ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

በደርግም ሆነ በወያኔ ስርዓት ሳለፉት አርባ አራት ዓመታት ከአገር ርቀው የቆዩት ፕ/ር ጌታቸው በጋሻው፣ ለውጡን ተከትሎ በቀረበላቸው ግብዣ መሰረት ወደ አገር ቤት መጥተዋል፡፡ በቅርቡም "ቪዥን ኢትዮጵያ" በተሰኘው ድርጅታቸው አማካይነት በባህርዳር ዩንቨርስቲ ያዘጋጁት ታላቅ ኮንፈረስ በስኬታማነት ተጠናቋል፡፡ በቁጥር 61 ዕትማችን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩች ዙሪያ የሰጡንን ማብራሪያ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ በዛሬውና በመጨረሻው ክፍል ቆይታችን በውጪው ዓለም ስለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ምሁራን፣ ስለቪዢን ኢትዮጵያ አመሰራረትና ቀጣይ እቅዶች የሰጡንን ምላሽ ይዘን ቀርበናል፡ ፕሮፌሰርን የግዮን ጋዜጠኞች ሮቤል ምትኩና ፍቃዱ ማ/ወርቅ ባረፉበት ሂልተን ሆቴል አግኝተው ፣ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግረዋቸዋል፡፡

መልካም ቆይታ፡፡

# "አገሪቱን የሚጠላ መንግስት ገዢ ሲሆን ውጤቱ አስከፊ ነው"

## ፕ/ር ጌታቸው በጋሻው

**ግዮን፡ ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በርካታ ታላላቅ አገራዊ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኘው ቪዥን ኢትዮጵያ መቼና እንዴት ተመሰረተ?**

**ፕ/ር ጌታቸው፡** ለሁለተኛ ጊዜ ኢህአፓ ውስጥ ገብቼ ስወጣና ከነመርሻ ዮሴፍ ጋር ስለያይ፣ በዩንቨርስቲ ደረጃ የማስተምር ፕሮፌሰር እንደመሆኔ መጠን በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚዘጋጁ የምሁራን ስብሰባ ላይ እየሄድኩ እሰበሰባለሁ፡፡ ውሎዬ እና ትውውቄም እንዲሁ ከስራዬ ጠባይ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በዚህ ዓይነት ስብሰባዎች ላይ እጋበዛለሁ፤ አገራዊ ሁኔታው ይጠይቃል በምልበት ጊዜም እኔ ራሴ የተለያዩ ስብሰባዎችን አዘጋጃለሁ፡፡

ይሄ ደስ ባለን ጊዜ፣ በአጋጣሚ ወይም በዘፈቀደ የሚደረግ ነው እንጂ በተያያዘና ቀጣይነት ባለው፣ መሰረቱን በጣለ ደረጃ የሚጓዝ አልነበረም፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ምሁራን ለአገራቸው ብዙ አስተዋፅኦ እያደረጉ አይደለም፡፡ በነገራችን ላይ ብዙዎቹ አገራችንን አንፈልግም ብለው እዘው የቀሩ አይደሉም፡፡ እኔ ራሴ ጓደኞቼ በሙሉ ሲያልቁ፣ ሲገደሉ "ቆሜ አላይም" ብዬ ነው ሳልፈልግ ለስደት የተዳረግሁት፡፡ ብዙዎች እንደዚህ አይነት ሰዎች ናቸው፤ እንቀራረባለን፡ ፡ በአገራችን ጉዳይ ሀሳብ ለማፍለቅና ለመስራት ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖረንም በተቀናጀ መንገድ የሚያስኬደን ምንም ድርጅት ግን አልነበረንም፡ ፡

ከዛ በመነሳት እ.ኤ.አ 2014 ላይ አንድን ትልቅ ነገር ለመጀመር አንድ ሰው የግድ ኃላፊነቱን መውሰድ አለበትና፣ በዛ መልክ ነፃ አስተሳሰብ አላቸው ያልኳቸውን ሰዎች ጠራኋቸው፡፡ ቴሌ ኮንፍረንሶች እያደረግሁ፣ የቪዥን ኢትዮጵያ መስራቾችን መመልመል ጀመርኩ፡፡ ዋናው ነገር የኢትዮጵያ ምሁራንን እየሰበሰቡ፣ እነኚህን ተመራማሪዎችና የሀሳብ መሪዎችን አገናኝቶ በአገራቸው ጉዳይ ላይ በተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ ኮንፈረንሶችን እንዲያደርጉ ማመቻቸት ነው፡፡ በዛ መልክ መጀመሪያ ተገናኝተን በሀሳቡ ላይ ከተወያየን በኋላ ራዕያችን፣ ተልዕኮችን ምንድን ነው? ግባችን ምንድን ነው? የሚሉትን በጽሁፍ መለዋወጥ ጀመርን፡፡ ከስምምነት ስንደርስ ድርጅታችን ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት እንዳይወግን፣ ለማንኛውም መንግስት ተገዢ እንዳይሆን፣ ነፃ ተቋም ሆኖ እንዲሰራ ስያሜያችንንም ቪዥን ኢትዮጵያ ልንለው ችለናል፡፡

**ግዮን፡- ራዕይ ለኢትዮጵያ (vision Ethiopia) መስራቾች እነማን ነበራችሁ?**

**ፕ/ር ጌታቸው፡-** ፕሮፌሰር ሰዒድ ሀሰን፣ ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ፣ ፕሮፌሰር አሸናፊ ጎሳዬ፣ ፕሮፌሰር አቡ (ጃፓን የሚኖር)፣ አቶ ግዛው ለገሰ (የኢሳት ባልደረባ)፣ አቶ ግርማ በቀለ (ሳንፍራንሲስኮ) እንዲሁም እኔ ሆነን ነው ቪዥን ኢትዮጵያን የመሰረትነው፡፡ እስካሁን ድረስ የሚደረጉት ጉባኤዎች በሙሉ በስብሰባ አዳራሽ ግድግዳ ውስጥ ነው ታፍነው የሚቀሩት፤ ከእንግዲህ የምናደርገው እንደዛ ►

ሳይሆን ስብሰባው በሙሉ ተቀርፆ ወደ ሕዝብ እንዲሰራጭ ምን እናድርግ? ለሚለው ከኢሳት ጋር ተባብረን እንስራ ከሚለው መደምደሚያ ላይ ደረስን። ቀደም ሲል ከእነሱ ጋር መልካም ግንኙነት ስለነበረን ውይይቶቻችን በእነሱ አማካይነት ለሕዝብ ማድረስ ጀመርን።

በቅድሚያ መስራት ያለብን አገሪቱ ላይ በብዙ መልክ ችግር የሚፈጥረው ከኤርትራ ጋር ያለው ግንኙነት ነው፤ እሱን መመልከት አለብን ከሚል ነጥብ ላይ ደረስን። እኔ አንደኛ በአሰብ ጥያቄ ላይ አክርሬ ብዙ ነገሮችን እፅፍ ነበር። አሰብ የኢትዮጵያ ናት። በታሪክም፣ በሕግም አሰብ የኢትዮጵያ ናት ብዬ አምናለሁ። አንድን ትልቅ ሕዝብና አገር አፍኖ ማስቀመጥን የዓለም ሕግም ይቃወመዋል። በዩናይትድ ኔሽን ስምምነት፣ እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ትላልቅ አገር ቀርቶ ትናንሽ አገሮችም ወደ ባህር የሚመጡበት መካኒዝም ወይም ስምምነቶች መፈጠር እንዳለባቸው በግልጽ አስቀምጧል።

አሁን ያለውን ነገር ለተመለከተ ቀጥ ብሎ ባህርን ይዞ ኢትዮጵያን የማፈን ካርታ ነው የተሰራው በኮለኒያልስቶች። እስከ ቀይ ባህር የሚሄደውን የኢትዮጵያ ክፍል የሚይዘው አፋር ነው፣ አፋር ደግሞ ኢትዮጵያዊ ነው። በርግጥ ኤርትራ ውስጥ፣ ጅቡቲም ውስጥ አለ። በምን ተዓምር ነው ይሄ የኢትዮጵያ አፋር በአሰብ በኩል የኤርትራ እንዲሆን የተደረገው? ከታች ጅቡቲ ራሷን የቻለች አገር አለች ኤርትራ ደግሞ ከላይ ወጥራ እንድትይዝ ነው የተደረገው። የተለየ ሕዝብ ቢሆን ችግር የለውም፤ ግን ሀቁ ቀይ ባህር የተያዘው በአፋር ነው፤ የአፋር ግዛት ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ይሄ በመጥፎ ዓላማ የተነሳ ኢትዮጵያን የማፈንና የመግደል ነገር ነው፤ አንድ አገር የባህር በር ከሌላት እንዴት በኢኮኖሚ ልትወድቅ እንደምትችል በተደጋጋሚ ከማስረጃዎች ጋር በተያያዘ እጽፍ ነበር።

**ግዮን፡- ከኤርትራና ከአሰብ ወደብ ጋር በተያያዘ በሚፅፏቸው ጽሁፎችና በሚሰጧቸው አስተያየቶች ከኤርትራውያን የተጋጩበት አጋጣሚ እንደተፈጠረም ሰምተናል።**

**ፐ/ር ጌታቸው፡-** እንዲህ ዓይነቱ ነገር ይኖራል። አንድ ወቅት የኤርትራ ፕሮፌሰር፣ ድሮ በጃንሆይ ጊዜ ጀነራል የነበሩ የሐረር ጦር አካዳሚ ግራጁየት ከሆኑት ፐ/ር ግደይ ጋር ተገናኘን። በዚህ ጉዳይ ባለመግባባታችን ቨርጂኒያ ውስጥ በቦክስ ልንደባደብ ስንል ሰዎች ናቸው የገላገሉን።

እኔ በወቅቱ በኤርትራ ጉዳይ ያለኝን አቋም በግልፅ ተናገርኩ፣ እሳቸው ያኔ ተነስተው ተሳደቡ። ለስድባቸው ምላሽ ስሰጥ ካልተደባደብኩ ብለው ያዙኝ፣ ልቀቁኝ አሉ። በርግጥ እሳቸው የድርጅት ሰው ናቸው፣ ብዓይ ኢሳይያስ አፈወርቂ ስለሚከታተሏቸው ስራቸውን በተግባር ማሳየት ያለባቸው መሰለኝ። እኔ ደግሞ የምታየኝ ኢትዮጵያ ናት፤ የኢትዮጵያ ኢንተረስት ደግሞ ሌላ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ልዩነትን የሚያመጣው የኢትዮ - ኤርትራ ችግር ካልተፈታ ሁለቱም አገሮች ተጎጂ ናቸው።

ኤርትራውያኖች 300 ሺኅ ጦር በድንበር ላይ አስቀምጠው፣ ኢኮኖሚያቸው እየወደቀ፣ ሕዝብ እየተራበ፣ ያ ጦር ጉድጓድ ውስጥ ቁጭ ብሎ ምንም አያመርት፣ ምንም አይሰራ ችግሩ ብዙ ነው የሚሆነው። ዕድገታቸውን ወደ ኋላ ይጎትተዋል። ኢትዮጵያንም እንደዚሁ። ኢትዮጵያ ባህር በሯን ልትይዝ ስትችል ይሄን ለማድረግ የማይፈልግ መንግስት ስለነበረን አሳልፎ ሰጠ። አገሪቱን የሚጠላ መንግስት መሪ ሲሆን ወይም አገሪቱን ሲገዛ ውጤቱ መጥፎ ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያ እየተበደለች ልትቀጥል አትችልም። ስለዚህ የሁለቱ አገራት ግንኙነት በምን መልክ ነው መቀጠል ያለበት? በሚለው ሀሳብ ነበር የመጀመሪያውን የቪዥን ኢትዮጵያ ጉባኤ ያዘጋጀነው።

**ግዮን፡- ውጤቱ ምን ሆነ?**

**ፐ/ር ጌታቸው፡-** እዛ ጉባኤ ላይ የመንግስት ስልጣንን ቀጥታ ከደርግ ወደ ወያኔ ያዘዋወሩት አምባሳደር ኸርማን ኮህን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የአሜሪካ አምባሳደር በመሆን የሰሩት ዴቪድ ቪንን ከአሜሪካ፣ ከኢትዮጵያ መንግስት በኩል ለኮ/ል መንግስቱ ቅርብ የነበሩት አምባሳደር (ዶ/ር) ካሳ ከበደን፣ በኢትዮጵያ የጆኦግራፊ ምሁርና ብዙ የፖለቲካ ተሳትፎ ያላቸው ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያምንና ሌሎች በርከት ያሉ ምሁራኖችን ጠርተን የመጀመሪያው የቪዥን ኢትዮጵያ ኮንፍረንስ ለሁለት ቀን ተካሄደ። ያኔ ነው ነገሩ ለኛ ግልፅ የሆነው። የኢትዮጵያና የኤርትራ ችግር እንዲፈታ የአሜሪካን መንግስት ፍላጎት እንዳለው፣ ያ ነገር በብዙ መልኩ እንደሚገፋም ከኸርማን ኮህንና ዴቪድ ቪን በቀረቡት ሪፖርቶች መረዳት ቻልን።

ኢትዮጵያ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ችግር ውስጥ ነው ያለችው። ከአገራችንም፣ ከዓለምም እንደተማርነው፣ እነኚህ ችግሮች በየጊዜው ሲኖሩ እንደዛው እንዲሆኑ ለዘላለም አይቀመጡም፣ ይፈነዳሉ። መፈንዳት ስንል? ሕዝብ በመንግስት ላይ ይነሳል፤ ሕይወቱን በመገበር ስርዓቱን ይጥላል። መንግስት እንዲህ በሚወድቅበት ጊዜ ምንድን ነው የሚሆነው? ስንል ደግሞ ሽግግር የሚባል ጊዜ አለ። ከእንግዲህ በኋላ በተከታታይ የሚደረጉ ስብሰባዎቻችን በሙሉ "ሽግግር"ን ትኩረት ያደረጉ መሆን አለባቸው ከሚል አቋም ደረስን።

**...ጡረታ ብወጣ ወይም በእረፍታችን የምንሰጠውን የመልካም ስራ አገልግሎት ጊዜ ብወጣ፣ ኢትዮጵያ መጥቼ አስተምራለሁ። የማስተምርበትን ት/ቤቴን ወክዬ ከፐ/ር ሒሩት ወ/ማርያም ጋር ተነጋግረናል...**

**ግዮን፡- እናንተ የመረጣችሁት "ሽግግር" መንግስት የመመስረትን ሂደት ያካተተ ነው? ይሄንን ግልፅ ቢያደርጉልን?**

**ፐ/ር ጌታቸው፡-** ሽግግር ስንል ብዙ ቅርንጫፎች አሉት። ሽግግር አንድ አገር ውስጥ እንዲመጣ ምን ምን ዓይነት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው? ይሄ ራሱን የቻለ አንድ ኮንፍረንስ በመሆኑ ሁለተኛው ኮንፈረንሳችን በዛ ላይ ነው ያደረግነው። ሶስተኛው ይሄ ሽግግር እንዲፀና ወይም ጥሩ ውጤት እንዲያመጣ ማን ምን ማድረግ አለበት? የፖለቲካ ድርጅቶች ኃላፊነት ምንድን ነው? የብዙኃን ድርጅቶች ኃላፊነት ምንድን ነው? የሀይማኖት ተቋሞች ሚና ምንድን ነው? ምሁራኖች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? በኢትዮጵያ ኢንተረስት ያላቸው የውጭ መንግስቶችስ ምን ማድረግ ይችላሉ? ይሄ ሽግግሩን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችለው ሌላኛውና ሶስተኛው ጉባኤያችን ሆነ።

በሽግግር ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ምንድን ናቸው? ይሄ ደግሞ አራተኛው ጉባኤያችን ሆነ። ኢትዮጵያ አሁን በዘር የተከፋፈለች፣ ጥሩ ያልሆነ ሕገ መንግስት ያላት፣ መጥፎ የሆነ በቋንቋና በማንነት ላይ የተመሰረተ ፌደሬሽን ያላት በመሆኑ፤ እሱ እንቅፋት ስለሚፈጥር ከዚህ ሁኔታ እንዴት ተደርጎ ለመውጣት ይቻላል? በሚል አምስተኛው የሁለት ቀን ኮንፈረስ ተካሄደ። በዚህ የሽግግር ሂደት ላይ እያለን፣ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን መጡ። ዶ/ር ዐቢይ ሲመጡ እሳቸውን መቀበል ስድስተኛው የቪዥን ኢትዮጵያ ኮንፈረንስ አደረግነው።

ጠ/ሚኒስትሩን ተቀበልን። ብዙ ምሁራኖች፣ ብዙ የኮሚኒቲ መሪዎችንና የኢኮኖሚ ተቋም ባለንብረቶችን ሰብስበን፤ በአሜሪካን አገር ከእሳቸው ጋር እንዲገናኙ፣ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በመተባበር የእራት ግብዣ አድርገን በዛ ላይ ከጠ/ሚ/ሩ ጋር ተወያየን። ይሄ ደግሞ ራሱን የቻለ አዲስ ምዕራፍ ነው።

**ግዮን፡- ቪዥን ኢትዮጵያ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ፖለቲከኞችን በመሰብሰብ ብዙ ጊዜ አንድ ለማድረግ ከፍተኛ ትግል አድርጋችኋል። በዛ እንቅስቃሴ ውጤታማ ነበርን ማለት ትችላላችሁ?**

**ፐ/ር ጌታቸው፡-** ውጤቱን ለመለካት ያስቸግረኛል። አሁን ለምሳሌ የእነ ሌንጮ ለታ ኦ.ዴ.ግ በጣም ብዙ ጊዜ ጉባኤዎችን ተሳትፏል። ሌንጮ ባቲ፣ በያና ሰቆጻ፣ ዲማ ነገዎን የመሳሰሉ የድርጅቱ ሰዎች በምናዘጋጃቸው አገራዊ ጉባኤዎች ላይ በተደጋጋሚ ተሳትፈዋል።

በቅርብ ጊዜ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና የለውጡ ቡድን አባል ከሆኑት አቶ ጉዱ አንዳርጋቸው ጋር ስንገናኝ ሰርፕራይዝ ያደረገኝ ነገር እያንዳንዱ ጉባኤያችንና እንቅስቃሴያችንን እዚህ አገር ሆነው ይከታተሉን ነበር። በጉባኤዎቹ ላይ እነማን ምን እንደተናገሩ ሲነግሩኝ በጣም ነው የገረመኝ። እውነትም እኚህ ሰው ጥሩ መሪ ናቸው ብዬ እንዳምን አድርጎኛል። በባህር ማዶ የሚደረግ አገራዊ ጉባኤን እንዲህ በጥልቀት መከታተላቸው ያላቸውን ቀናዒነት ያሳያል።

ለምሳሌ የኤርትራ ጉዳይ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ገና ስልጣን እንደያዙ ወደ እዛው በመሄድ እርቁን

**...እኔ የፈለግሁትን ተምሬያለሁ። አሁን በማልፈለግበት፣ የእኔ አስተዋፅኦ ምንም ዋጋ በሌለው አገር ነው እየሰራሁ ያለሁት። በእዛ አገር ጌታቸው ባያስተምርም አሜሪካ ምንም አትሆንም። ጌታቸው ስላስተማረም ያን ያህል ምንም የለወጠላት ነገር የለም። ግን ተወዳድሬ ስራ የመያዝ መብት ስላለኝ፣ ለዛ ነው የተሰጠኝ እንጂ ይሄ ሰውዬ ያስፈልገናል ብለው አይደለም...**

እውን አደርገው አሁን ፍቅር ላይ ነን። ይሄ ውጤት የእኛ ነው ለማለት ሳይሆን የሆነው ይሁን ብቻ በጉዳዩ ላይ አንድ የተለወጠ ነገር አለ። በርግጥ እኛ እሳቸው ይሄን ከማድረጋቸው ሁለትና ሶስት ዓመት በፊት አንስተን ነው በጉዳዩ ላይ የመከነርነው። ከኤርትራውያኖች ጋር በጣም መቀራረብ የጀመርንበት ጊዜ ነበር፤ በመንግስት ደረጃ ባይሆንም።

የመናገር፣ የመፃፍ የመሰብሰብ ጉዳይ ይሄ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ የሚሏቻን ነገሮች በሙሉ እኛ እንግዲህ ስንለምናቸው የቆዩና መሆን አለባቸው፣ ችግሮቿን ፈትታ ኢትዮጵያን ወደ ፊት ያስኬዷታል የምንላቸው ጉዳዮች ናቸው። አሁን የሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች እኛ አስቀድመን ያላነሳናቸውና ያልተነጋገርንባቸው፣ መፍትሄም ለመፈለግ ያልጣርንባቸው ጉዳዮች የሉም። የእኛ ስብሰባ ከአንደኛው እስከ ስምንተኛው ድረስ ሪከርድ ሆኖ ዌብሳይት ላይ አለ። የፈለገ ሰው ወደ ኋላ ሄዶ ሊሰማው ይችላል።

የኢትዮጵያ ምሁራኖች ከመደበቅ ወጥተው በድፍረት መናገር፣ ሀሳባቸውን ሼር ማድረግ፣ መለገስ የጀመሩት በቪዥን ኢትዮጵያ አማካይነት ነው። ዛሬ ብዙ ምሁራኖችን እናያለን፤ ይሄ ትልቅ ውጤት ነው።

**ግዮን፡- የቪዥን ኢትዮጵያ ራዕይ ምን ድረስ ነው?**

**ፕ/ር ጌታቸው** አናቆምም፤ እንቀጥላለን። ራዕያችን ለሁልጊዜ የሚኖርና ዘላቂ ነው። አሁን ለምሳሌ ሽግግር የሚለውን አቁመናል፤ እስከ ሰባተኛው ጉባኤያችን ድረስ ሽግግር ነበር። በስድስተኛው ላይ ጠ/ሚ/ር ዐቢይን “እኛ ኢትዮጵያውያን ነን፣ የምንናገረው ነገር ስለ ኢትዮጵያ ነው። ጉባኤያችንን ሁልጊዜ በአሜሪካ ውስጥ የምናደርግበት ምንም ምክንያት የለም፤ ስለተባረርንና ኢትዮጵያዊነታችንን ስለተነፈግን እስካሁን በሰው አገር አካሂደናል። አሁን እርስዎ ፍቅርና ይቅርታ ብለዋል፤ ሰባተኛውን ኮንፍረስን በአዲስ አበባ ነው የምናደርገው። የእርስዎ መንግስት ለዚህ ትብብር ያድርግልን” ብዬ ጠየቅኋቸው። እሳቸውም መልካም ፍቃደኝነታቸውን ገልፀውልኝ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ እንደሚያደርጉ ቃላቸውን ሰጡን።

በዛ መሠረት ከወራት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ምሁራንን በቪዥን ኢትዮጵያ ቦርድ አማካይነት መዝግበን አርባ አንድ ሆነን ወደ አገር ቤት መጥተናል። በርግጥ በእኛ ጉባኤ ላይ የሚሳተፉ ሌሎች ሰዎች ደግሞ በሌላ መንገድ ተጋብዘዋል። ለእኛ ነግረው፣ በእኛ ዌብሳይት ላይ ተመዝግበው ከአሜሪካ የመጡት ግን አርባ አንድ ምሁራኖች ናቸው። በሌላ መንገድ የመጡትን ጨምሮ ጉባኤው ላይ የተሳተፍነው መቶ አስራ አራት ሰዎች ነን።

**ግዮን፡- እናንተ ባዘጋጃችሁት አገራዊ ጉባኤ ላይ ከእውቅናችሁና ፍቃዳችሁ ውጪ በሌላ መንገድ ሰዎችን መጋበዙ ተገቢ ነው? ማን ነበር እነዚህን አካላት የጋበዘው?**

**ፕ/ር ጌታቸው፡-** ሁሉ ነገር ፐብሊክ ነው፣ በሚዲያ ላይ ያያሉ። በተለይ የባህልና የቱሪዝም ሚኒስቴር ዳታዎችን ያገኛሉ፤ እነሱ ናቸው ቆጥረው ለጉባኤው ይሄን ያህል ሰው መጥቷል ብለው የነገሩን። እንደውም “አሁን የመጣችሁት አንድ መቶ አስራ አራት ናችሁ። ለሚቀጥለው አንድ ሺኅ አንድ መቶ ሆናችሁ እንድትመጡ” ነበር ያሉን።

የመጀመሪያው አመጣጥና አቀባበል ላይ ጥቂት ችግሮች ነበሩ። ጠ/ሚ/ሩ ምሁራኖችን በአገር ቤት እንድንሰባሰብ ቢፈቅዱልንና ቢጋብዙንም ያ እንዳይሆን ፍላጎት ያላቸው ወገኖች ወይም የመንግስት ባለስልጣናት ነበሩ። ግልፅ ክህደትና ውሸት የፈፀሙብን ከፍተኛ የአገሪቱ ባለስልጣን አሉ። ይሄ ከምን ዓይነት ስሜት እንደሚመነጭና ምን ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች እንደሚያደርጉት እናውቃለን። ለጊዜው እንተወው፤ ዳግም እንዲህ ዓይነቱ ነገር እንደማይፈጠር ተስፋ እናደርጋለን። እኛም ብዙ አልጠየቅንም፤ “ከበፊት ጀምሮ እኛ ከመንግስት አምስት ሳንቲም አንልፈልግም፣ በራሳችን ሆቴል ወጪ ነው የምንመጣው” ብለን ነግረናቸዋል። “እኛ አርጅተናል ስልጣን አንፈልግም፤ ከኪሳችን አውጥተን ትኬት ቆርጠን፣ ሆቴል አርፈን አገራችንን መርዳት ነው የምንፈልገው። እዛ ጥሩ ስራ አለን ባለንበት አገር የሚከፈለንን ደምወዝ እናንተ ለእኛ መክፈል አትችሉም ነበር” ያልናቸው።

ለምሳሌ አሁን እኔ ጡረታ በምወጣበት ጊዜ ገንዘብ አገኛለሁ። ስለዚህ እዚህ መጥቼ ከመንግስት ገንዘብ የምፈልግበት ምክንያት የለም። ዝም ብዬ ምንም ሳልሰራ ቁጭ ብዬ ከምሞት አገሬ አንድ ዩንቨርስቲ ውስጥ ሄጄ አንድ ኮርስ አላስተምርም? ለዚውም በነፃ። እዚህ የማስተምርበት ዩንቨርስቲ በአሜሪካ “ሳባቲካል” የሚባል የእረፍት ጊዜ አለ፣ በእዛ እረፍትህ የግድ አንድ መልካም ነገር መስራት አለብህ፤ ፈረንሳይ ወይም ፔሩ ሄጄ የእረፍት ጊዜዬን ከምሰራ ለምን ኢትዮጵያ መጥቼ ለአገሬና ለሕዝቤ አልሰራም? በዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስትን እጠቅማለሁ እንጂ አልጎዳም። ይሄንን አድርጉልን ነው የእኛ ጥያቄያችን፤

**ግዮን፡- ከሁለት ሳምንት በፊት በባህርዳር ያካሄዳችሁት ሁለተኛው ጉባኤ ከመጀመሪያው የተሻለ፣ ለፍላጎታችሁ ምላሽ የሰጠ ነበር ማለት ይቻላል?**

**ፕ/ር ጌታቸው፡-** አሁን ገባቸው መሰለኝ በደንብ ነው የተቀበሉን። ወደ እዚህ ከመምጣችን በፊት የጉባኤው ዝግጅት ሁልጊዜ አዲስ አበባ መከናወን የለበትም፣ በሌሎች ክልሎችም ማካሄድ እንፈልጋለን፣ ሁሉም ዕድል ሊያገኝ ይገባል አልን። በዚህም መሰረት ባህርዳር ይደረግልን ብለን ጠየቅን ፈቀዱልን። ባህርዳር የኒቨርስቲ ጉባኤውን ለማዘጋጀት ኃላፊነቱን ወሰደ። እኛ ከገመትነው ውጪ በሆነ መንገድ፣ በጣም በሚያምር መልኩ ነው ያዘጋጁት። ከብሔራዊ ቴአትር የመጣ ባንድ ነው ጉባኤያችንን የዘጋው፣ ለክብሩም ለመልዕክቱም ያ ቡድን እኛ ከምንሰራው ስራ ጋር የሚመሳሰል ስለመሰላቸው በጣም ደስ ብሏቸው መጥተው ነው ዝግጅቱን ያደመቁት።

**ግዮን፡- የቪዥን ኢትዮጵያ የገቢ ምንጭ ምንድን ነው?**

**ፕ/ር ጌታቸው፡-** ሁሉን ነገር የምናደርገው ከኪሳችን በሚወጣ ገንዘብ ብቻ ነው። አናስከፈልም። ገንዘብም አንሰበስብም፤ በቪዥን ኢትዮጵያ በኩል ምንም ጥቅም ለማግኘት አንፈልግም። አንድም ቀን የገቢ ማሰባሰቢያ አድርገን አናውቅም። እኛ ሁሌም ለአገራችን ከዕውቀታችን ባሻገር ከራሳችን ኪስ በሚወጣ ገንዘብ ይሄንን ነገር ለመስራት ዝግጁዎች ነን። ከኢትዮጵያ መንግስት የምንፈልገው የመሰብሰቢያ አዳራሽ በነፃ እንዲሰጡን ነው፤ አሜሪካ ውስጥ የሁለት ቀን ኮንፍረንስ ዘጠኝ ሺህ ዶላር ለትላልቅ ሆቴሎች እየከፈለን ነው ጉባኤውን የምናካሂደው።

አሁን ከባህርዳር ዩንቨርስቲ በተማርነው ቀጣይ ጉባኤዎችን ዩንቨርስቲዎች ውስጥ ነው ምናካሂደው። አንደኛ የምሁራን ሰፊ ተሳትፎ ይኖራል፤ ሁለተኛ ወጪ ይቀንሳል። ሶስተኛ በየክልሉ ያሉ ዩንቨርስቲዎችንም በዙር ማዳረስ ይቻላል። በቀጣይ የምናካሂድበትን ወደ አሜሪካ ከተመለስኩ በኋላ ቦርዱ ይወስናል። በጭንቅላታችን ውስጥ ያለው ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ መጓዝ ነው። ከዛ በቀጣይ ሌሎችንም እናዳርሳለን።

**ግዮን፡- ወደ ኢትዮጵያ በምትመጡበት ወቅት በሳምንት ወይም በቀናት ልዩነት በተለያዩ ከተሞችና ዩንቨርስቲዎች ውስጥ ፕሮግራሞቹን የማዘጋጀት ሀሳብስ የላችሁም?**

**ፕ/ር ጌታቸው፡-** ከመጣችሁ አይቀር በተለያየ ቦታ በቀናት ልዩነት ለምን ኮንፍረንሱን አታካሂዱም የሚለው ትንሽ ይከብዳል። በጉባኤው የሚመጡት የቦርድ አባላትና ጽሁፍ አቅራቢዎች ረዘም ላለ ጊዜ እዚህ መቆየት ሊኖርባቸው ነው። አሁን ለምሳሌ ይሄን ጉባኤ ለማዘጋጀት እዚህ ስመጣ አሜሪካ አገር በምሰራበት ዩንቨርስቲ ኦንላይን እያስተማርኩ

ነው ያለሁት፡፡ የረዥም ርቀት ትምህርት በየቀኑ እዚህ ሆኜ እሱን እሰጣለሁ፡፡ ሰሞኑን ለቀናት ኢንተርኔት ተቋርጦ ጉድ ፈልቶብኝ ነበር፡፡ "እረ ባካችሁ ከስራ ልባረር ነው" እያልኩ ስጮህ ነው የቆየሁት፡፡ ረዘም ላለ ጊዜ ወደ እዚህ መጥተህ፣ በየሳምንቱ በየክልሉ እየተዘዋወሩ ኮንፈረንሶችን ላካሂድ ማለት ከብዙ ነገሮች አንፃር ትንሽ ያስቸግራል፡፡

**ግዮን፡- ያኔ በደርግ ዘመን ከአገር ሲወጡ ኢኮኖሚ አጥንቼ፣ አገሬ ገብቼ፣ ሕዝቤን በሙያዬ አግዛለሁ የሚል ጉጉት ነበርዎት፡፡ ግን ሕልምዎ ሳይሳካ ብዙ ዓመታት ቢያልፉም አሁን ዕድሉን አግኝተው ኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ እንደው ምን ተሰማዎት?**

**ፕ/ር ጌታቸው፡-** እንዳልከው እኔ የፈለግሁትን ተምሬያለሁ፡፡ አሁን በማልፈለግበት፣ የእኔ አስተዋፅኦ ምንም ዋጋ በሌለው አገር ነው እየሰራሁ ያለሁት፡፡ በእዛ አገር ጌታቸው ባያስተምርም አሜሪካ ምንም አትሆንም፡፡ ጌታቸው ስላስተማረም ያን ያህል ምንም የለወጠላት ነገር የለም፡፡ ግን ተወዳድሬ ስራ የመያዝ መብት ስላለኝ፣ ለዛ ነው የተሰጠኝ እንጂ ይሄ ሰውዬ ያስፈልገናል ብለው አይደለም፡፡

አንዳንዴ ስታስተምር ደስ የሚልህ ርዕስ አለ፡፡ ተማሪዎች እንዴት እንደሚቀበሉትና እንዴት ከአንተ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተረድተህ ደስ በሚል ሁኔታ ታስተምራለህ፡፡ ልክ ክፍለ ጊዜው ሲያልቅና ተማሪዎቹ ሲወጡ "ለማን ነው ይሄን ያደረግሁት?" ትላለህ፡፡ "ለአገሬ ልጆች ነው? ወይስ እኔ ምናቸውም ላልሆንኩላቸውና ለማላውቃቸው ሰዎች?" ብዬ አንዳንዴ አለቅሳለሁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ብሶት ብዙ ጊዜ ስለሚሰማኝ፣ ቶሎ ቢሮዬ ገብቼ የውስጤን በዕንባ ነው የማወጣው፡፡

መቼ ነው እንዲህ ዓይነቱን ትውልድን በእውቀት የማነፅ ዕድል የማገኘው? አገሬ ገብቼ ደስ ብሎኝ የምሰራውስ መቼ ነው? እላለሁ፡፡



አንድ እውነት ልንገራችሁ፤ ከስድስተኛ ክፍል ጀምሮ እኔ አስተማሪነት እንጂ ሌላ ነገር ሰርቼ አላውቅም፡፡ መሀይምነትን ማጥፋት በሚል ቀን ቀን ጉሊት ሲሸጡ፣ ሲሸከሙ የሚውሉ ሰዎችን ልጅ እያለሁ ማታ ማታ በኃይለስላሴ ዘመን አስተምር ነበር፡፡ ሀይስኩል ከገባሁም በኂላ በክረምት ወቅት ት/ቤቶች ሲዘጉ ከእኛ ዝቅ የሚሉትን እናስተምር ነበር፡፡ እኔ ከትምህርት ዓለም የተለየሁበት ጊዜ የለም፡፡ ኢ.ህ.አ.ሠ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ እንኳን ካድሬ ት/ቤት ውስጥ ነበር የማስተምረው፡፡ ማስተማር በጣም እወዳለሁ፡፡ ይሄን ያህል ዘመን ለአገሬ ሳላደርግ በመቅረቴ ግን ይቆጨኛል፡፡

አሁን ጡረታ ብወጣ ወይም በእረፍታችን የምንሰጠውን የመልካም ስራ አገልግሎት ጊዜ ብወጣ፣ ኢትዮጵያ መጥቼ አስተምራለሁ፡፡ የማስተምርበትን ት/ቤቴን ወክዬ ከፕ/ር ሒሩት ወ/ማርያም ጋር ተነጋግረናል፡፡ በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋምና ቺካጎ በሚገኘው እኔ ባለሁበት ዩንቨርስቲ መሀል አንዳንድ ነገሮች መነጋገር ጀምረዋል፡፡ በኢትዮጵያ ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት አድቫይዘሪ ካውንስል አለ፤ ቪዥን ኢትዮጵያ ውስጥ ይሳተፋል፡፡ በዛ የኢትዮጵያ የዩንቨርስቲዎች የትምህርት ደረጃና ጥራት እንዴት ይጠበቃል? እንዴትስ ማዳረስ ይቻላል? ይሄን ለማድረግስ በውጭ ያለን ኢትዮጵያኖች ምን ልንረዳ እንችላለን? እያንዳንዳችን የምናስተምርባቸው ዩንቨርስቲዎችን እንዴት ከአገራችን ጋር አገናኝተን መስራት እንችላለን? በሚሉት ላይ በጣም ትኩረት ሰጥተን እየሰራን ነው ያለነው፡፡ አሁን ያለው ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ለአገራችን ለመስራት ፈቅዶልናል፡፡ ሁኔታው የተሻለና የሚያሰራ ነው፡፡ ዕንቅፋት ለመሆን የሚሞክሩ ጥቂቶች አሉ፤ ከተለየ አጀንዳ በመነሳት፡፡ እነሱን ወደ ጎን ትቶ ከሌላ ጋር ለመስራት የሚቻልበት ወይንም ደግሞ ቀጥታ መጋፈጥም የሚቻልበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

በእኛ በኩል በጣም ርግጠኞች ነን፤ ምንም ጥቅም አንፈልግም፡፡ ተቃዋሚ አይደለንም፤ ግን ደግሞ አጨብጫቢዎችም አይደለንም፡፡ እውነታን ብቻ ነው ለመናገርም፣ ለማድረግም የምንፈልገው፡፡ ትክክል ያልመሰለንን ነገር ትክክል አይደለም ብለን እንናገራለን፡፡ በዛ የሚመጣብን ነገር ካለም ለመቀበል ዝግጁ ነን፡፡ ይሄን ማድረግ መብታችን ነውና፡፡

**ግዮን፡- ኢትዮጵያ የብዙ ምሁራን ባለቤት ብትሆንም እነዛ ምሁራን ለሰው አገር እንጂ ለእሷ አልሰሩላትም፡፡ ከዚህ በኂላ ይሄ ነገር እንዲቀየር ከእርስዎና ጓደኞችዎ በመነሳት ምሁራኑ ምን ማድረግ አለባቸው ይላሉ?**

**ፕ/ር ጌታቸው፡-** እንደገና በኩራት የምነግራችሁ ነገር፤ ተሰደን በውጭ ያለን ኢትዮጵያውያን ምሁሮች በትምህርት ደረጃ በነፍስ ወከፍ ከዓለም አንደኛ ነን፡፡ አንደኛ፡፡ ፒኤችዲ ያላቸው ዶክተሮች በሁሉም መስክ፣ በሕግ በለው በሳይንስ ብዙ አሉ፡፡ ናሳ ውስጥ ሳይቀር ከፍተኛ ጥናት የሚያደርጉ ኢትዮጵያውያን አሉ፡፡ በየዩንቨርስቲው የምናስተምር ፕሮፌሰሮች በጣም በርካታ ነን፡፡ እነዚህ ሁሉ በእውነተኛ መንገድ ለኢትዮጵያ መስራት የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሮላቸው ከሰሩ አገራችን በአንድ ጊዜ በጣም ትመነጠቃለች፡፡

አሁን ችግር የሆኑብን ተራ የመንደር ፖለቲካዎችንና ዕንቅፋቶችን ማስወገድ ከቻልን፣ በኢትዮጵያዊነት የአንድነት መንፈስ ቆመን፣ በውጭው ዓለም ያሉ ምሁራኖቻችንን መጠቀም ብንችል እንደ እኛ ማንም ዕድለኛና ውጤታማ የሚሆን የለም፡፡ በቅርቡ ባህርዳር ላይ ባካሄድነው ኮንፈረንስ በተለይ በጤና በኩል ተሰልፈው የመጡት የሆስፒታል ኃላፊዎች፣ በዩንቨርስቲዎች ውስጥ ኤክስፐርት ተብለው በከፍተኛ ደምዎዝ የሚያገለግሉ ሁሉ መጥተው ጉባኤውን በመሳተፍ አስተያየቶችም ሰጥተዋል፡፡

ፕሮፌሰር ሳላህዲን አብዲ ትልቅ ሀኪም ናቸው፤ የካንሰር ምርምር ሆስፒታልና ዩንቨርስቲን የሚመሩ፤ ዶ/ር እናውጋው መሀሪን ታውቁታላችሁ በጣም ከፍተኛ ባለሙያ ነው፡፡ እሱ "እኔ ከዛሬ ጀምሮ የቪዥን ኢትዮጵያ አባል ነኝ" ብሎ በጣም ተደስቶ ነው የሄደው፡፡ ብዙ ሰዎች መጥተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ምሁራኖች ከዚህ በኂላ ምንድን ነው ማድረግ ያለባቸው? ለሚለው በቅድሚያ መደራጀት ያስፈልጋቸዋል፡፤ ለየብቻ መሮጥ ሳይሆን የሚገናኙበት አንድ ተቋም ሊኖር ግድ ነው፡፡ ቪዥን ኢትዮጵያ ለምሳሌ የአንድ ሙያ ኤክስፐርቶች ብቻ አይደሉም ያሉበት፤ ሁሉንም አቅፎ ለማንኛውም ዘርፍ ዕድልና መድረክ ይሰጣል፡፡

ለምሳሌ ባህርዳር ላይ አምስት የተለያዩ ዶክተሮች ነበሩ፡፡ ያቀረቡት ጥናት በጣም ይገርማል፡፡ አንድ ታዳሚ ተነስቶ "ለመሆኑ እናንተ አምስታችሁ እርስ በርስ ትተዋወቃላችሁ?" የሚል ጥያቄ ጠየቀ፤ ዶ/ር አልማዝ ከደብረ ብርሃን ዩንቨርስቲ "አንተዋወቅም፤ ግን ከዛሬ ጀምሮ ተጋብተናል" ነበር ያለችው፡፡ እኛ ለባለሙያዎች እንደዚህ ዓይነት የመገናኛ መድረክ እንፈጥራለን፡፡ እነሱም እንዲህ ባለ መልኩ በመተባበር የጋራ መሰባሰቢያ መፍጠር አለባቸው፡፡ ብዙ ዓይነት ሙያዎች በአንድነት የሚዋቀሩበት ሁኔታ በመፍጠር፣ በውጭ ያለን ምሁራን አገራችንን በደንብ መርዳት እንችላለን፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

# “ዳኀዲ ኦነግ” . . .

*ከገጽ 10 የዞረ*

በእጅጉ እንዲዳከም ያደረገ እርምጃ ተወሰደ:: በዚህ እርምጃም ቁጥሩ ወደ 20ሺህ የሚጠጋ የኦነግ ጦር በድንገቴው የሕወሓት/ኢህአዴግ የጥቃት እርምጃ ወዲያው በቁጥጥር ስር ውሎ ለዕስር ሲዳረግ፤ በሺህዎች የሚቆጠሩ የኦነግ ጦር አባላት ደግሞ በተከበቡበት ካምፕ መገደላቸው ተነግሯል::

ይህ ጥቃት ለዓመታት ኦነግ የገነባውን ተዋጊ ጦር በማዳከም፣ የድርጅቱን ተዋጊ ሀይል ቁጥር በእጅጉ አመነመነው:: ይሁን እንጂ ኦነግ ቀድሞውንም ሕወሓት ላይ እምነት ስላልነበረው የተወሰነ ጦሩን ከካምፕ ውጭ እንዲቆይ ማድረግ ችሎ ስለነበር፤ ከካምፕ ውጭ አቆይቶት የነበረውን ጦሩን አሰባስቦ ከኢህአዴግ ጋር ጦርነት ገጠመ:: ኦነግ በዚህ ጦርነት የተወሰነ ድልን መቀዳጀት ችሎ የነበረ ቢሆንም ኢህአዴግ በነበረው የተዋጊ ጦርና የትጥቅ ብልጫ ኦነግን “ከመደበኛ ውጊያ” ወደ “ጎሬላ ውጊያ” እንዲያፈገፍግ አስገድደው::

በዚህም በርካታ የኦነግ ሰራዊት ጉምቱ አመራሮች ከሀገር እንዲወጡና ወደ ውጭ አገራት እንዲሰደዱ ያደረገ አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጠረባቸው:: በተጨማሪም የኦነግ ተዋጊ ሰራዊት በውጊያ አሸንፎ በቁጥጥሩ ስር አውሏቸው የነበሩትን ነጻ የውጊያ ቀጠናዎች ለኢህአዴግ ጦር እያስረከበ እንዲሸሽ ግድ ሆነ::

ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኋላ አብዛኞቹ የኦነግ አባላት ወደ ኤርትራ በመጓዝ የተበተነው ጦራቸውን መልሰው በማሰባሰብ በዚያ ጦራቸውን እንደ አዲስ የሚያዋቅሩበትና በኤርትራ መንግስት ዕገዛ የሚሊተሪ ስልጠና የሚሰጡበትን እድል ማግኘት ቻሉ:: ይህ በእንዲህ እንዳለ በፓርቲው ውስጥ በከፍተኛ አመራሩ መካከል በተፈጠረ የእርስበርስ አለመግባባት ምክንያት ኦነግ የድርጅቱን የትግል እንቅስቃሴ በእጅጉ በጎዳ መልኩ ተከፋፈለ:: ይህ አጋጣሚ ኦነግ ከመንግሥት ጋር ያደርገው የነበረውን የትጥቅ ትግል እንዳዳከመው ይታመናል:: በ1998 ዓ.ም በደቡብ ኦሮሚያ የነበረው የኦነግ ተዋጊ ጦር ወደ ኬንያ በማፈግፈግ እራሱን መልሶ ለማደራጀት ጥረት ማድረግ ጀመረ:: በተመሳሳይ ወቅትም የኢፌዴሪ የመከላከያ ሰራዊት አባል የነበሩት ብርጋዲየር ጀነራል ከማል ገልቹ መቶ የሚሆኑ የመከላከያ ሰራዊት አባላትን በማስከተል የኢትዮጵያን መከላከያ ሠራዊት በመክዳት ኤርትራ የሚገኘውን የኦነግ ጦር ተቀላቀሉ:: ይህ የጀነራሉ ኦነግን መቀላቀል ተዳክሞ ለነበረው የኦነግ እንቅስቃሴ ተጨማሪ ሃይል በመፍጠር በድርጅቱ የትግል እንቅስቃሴ ላይ የሰራዊቱን ሞራል በማነሳሳት ነፍስ እንደዘራበት ይታመናል::

ይሁን እንጂ ብርጋዲየር ጀነራል ከማል ገልቹ ለሁለት ዓመታት ያክል ከኦነግ ጋር አብረው ከሰሩ በኋላ ከኦነግ አመራሮች ጋር በሃሳብ መግባባት ሳይችሉ በመቅራታቸው በ2000 ዓ.ም ጦራቸውን ይዘው ከኦነግ ጋር ፍቺ በመፈጸም የራሳቸውን የፖለቲካ ድርጅት መስርተው ኢትዮጵያን ዲሞክራሲያዊት ሀገር ለማድረግ በተናጥል እንደሚሰሩ ገለጹ:: ኦነግም በበኩሉ ጀነራሉን ከድርጅቱ አባልነት በይፋ እንዳሰናበታቸው ገልጾ መግለጫ አወጣ::

**...ሕወሓት ሰራሹ ኢህአዴግ ትግሉ ሰምሮለት፣ ትግራይ እና አማራ ክልል ላይ የነበረውን የደርግ መንግስት ከደመሰሰ በኋላ ትግሉን ለማስፋት ፊቱን ወደ ኦሮሚያ ክልል አዙሮ ነቀምት ከተማን ለመቆጣጠር ፣ኦሮሚያን ነጻ ማውጣት የሚል እቅድ ነድፎ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመረ...**

እንግዲህ በነዚህ ሁሉ የታሪክ ሂደቶች ውስጥ የራሱን በርካታ የስኬትና የውድቀት ታሪኮች እያሳለፈ የመጣው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)፤ በቅርቡ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ ከመንግሥት የቀረበለትን የሰላም ጥሪ ተከትሎ ወደ አገር ውስጥ በመግባት በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ተስማማ:: በዚህም መሰረት መስከረም 05 ቀን 2011 ዓ.ም ድርጅቱ የቀደመ የትጥቅ ትግል ስትራቴጂውን በመቀየር በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ በአገር ውስጥ በሐሳብ ለመታገል ፈቅዶና ወዶ በሊቀመንበሩ ኦቦ ዳውድ ኢብሳ እየተመራ ከሀገረ ኤርትራ በአየርና በየብስ ወደ አገር ቤት ተመለሰ::

በዚያ ቀንም የኦሮሞ ህዝብ ከዳር ዳር፤ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በነቂስ በመውጣት ለኦነግ አመራሮች የጀግና አቀባበል አደረገላቸው:: ሆኖም ኦነግ ከጥቂት ጊዜያት የአገር ውስጥ ቆይታው በኋላ የድርጅቱን ታሪክ ጥቁር ጥላሸት የሚቀቡ ተግባራትን በመፈጸም በአገር ውስጥ የንትርክና የውዝግብ ምንጭ በመሆን የአገሪቱን የፖለቲካ ከባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳረፈ::

ከነዚህ የኦነግን ታሪክ ያጠለሹ ኩነቶች መካከል፦ ድርጅቱ በሰላማዊ መንገድ ወደ አገር ገብቶ ለመታገል ተስማምቶ ሲያበቃ፤ ትጥቅ አልፈታም በማለቱ ከመንግሥት ጋር የፈጠረው ውዝግብና ፍጥጫ፣ አመራሮቹ አዲስ አበባ ላይ ተቀምጠው በመንግሥት ጦር ላይ የጦርነት አዋጅ ማወጃቸው፣ የድርጅቱ ታጣቂዎች በርካታ ባንኮች መዝረፋቸው፣ በወለጋ ህዝብ ላይ የድርጅቱ ታጣቂዎች ያደረሷቸው በደሎች፣ በአማሮ ኬሌ የኦነግ ታጣቂዎች የፈጸሟቸው ተደጋጋሚ የዝርፊያ ወንጀሎች፣ በከሚሴ፣ በወሎ አካባቢዎችና በጋምቤላ በተፈጠሩ ደም አፋሳሽ ግጭቶች ውስጥ በተሳታፊነት ስሙ መነሳቱ ወዘተ… ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው::

በቅርቡ ደግሞ ከሁሉም የኦሮሞ ህዝቦች በላቀ ሁኔታ የኦነግ ህዝባዊ መሰረትና ዋነኛ ደጋፊ ተደርጎ የሚወሰደው የወለጋ ህዝብ በሰላማዊ ሰልፍ “የኦነግ ነገር በቃኝ፣ መንግስት ኦነግን ከትክሻዬ ላይ ያውርድልኝ” በማለት ያካሄደውን ሰላማዊ ሰልፍ አንድምታ ላጤነ፤ የድርጅቱ የአራት አስርት ዓመታት ጉዞ የመጨረሻው መጀመሪያ ላይ እንደደረሰ ለመገንዘብ የሚችልበት ደረጃ ላይ ሊያደርሰው ይችላል::

በርግጥ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አሁን ባለበት ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ቁመናው፤ በርካታ ጥያቄ የሚያጭሩና የተወሳሰቡ ችግሮች ውስጥ እንደሚገኝ መረዳት ይቻላል:: ድርጅቱ አሁን ባለበት ሁኔታ ውስጥ ከሚነሱበት ውሱንነቶችና ካጋጠሙት ፈታኝ ተግዳሮቶች መካከል በአለፍ ገደም ጥቂቶቹን በማሳያነትለመመልከት እንሞክር::

በዚህ ረገድ በቀዳሚነት የሚነሳው፤ ድርጅቱ ግልጽ የሆነ የፖለቲካ መስመርና ርዕዮተ ዓለማዊ መሰረት አለመያዙ ወይም ቢያንስ እስካሁን ድረስ በይፋ አለማሳወቁ እንደ አንድ የድርጅቱ ደካማ ጎን ተደርጎ በብዙዎች ሲነሳ የሚደመጥ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም በኦቦ ዳውድ ኢብሳ በሚመራው የድርጅቱ የፖለቲካ አመራር (ABO) እና በኦቦ ኩምሳ ድሪባ (ጃልመሮ) በሚመራው የድርጅቱ ተዋጊ ክንፍ (WBO) መካከል የተፈጠረው አለመናበብና ጫፍ የወጣ አለመግባባት ተባብሶ በቅርቡ ተዋጊ ኃይሉ ከእንግዲህ ከፖለቲካ አመራሩ ትዕዛዝ እንደማይቀበልና እራሱን ከፖለቲካ ኃይሉ መገንጠሉን በይፋ የማሳወቅ ደረጃ ላይ መድረሱ፣ ኦነግ በቀጣይ ህልውናውን ክፉኛ በሚፈታተን መልኩ ክፍፍል ውስጥ መግባቱን የሚያመለክት ነው::

ባጠቃላይ የኦሮሞን ህዝብ ጥያቄ ከማንም ቀድሞ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ በተደራጀ መልኩ ፋና ወጊ በመሆን እንዳነሳ የሚነገርለት “የኦሮሞ ነጻነት ግንባር” (ኦነግ)፤ በኦሮሞ ህዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥ የስሜት ምንጭ በመሆንና በትግል ተምሳሌትነት ያበረከተው አስተዋጽኦ እንደተጠበቀ ቢሆንም፤ ከድርጅቱ ጋር በተያያዘ አያሌ የኦሮሞ ህዝቦችን መስዋዕትነት ማስከፈሉ የሚዘነጋ አይደለም::

ይሁን እንጂ ድርጅቱ ከአርባ ዓመታት የትግል ጉዞው ተሞክሮና ልምድ በመውሰድ ጊዜውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የኦሮሞ ህዝቦችን ጥቅም ባገናዘበና በሚመጥን አግባብ፣ በየጊዜው እራሱን እየፈተሸ እንዳስፈላጊነቱ በሚቀያየርና ወቅቱን በሚመጥን መልኩ የፖለቲካ እስትራቴጂ ቅኝት እየቃኘ ከመሄድ ይልቅ፤ ዛሬም በተዘበራረቀና ወቅቱን ባላገናዘበ የፖለቲካ አካሄድ ላይ እራሱን ቸንክሮ ማስቀረቱ፤ “እታገልለታለሁ” ካለው የኦሮሞ ህዝብ ልብ እየራቀው እንደመጣና ከኦሮሞ ማህበረሰብ ውጭ ባሉ ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ዘንድ ያለው የቆየ አሉታዊ ገጽታ ይበልጡኑ እንዲያይል አድርጎታል ብለው የሚገልጹ ወገኖች ቁጥር ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም::

ይልቁንም በድርጅቱ ውስጥ ተራማጅ አስተሳሰብ ያላቸውንና ለኦሮሞ ህዝቦችም ይሁን ለጠቅላላው አገራዊ ፖለቲካችንና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የላቀ ሚናና አበርክቶ ሊኖራቸው የሚችሉ እንደነ ኦቦ ሌንጮ ለታና ኦቦ ሌንጮ ባቲን የመሰሉ ልሂቃንን ከድርጅቱ ማራቁ፤ ለድርጅቱ ዕድገትና አዲስ ሃሳብ የማፍለቅ ሂደት አደጋን መጋረጡ በድርጅቱ ላይ ከሚነሱበት ውስንነቶች መካከል በጉልህ የሚነሳ ነጥብ ነው::

ለማጠቃለል ያህል፤ ኦነግ ወቅቱና መድረኩ በሚጠይቀው ደረጃ እራሱን ፈትሾና አጠናክሮ በኦሮሞ ህዝቦችም ይሁን በጠቅላላው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ብቁ ሆኖ በመገኘት፤ ድርጅታዊና አገራዊ ተልዕኮውን ጉልህ በሆነ መልኩ ለመወጣት እራሱን በጥልቀት መርምሮና ፈትሾ፤ ከላይ የጠቃቀስናቸውን ችግሮቹን ቀርፎ በአዲስ መልክ መምጣት ይጠበቅበታል እንላለን:: የሆነው ሆኖ ድርጅቱ ይህንን ለማድረግ የሚሳነው ከሆነ፤ በአርባ ዓመታት የትግል ጉዞው ውስጥ ድርጅቱ በመስዋዕትነት የተከፈለውን ውድ የኦሮሞ ልጆች የመስዋዕትነት ዋጋ ሊያሳጣ የሚችል የታሪክ ተወቃሽነትን የሚያስከትል አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል መገመት አያዳግትም::

# በጠ/ሚ/ር ዐቢይ ቿልተኝነት የብር የመግዣ አቅም እየወረደ ነው



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት በ1998 ዓ.ም በቀረበ የኦዲተር ሪፖርት፤ የክልል መስተዳድሮችን የሂሳብ አያያዝ መቆጣጠር እንዳልተቻለ ተገልጿል፡ በቀረበው ሪፖርት ላይ የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ "ክልሎች በጀታቸውን ቢፈልጉ ያቃጥሉት" የሚል እብሪት የተሞላበት አስተያየት ሰጥተውም ነበር፡፡ ክልሎቹ ግን የሕዝብን ገንዘብ እንደተባለው ባያቃጥሉትም፣ወደ አዲስ አበባና ወደ ውጭ አገራት እያጋዙ አገራችንን ለከፋ ድህነት ዳርገዋት እንደነበር ከበቂ በላይ ማስረጃዎች አሉ፡፡ በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ በአዲስ አበባ በተከታታይ እጅግ ፈጣን የሚባል የገንዘብ እንቀስቃሴ ልማት እንደነበረ ማንም ሊመሰክረው የሚችለው ጉዳይ ነው፡፡ ሕወሓቶች መቼም ከስልጣናችን እንወርዳለን ብለው አስበው ስላልነበር እጅግ በርካታ ቢሊዮን ብሮችን ራሳቸውን ለሚጠቅም ከፍተኛ ልማት አውለዋል፡፡

አሁን በድንገት ሥልጣናቸውን ሲያጡ ግን የሆነው በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ የጨረቃ ቦታ ይዘው ሕጋዊ ያደረጉትን ይዞታ፤ ወይም በተለያየ መንገድ ያለሙትን ቋሚ ሐብት በከፍተኛ ገንዘብ በመሸጥ፣ ገንዘቡን በጥቁር ገበያ በተገኘው ምንዛሬ እየቀየሩ ወደ መቀሌና ውጭ አገር በማዘዋወር ላይ ናቸው፡፡

እነዚህ ሰዎች ያፈሩት ሀብት ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የነበረ ከመሆኑም በላይ፣ በዚህ መጠን ከፍተኛ የገንዘብ ሀብት ከአንድ የአገር ክልል ወደ ሌላ የአገር ክልል ሲጓዝ በሁሉም መመዘኛ አደጋው የከፋ ነው፡፡ በጣም የሚገርመው ይህ ሁሉ ጉድ በከተማው ሲከናወን፣ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ የቤተ መንግስት አጥር በማሰራትና መካነ እንስሳት በማሰራት ሥራ ላይ ተጠምደዋል፡፡

በ1998 በቀረበው የኦዲት ሪፖርት መሰረት (ሁኔታው እስከ አሁንም ቀጥሏል) ለ28 ዓመት ኦዲት የማይደረጉ የሕዝብ አስተዳዳሪዎች ያሉባት አገር በኔ እምነት በአለም ላይ ኢትዮጵያ ብቻ ትመሥለኛለች፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ ምዝበራ ተካሂዶ፣ እንዲህ ዓይነት የተበላሸ ሥርዓት ባለበት አገር ድህነት፣ ወንጀል፣ የውጭ ዕዳ መናር ወዘተ ቢበዛ ምን ያስደንቃል?

በሌላ አነጋገር እነዚህ መዝባሪዎች ከነጋዴው ባልተናነሰ መልኩ በገበያ ያለውን ዶላር ለመቀራመት ሲሯሯጡ እና የብር የመግዛት አቅም በዚህ መልኩ ቢቀንስ ብዙም አያስደንቅም፡፡በኢኮኖሚክስ "ሀ" "ሁ" አንድን ነገር የሚፈልጉ ኃይሎች በብዙ ቁጥር የዚያ ነገር ዋጋ ውድ መሆኑ የግድ ነው፡፡ለዚህ ነው በደርግ ዘመን በ2 ብር ከ7 ሳንቲም ይመነዘር የነበረው ዶላር አሁን ከአርባ ብር በላይ የደረሰው፡፡ ይህ ደግሞ ቋሚ ገቢ ባላ ደሞዝተኛ ላይ የሚፈጥረው ጫና ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ ሊቅ መሆን አያስፈልግም፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ለ28 ዓመታት በፌደራል ኦዲተር ኦዲት ያልተደረጉ ባለስልጣናት ሳይሰሩ ያገኙትን ሀብት ገበያ ውስጥ እየረጩ አስደንጋጭ የዋጋ ግሽፈት ቢፈጥሩ በእጅጉ የሚጠበቅ ነው፡፡ እዚህ ላይ የግድ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ የፌደራል መንግስት ይቅርና አንድ ባንክ እንኳን በብድር የሠጠውን ገንዘብ ተበዳሪው ምን እየሰራበት እንደሆነ የመቆጣጠር ሙሉ ስልጣን አለው፡፡

የፌደራል መንግስት ከኢትዮጵያ ሕዝቦችን አንገት አንቆና የግድ "ክፈል" ብሎ የሰበሰበውን ገንዘብ ለቀማኞች እያስረከበ፣ አገራችን አሁን የደረሰችበት አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንድትደርስ አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብም ዶ/ር ዐቢይ ወደ ስልጣን ሲመጡ፣ ይህ ሁኔታ ይለወጣል ብሎ ያደረበት ስሜት አሁን ከመቀዝቀዝም አልፎ በረዶ እየሰራ ነው፡፡

አሁን ሕወሓት ኢሕአዴግ ከስልጣን በመወገዱ እና ወደ ትግራይ በማፈግፈጉ፣ እዚህ አዲስ አበባ ያሉ የሕወሓት አባላት ንብረታቸውን በከፍተኛ ፍጥነት በመሸጥ ላይ ሲሆኑ፤ በሌላ አነጋገር ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ከአዲስ አበባ ወደ ትግራይና ወደ ውጭ አገር ማጓጓዙ በትግራይ ሕዝብ ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ አለ፡፡ ብዙ ገንዘብ ወደ ክልሉ ሲጓዝ የወር ደምዎዝተኛ የሆነው ማሕበረሰብ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የኑሮ ውድነት ያጋጥመዋል፡፡ ምክንያቱም በክልሉ ካለው የገንዘብ መጠን የሚነፃፀር የምርት አቅርቦት ስለማይኖር፡፡ በመሆኑም ክልላዊ ግሽፈት ያስከትላል፡፡ በማንኛውም የኢኮኖሚ ስርዓት ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ መንቀሳቀሱ ጤነኛ ያልሆነ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ መፍጠሩ አይቀርም፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የተበላሸ የገንዘብ አስተዳደር ስርዓት አንዱ አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት በአንድ የአገሪቱ ክልል ያፈራውን ከፍተኛ የገንዘብ ሀብት ባንክ ካስገባ በኋላ ሌላ፣ ክልል ሄዶ ያንኑ ገንዘብ ከባንክ ቢያወጣው የሚከለክል ምንም ዓይነት አሰራር ባለመኖሩ በመላው አገሪቱ ጤነኛ ያልሆነ የገንዘብ አወጣጥ ስርዓት ይስተዋላል፡፡ መሆን የነበረበት አንድ ሰው ከፍተኛ ገንዘብ አንድ ክልል ያለ ባንክ ካስገባ በሌላ ክልል ያንን ገንዘብ ሊያወጣ ሲሞክር "ይህ ገንዘብ እከሌ የሚባል ክልል በሚገኝ ባንክ የገባ በመሆኑ መውጣት የሚችለውም እዚያው ነው" የሚል ምላሽ የሚሰጥ አሰራር መዘርጋት ነበረበት፡፡

የያዝነው ዓመት ሊጠናቀቅ ጥቂት ቀናት ብቻ የቀረው በመሆኑ የፌደራልም የክልሎችም የተሰበሰበ ገቢ ሪፖርት እየወጣ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አሁንም የፌደራል ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ቅናሽ ሲያሳይ፣ የአዲስ አበባ የአስር ወር ገቢ ግን በ18% ጭማሪ እንዳሳየ ዘገባው ያሳያል፡፡ ይህ የሆነው የመሬት ሊዝ ሽያጭ ሙሉ በሙሉ በቆመበት ሁኔታ ነው፡፡ በኔ ዕምነት በአንድ አገር ውስጥ ይህን ያህል የተዘበራረቀ ልዩነት መከሰቱ ጤነኛ አይመስለኝም፡፡ ምናልባት ሙያችሁ የሆነ ኢኮኖሚስቶች በጉዳይ ላይ ሀሳብ ብትሰነዝሩ መልካም ይመስለኛል፡፡

ለዚህ ጽሁፍ እንደ መነሻ የወሰድኩት በአገሪቱ እየተከሰተ ያለው እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ እና የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ የትኩረት አቅጣጫ ለኔ በምንም መልኩ ሊዋጥልኝ ባለመቻሉ ነው፡፡

ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ምንም ችግር ያልነበረበትን የቤተ መንግስት አጥር አፍርሰው የሚያሰሩበት ገንዘብ ፣በእርግጠኝነት ሰቆጣ (በሌሎች አካባቢዎችም) ዛፍ ሥር ጸሐይ፣ አቧራና ብርድ እየተፈራረቀባቸው ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ለሚማሩ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ማሰሪያ ቢያውሉት በእጅጉ የተሻለ ነው የሚል የግል አስተያየት አለኝ፡፡

ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊመሰክረው የሚችለው ዋነኛ ነጥብ በአገሪቱ ያለ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይና የኢህአዴግ ባለስልጣናት የትኩረት አቅጣጫ በእጅጉ የተለያየ መሆኑ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄር ግጭት፣ የወጣቶች የሥራ አጥነት፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት የመሳሰሉ እጅግ ፈጣን ምላሽ የሚፈልጉ ጉዳዮች እያሉ በቴሌቭዥን መስኮታችን ስራ፣ ክልል፣ ድንበር የመሳሰሉ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ጉዳዮች ሰፊ የዜናና የዶክሜንተሪ ትኩረት ማግኘታቸው ያሳስበኛል፡፡ በጣም አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮችን የምንሰማው ከEBC ውጭ ባሉ የዜና ምንጮች መሆኑ፣ ሕብረተሰቡ የመረጃ ውዥንብር ውስጥ እንዲገባ የሚያደርገው በመሆኑ የመንግስት ሚዲያ ተቋማት ወሳኝ የሆኑ ክስተቶችን ሳይዘገይ፣ ሕብረተሰቡ ሳይወናበድ በተቻለ ፍጥነት ወደ ሕዝብ ጆሮ ለማድረስ ተግታችሁ ብትሰሩ የተሻለ ነው ለማለት እወዳለሁ፡፡

# 6ቱ የሆቴል ሾው አፍሪካ ምርጥ ተሸላሚዎች

## "ይህ እንደ አገር የተገነባውን ስም እንዳይጠፋ በተሳካ ሁኔታ አልፈነዋል"

### አቶ ቁም ነገር ተከተል

"ሆቴል ሾው አፍሪካ 2011" በአፍሪካ ካሉት ፤ ትልቁ የሆስፒታሊቲ እና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት፣ አውደ ርዕይ አንዱ ሲሆን፣ 7ኛው ሆስፒታሊቲ እና ቢዝነስ ግሩፕ በሚሊኒየም አዳራሽ ከሰኔ 20-23ቀን 2011ዓ.ም ሲካሄድ፤ የማይስ ኢስት አፍሪካ ፎረም "የዓውደ - ርዕይ ግብዣ" ባደረገበት ወቅት፣ ኦዚ አማካሪዎች ዓለም አቀፍ የሆቴል ፕሮጀክት ስድስት "ምርጥ" ላላቸው ካምፓኒና ግለሰቦች እውቅናና ልዩ ሽልማቶችን ሸልሟል፡፡ በተዘጋጀው ዓውደ ርዕይ ላይ ፈርኒቸርና ተገጣጣሚ ማሽነሪዎች፣ ኤሌክትሪካል እና ሚካኒካል ቴክኖሎጂዎች፣ ኢንቲሪየር እና አርክቴክቸራል ዲዛይን፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ጤና እና ሴኩውሪቲ ቴክኖሎጂ፣ አላቂ መገልገያ ዕቃዎች እና ማሽኖች፣ የዘመናዊ ሆቴሎች፣ ባህላዊ ሎጅ እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተሳታፊ ነበሩበት፡፡ በኤግዚቢሽኑ ላይ በስፋት የቀረቡ ምርቶችን፣ የዓውደ -ርዕዩን ገፅታና ተሸላሚዎቹን በተመለከተ የግዮን ጋዜጠኛሙሉጌታ አክሊሉ ያጠናቀረውን ዘገባ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡

ኢንተርናሽናል ዝግጅቶች ሲዘጋጁ ብዙውን ጊዜ የተለመደው ነገር "በእዚህ ሴክተር ላይ ጥሩ ተግባር የፈፀመው ማነው? የተሻለ ውለታ ለዘርፉ ያበረከተውስ?"የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በዘርፉ ላይ ኃላፊነት ተሰምቷቸው ሥራቸውን በአግባቡ የሚሰሩ ሰዎችን በየካታጎሪው መምረጥ ተቀዳሚ ተግባሩ ባደረገው"AFRICAN TOURISM AND HOSPITALITY PERSONALITY OF THE YEAR 2018/19"በተሰኘው ፕሮግራም በትራቭል ሴክተሩ ላይ ተሳትፎ ካደረጉ ሰዎች መሀል አቶ ተወልደ ገ/ማርያም ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ አቶ ተወልደ በሶስት ዋና ዋና ነጥቦችእንደተመረጡ የኦዚ ቢዝነስና ሆስፒታሊቲ ግሩፕ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ቁምነገር ተከተል ይናገራሉ፡፡"የመጀመሪያውና ዋነኛው ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በተያያዘ የ‹ኤክስፓንሽኑ ፕላን› ላይ በውጤታማነትመጨረሳቸውና ሊደርሽፑን (አመራሩን) መውሰዳቸው ጥሩ እንቅስቃሴ ፤በሁለተኛ ደረጃ የኢትዮጵያን አየር መንገድ በደረሰበት አደጋ አገርን ‹ፕሮቴክት› ከማድረግ አኳያ፣ የአገርን ስምና ዝናን ከማኔጅመንታቸው ጋር በማስጠበቅ ለሰሩት ስራ፡፡በመጨረሻም የኢትዮጵያ አየር መንገድ የ2025 ዓ.ም ዕቅዳቸውን ‹አቺቭ › (የስራ አፈፃፀም)አድርገው የ2035 ዓ.ም ዕቅድን ከ15 ዓመት በኋላ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የት እንደሚደርስ ፕሮግራም አውጥተዋል፡፡ በእነዚህ 3ቱ ምክንያቶች ተሸላሚ ሆነዋል"ብለዋል፡፡

ሁለቱTOP WOMEN IN TOURISM AFRICA 2018, MS LILLY AJAROVA CEO UGNADA TOURISM BOARD AND CONSERVANTIONIS JUNE, 2019 እና TOP ETHIOPIAN WOMEN IN TOURISM 2018 እና MRS SAMRAWIT MOGSES CEO TRAVEL ETHIOPIA JUNE 2019 መሆናቸው በሽልማት ሥነ-ሥርአቱ ከሸላሚዎቹ ተገልጿል፡፡‹‹ቶፕ ውመን››(ከአፍሪካ ውስጥ እና ከኢትዮጵያ ውስጥ ሁለቱም በተመሳሳይ )በቱሪዝም እንቅስቃሴ ያደረጉ እነማን ናቸው?" ብለን ስንወስድ፣ አንዷ የዩጋንዳ የቱሪዝም ቦርድ ኃላፊዋ ሚስ ሊሊን ስለሆኑ አዋርዱን ሰጥተናቸዋል፡፡ይህ ደግሞ ጠቃሚነቱ በአፍሪካ ውስጥ በ"ኮንሰርቬሽን" (ጥበቃ) ላይሀብትንከመጠበቅ፣ ደንን ከመጠበቅ፣ ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ጥረቶችን ‹ሰፖርት› ያደረጉትን ሰዎች መርጠን ነው ሽልማትና የማበረታቻ እውቅና ያደረግነው"ብለዋል አቶ ቁምነገር ተከተል በሽልማቱ ስነ ስርዓት ላይ፡፡

በዚህ ዘርፍ የተመረጡትበኢትዮጵያ የ "ትራቭል ኢንዱስትሪ" ላይ እንደ ሮል ሞዴል ጥንቃቄን በተሞላበት ብዙ ነገሮችን ያደረጉትና የሰሩት ወ/ሮ ሳምራዊት ሞገስ የ "ትራቭል ኢትዮጵያ" ባለቤት ናቸው፡፡ ተሸላሚዋምበዝግጅቱ ላይ ተገኝተው ሽልማታቸውን ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስትርዋ ዶ/ር ሂሩት ካሳው እጅ ተረክበዋል ፡፡ "ኢኮ ቱሪዝም ላይአግሬሲቭሊ በመስራት የአዲስ አፍሪካ ኮንቬንሽን ሴንተር እንዲሰራ እና እንዲቋቋም ጥረት በማድረግ፣ በትራቭል ኢንዱስትሪው ላይ ጠንካራ አቋሞች እንዲኖሩ ‹አድቮኮሲ› በመሥራት የምትታወቅ ሴት በመሆኗ ነው ወ/ሮ ሳምራዊት ሞገስን የመረጥናት" በማለት የኦዚ አማካሪዎች ባለቤት አሸናፊዋን በጥሩ መንገድ ገልጸዋታል፡፡

"በቱሪዝም ላይ የሚፅፍ፣ የሚሰራና ለዘርፉ ድጋፍ እያደረገ ያለ ጋዜጠኛ












ማነው?"በሚለው TOP TOURISM JOURNALIST IN ETHIOPIA 2018, HENOK SEYOUM, HAGERE MEDIA AND COMMUNICATION, JUNE 2019 ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩምን ሁሉንም ሰው ባስማማ መልኩ ተሸላሚ ሆኗል።ከዚህ ቀደም ሄኖክ ስዩም የተለያዩ ሽልማቶችን አግኝቷል። "በቱሪዝም የጋዜጠኝነት ዘርፍ ላይ በትክክል ራሱን የሚገልጽ አይነት አዋርድ ተሰጥቶት ባያውቅም ሁልጊዜ የእርሱን ፅሁፎችና እውቀት እንጠቀማለን። ይህንንም ታሳቢ በማድረግ ነው ሄኖክን የመረጥነው"ብለዋል የኦዚ ቢዝነስና ሆስፒታሊቲ ግሩፕ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ቁምነገር።

እውቅናና ሽልማቱን እንዲያገኙ ከተመረጡት ውስጥ CATERIA AND TOURISM TRAINING INSTITUTION(CTTI) 50 ANNIVESERY የካትሪንግ ስኩል 50ኛ ዓመታቸውን በማስመልከትና በአጠቃላይም በዘርፉ ለሰሩት መልካም ስራ ተሸላሚ ሆነዋል።

ሌላው ተሸላሚና ዕውቅና ያገኙት "ኢንቫይሮመንታል ፍሬንድሊ ፕሮጀክቶች ምንድናቸው? ብለን በሆቴሎች በራሳችን መንገድ ግምገማ ወስደናል። መስፈርቱም ለኢንቫይሮመንት የሚጨነቁ፣ ከገበሬው ጋር አብረው የሚሰሩ፣ ሆቴላቸው ‹ኢንቫይሮመንታል ፍሬንድሊ› እንዲሆኑ ከሚያደርጉ አዳዲስ ፕሮጀክቶች መካከል በዋናነትTOP ENVIROMENTAL FRIENDLY HOTEL IN ETHIOPIA 2019, HYAH REGENCY ADDIS ABABA ETHIOPIA, JUNE 2019, የሀያት ሪጀንሲ አዲሱ ሆቴል ተመራጭ ሊሆን ችሏል" ብለዋል አቶ ቁምነገር በሽልማትና በዕውቅና ፕሮግራሙ ላይ።

ኦዚ በ2011 ዓ.ም በሆቴል ሾው አፍሪካ ካቀረባቸው፣ ካካተታቸው እና ከተደረጉ የተለዩና አዲስ ስራዎች ውስጥ የቱርክ (ተርንኪ) ካምፓኒዎች ነበሩ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ፕሮጀክቶችን አጠቃለው የሚሰሩ ኢንተርናሽናል ካምፓኒዎችምተሳታፊ ነበር፡ ፡ አንድ ካምፓኒ በስሩ ያሉ 60 ድርጅቶችን ይዞየመጣበትንሂደትም በስፍራው ተገኝተን ለመረዳት ችለናል። የዚህ ዓይነት ስራዎችና ፕሮጀክቶች እንዴት እንደሚሰሩ ከማመላከት ባሻገር ፕሮጀከቶች እንዴት እየዘመኑ እንደሆነ ከዓውደ -ርዕዩ ለማሳየት ረድቷል።

የ`ኦዚ ቢዝነስና ሆስፒታሊቲ ግሩፕ ማኔጂንግ ዳይሬክተር እንደተናገሩት "ሥልጣኔ ባህልን ትተህ አይደለም። ባህልን የተወ ስልጣኔ ስልጣኔ አይደለም፣ እርሱ ኋላቀርነት ነው፡ ፡ የሆስፒታሊቲ አስተሳብ የሚመነጨው ከባህል ስለሆነ፣ የቱሪዝምን አካሄድ ከባህል ጋር አዋቅረው የሚሄዱትን ሰዎች ስንመለከት ሎጆች በተሰሩበት ቦታ ገበሬውን የሚረዱ፣ ገበሬውን ያዋቀረ እና ያሳተፈ እንቅስቃሴ ያካተቱ ሎጆች ምን ያህል ውጤታማ እንደሚሆኑ ታይተዋል። ገበሬዎች ምን ያህል ተጠቃሚና ደስተኛ እንደሚሆኑ ለማሳየት በመክፈቻ ፕሮግራማችን MULU ECO LODGE እንደምሳሌ የቀረበ ፕሮጀክት ነው።" በማለት አድናቆታቸውን ቸረዋል።

"የመጨረሻውን ቴክኖሎጂና ከገጠር ውስጥ ያለውን ውብ አስተሳሰብ ለማሳየት በዓውደ-ርዕዩ ተሞክሯል። ከአዕምሮ ዝግመት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ልጆች (የኦቲዝም ተጠቂዎች)፣ ከጃክሰን (ታደሰ ገብሬ) የውዝዋዜና የዳንስ ግሩፕ ጋር በመሆን ያሳዩት ትርኢት የተሻለ ነገር ይዘው መምጣት እንደሚችሉ አመላክቷል። "ሁልጊዜ የምናውቃቸውን ሰዎች ጭፈራዎችን ብቻ ሳይሆን ማሳየት ያለብን፣ እነዚህ ሰዎች ከእኛ በተሻለ ምን ያህል አገራቸውን ሊጠቅሙ የሚችሉ ዜጋ እንደሆኑ ካቀረቡት ኢትዮጵያዊ ዘፈንና ባህላዊ ውዝዋዜ ለማየት ችለናል። እነዚህን ነገሮች ስናሳይና በሁለቱም አቅጣጫ ማዋቀር ስንችል ውቧን ኢትዮጵያ ማየት እንችላለን ብለን ስላሰብን ፕሮገራሙን አዘጋጅተናልም" ሲሉ ተደምጠዋል።

"በሚሊኒየም አዳራሽ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ካምፓኒዎች ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ፣ ከዴንማርክ፣ ከዱባይ፣ ከህንድ፣ ከቻይና፣ ከተርኪሽ፣ ከዩናይትድ አረብ ኢምሬት በመምጣት ተሳትፈዋል። 150 ተሳታፊዎች እና ከ50 በላይ ብራንዶች ‹‹ሪፕረዘንት›› አርገው ነው የመጡት፣ ይህ ለእኛ ትልቅ እንቅስቃሴ ነው። እነዚህ ሰዎች የመጨረሻውን ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ አምጥተው ለማሳየት ሞክረዋል።" ያሉት አቶ ቁምነገር ተከተል። ኤክስፖው ውጤታማ እየሆነ እየቀጠለ መሆኑንና ከጎብኚው ቁጥር አንፃር የመጀመሪያው ቀን ቀዝቀዝ ያለ ቢሆንም ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ ህዝብ እየጎበኘው እንደነበር ገልጸው፤ " በእኛ በኩል እምነታችን ኢንቨስትመንቱ መፋጠን አለበት፣ ሰዎች የራሳቸውን እንቅስቃሴ ማድረግ አለባቸው፣ ድጋፍ ማድረግ ባለብን ደረጃ ኢንቨስትመንቱን ማገዝ ስላለብንና መቋረጥ ስሌለበት እየሰራን እንገኛለን። ከባድ ኪሳራ ውስጥ ብንሆንም፣ ማቆሙ ስህተት መስሎ ስለታየን ሁሉንም ነገር ችለን ዐውደ- ርዕዩ እንዲካሄድ አድርገናል" በማለት ለሀገር ሲሉ የከፈሉትን መስዋእትነት ግልጽ አድርገዋል።

"ሁሉንም ነገር መንግስት ይፈፅማል ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም፤ በመጀመሪያ ደረጃ ማድረግ እንደምትችል ካወቅህ ማድረግ ነው እንጂ መንግስትን መጠበቅ አያስፈልግም›› የሚሉት ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ አያይዘውም "እኛ ይኼን ነገር አዘጋጅተናል፣ ለአገር ይጠቅማል-አገርን ያስተዋውቃል ብለን ያሰብነውን ነገር ከተቀበሉ ለእኔ እርዳታ ነው፡ ፡ እኔ መንግስትን የምጠቁመው ‹ፕራይቬት ሴክተሩ፣ የቢዝነሱን ፕሮሞሽን› ጉዳይ ቅድሚያ እንዲሰጡት ነው። የግሉ ሴክተር ነው አገርን መቀየር የሚችለው የሚል እምነት መንግስት እስኪያዘ ድረስ አገር ይቀየራል። መንግስትንም ግለሰብንም ሀገርንም ማስተዋወቅ እስከቻለ ድረስ ሁሉ ነገር ከተፈቀደ፣ የተከለከለ ነገር የለም ብዬ ነው የማስበው። እውቅናውንና ሽልማቱን እኛ ያዘጋጀነው ቢሆንም ሽላሚው የመንግስት አካል መሆኑና የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር አላማችንን ለመደገፍ ከጎናችን ስለነበሩ እናመሰግናለን" ሲሉ ተናግረዋል።

...ባህልን የተወ ስልጣኔ ስልጣኔ አይደለም፣ እርሱ ኋላቀርነት ነው። የሆስፒታሊቲ አስተሳብ የሚመነጨው ከባህል ስለሆነ፣ የቱሪዝምን አካሄድ ከባህል ጋር አዋቅረው የሚሄዱትን ሰዎች ስንመለከት ሎጆች በተሰሩበት ቦታ ገበሬውን የሚረዱ፣ ገበሬውን ያዋቀረ እና ያሳተፈ እንቅስቃሴ ያካተቱ ሎጆች ምን ያህል ውጤታማ እንደሚሆኑ ታይተዋል...

"በገንዘብ ደረጃ ኪሳራ ውስጥ መውደቃቸውን የነገሩንማኔጂንግ ዳይሬክተሩ"በቢዝነስ ላይ ችግሮች ይደርሳሉ፣ ጉዳቶችም ይደርሳሉ፤ ምንም ጥርጥር የለውም። የመጣው አደጋ አንድ ሰው ዝም ብሎ የፈጠረው አደጋ አይደለም። በአገር ላይ የመጣና የተፈጠረ እስከሆነ ጊዜ ድረስ እርሱን በጋራ ነው መወጣትና መቻል ያለብን ብዬ የማስበው፡ ፡ ጉዳቱ ብዙ እንዳይሆን ነው ማሰብ የሚያስፈልገው። ጉዳት ከመጣ በኋላ ጉዳቱን እንዴት መቀነስ ይቻላል?› በሚል ስትራቴጂ መሆን ያለብን እንጂ፣ ጉዳቱ አይምጣ ብሎ ማሰብ አይቻልም። ጉዳቱ እንዳይባባስ ምን እናድርግ? የሚለው ላይ ስንሰራ ነበር። ዓለም አቀፍ ኢንቨስተሮች የተመዘገቡ ፕሮገራሙን ሰርዘዋል። አሳምነናቸው ለ2 እና ለ3 ቀን ብቻ የመጡ አሉ። ይህንን እንደ አገር የገነባነው ስም እንዳይጠፋ ‹ፕሮቴክት› አድርገናል በተሳካ ሁኔታ አልፈነዋል" በማለት ያጋጠማቸውን ኪሳራ ኃላፊው ገልጸዋል።

ከዚህ በኋላ ይህንን መሰል ነገር እንዳይከሰትና የፕሮግራም ለውጦች እንዳይፈጠሩ በጋራ መስራት መመካከር፣ ቅድሚያ ለኢንቨስትመንቱ መስጠት አስፈላጊ መሆኑንም ነግረውናል። በመጨረሻም አቶ ቁምነገር ተከተል "የሆቴል ሾው አፍሪካ በዚህ 5ዓመት ውስጥ በአፍሪካ ውስጥ ምርጥ 3ኢግዚብሽን እንዲሆን ነው የምናስበው። ከዓለም አቀፍ ፓርትነሮች ጋር ስምምነት እየፈፀምን ነው። እርሱ ወደዚህ ደረጃ እንዲያድግ እንፈልጋለን። በአማካይነት ደረጃ ደግሞ አፍሪካ ውስጥ ተመራጭ የ‹ኮንሰልታሲ ፋርም› እያቋቋምን ስለሆነ በዚህ መልክ እዚያ እንደርሳለን ብለን እናስባለን፡ ፡ መንግስት ደግሞ ከፕራይቬት ሴክተሩ ጋር በአግባቡ እየተመካከረ ስራዎችን እንዲሰራ እንፈልጋለን። ከፍቃድ ጋር የተያያዙ አንዳንድ መዘግየቶች ቢኖሩም፣ ወቅታዊ የሀገሪቱን ሁኔታ ተገንዝበው በመፍቀዳቸው ሳናመሰግን አናልፍም። በዋናነት ፕራይቬት ሴክተሩ በእኛ ላይ እምነቱን ስለጣለብን እናመሰግናለን፡ ፡ የግል ሴክተሩን አክብረው በቦታው ላይ በመገኘት ድጋፍ ለማድረግ የሞከሩት፣ በዋነኛነት ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዶክተር ሂሩት ካሳሁንን በጣም እናመሰግናቸዋለን፡ ፡ በየጊዜው ስልክ እየደወሉ ያበረታቱን ነበር፡ ፡ የት ደረጃ እንደደረስን፣ነገሮች እንዳይጓተቱ ከራሳቸው ፕሮግራም ውጭ እየሄዱ ክትትል ያደርጉልን ስለነበር እሳቸውንና ሚኒስቴር መ/ቤቱን ከልብ እናመሰግናለን" ሲሉ ምስጋናና መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።



# “ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል”

አፈወርቅ በቀለ

## አሥር የንባብ ፋይዳዎች (ጠቀሜታዎች)

እንዲያው ለነገሩ ያህል፣ ለመጨረሻ ጊዜ፣ አንድ ረዥም ልቦለድ ወይም ጠንካራና ትልቅ ርዕሰ ጉዳይ ያሰፈረ መጽሔት፣ አንብበው የነበረበት ጊዜ መች ነበር? ያስታውሳሉ? የየዕለቱ የንባብ ልምድዎ ማዕከል ያደረገው ምን ላይ ነው? መጽሐፍ፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ ወይስ ዘመን አመጣሹ ትዊትስ፣ ፊተ - መጽሐፍ፣ ድረገፅ ነው? ወይስ በጠዋቱ እንቁላል ጥብስ ላይ ወይስ የእንጀራ ትኩስ ፍርፍር ላይ ያተኩራሉ? እንግዲህ እርስዎ ንባብን ከማያዘወትሩ ቁጥር ስፍር ከሌላቸው ሰዎች መሀል አንዱ ንዎት? ከሆኑ ሰዎነትዎ በከፊል ብቻ ነው ማለት ነው። ምንአልባትም በዓለም ላይ ስለመኖርዎ ተዘንግተዋል።

ማንበብ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። ከበርካታ ጥቅሞቹ መሐል፣ እነሆ አሥር ያህል ፋይዳዎቹ።

### 1. የአዕምሮ መነቃቃትን ወይም መነሳሳትን ያበረክታል

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ የአዕምሮን መነቃቃት ወይም መነሳሳት፣ አልዛይመር ከተባለ የአዕምሮ የዝንጋታ ሕመም፣ እንዲሁም ዱመንትያ ከተባለ የአዕምሮ ዕድገትን የሚቀንስ በሽታ (ሕመም)፣ ንባብ እንደሚገታና አዕምሮ ሥራውን እንዳያቋርጥና ኃይሉን እንዳያጣ ይረዳል። በአካል ውስጥ እንደሚገኙ ሌሎች አካላት፣ ጡንቻዎች ሁሉ ፣ እእምሮም የአካል እንቅስቃሴ (ስፖርት) ያሻዋል። ስለሆነም “ንባብን ተገልገልበት ወይም ጥፋበት (ባለማንበብ)”፣ የሚለው አባባል፣ አዕምሮን በተመለከተ ተገቢ ይሆናል። እንቆቅልሾችን መጫወትና መመለስ፣ ቼዝ፣ ዳማ የመሳሰሉትን ጨዋታዎችን ማዘውተር፣ ለአዕምሮ ተጨባጭ የሆኑ መነሳሳቶች ለመፍጠር ጠቃሚነት አላቸው።

### 2. ንባብ የአዕምሮን ሽክምና ድብርት (ጫናን) ይቀንሳል

በሥራ ላይ ምንም ያህል ጫና ይኑርብህ እንጂ፣ በግል ግንኙነትህ ወይም በየዕለቱ በሚገጥሙ ሌሎች ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ችግሮች፣ በንባብ ውስጥ በምታገኘው ትልቅ ታሪክ፣ ተነክረህና ጭልጥ ብለህ በምትጓዝበት ጊዜ፣ ገጥሞህ የነበሩት አተካሮዎች፣ ሙልጭ ብሎ ይጠፋሉ። በደንብ ተደርጎ የተፃፈና የተሰናዳ ልቦለድ መጽሐፍ ታሪክ፣ ወደሌላ ሠፊ አዲስ ግዛት ያሸጋግርሃል። በሌላ በኩል አፍ የሚያስከፍት የጋዜጣ ወይም የመጽሔት ዜና በምታነብበበት ጊዜ፣ ከሌሎች አላስፈላጊ ጉዳዮች ለይቶህ፣ ጭንቀትህን አግልሎ እያዝናና፣ በአሁን ጊዜ ላይ ብቻ እንድታተኩር ይፈቅድልሃል።

### 3. ንባብ እውቀት ነው

እያንዳንዱ የምታነበው ነገር፣ ጭንቅላትህን ወይም አዕምሮህን በአዳዲስ መረጃዎች ይሞላዋል፡ ፡ ተጨማሪ ዕውቀት በሚኖርህና ባደበርህ መጠን፣ በሕይወት የሚገጥሙህን ማንኛቸውንም ተግዳሮቶች፣ መቋቋም ያስችልሃል። በተጨማሪም ለሐሳቦችህ ጥቂት ምግብ ይኸውልህ፡- ምናልባት አንተነትህን በአደገኛ ሁኔታ ወይም አጋጣሚ በምታገኝበት ጊዜ፣ አስታውስ፡- ሁሉንም ነገርህን ታጣው ይሆናል እንጂ ማለትም ቋሚ ሥራህን፣ ሥልጣንህን፣ ገንዘብህን፣ ትዳርህን፣ ወዳጆችህን ሌላው ቀርቶ ጤናህን ታጣለህ። ነገር ግን፣ ዕውቀትህ ፍፁም ከአንተ አይነጠቅም።

### 4.የካበቱ ቃላቶች ባለቤት ያደርግሃል

የሚቀጥለው ዓረፍተነገር፣ ከላይ ከተጠቀሰው ርዕስ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። አብዝተህ ባነበበህ መጠን፣ እንዲሁ አብዝተህ ከአዳዲስ ቃላቶች ጋር ትተዋወቃለህ። ትለምዳቸዋለህም፡ ፡ ስለሆነም፡- ያላንዳች ጥርጥር በየዕለቱ በምታደርጋቸው ንግግሮች፣ (የንግግርና የጽሕፈት ቋንቋዎች)፣ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡ ፡ ነገር አዋቂና አንደበተ ርቱዕ ስለምትሆን፣ ንባብ ለሙያህ የጎላ አስተዋፅኦ ያበረክትልሃል፡ ፡ በራስ መተማመን መንፈስ፣ ከታላላቅ ሰዎች ጋር መግባባትና መነጋገር ስለምትችል፣ ስለራስህ የሚኖርህ ግምትና ስተሳሰብ ከፍ ያለ ይሆናል። የተሰማራኽበትን የስራ ዘርፍ ይረዳል። በደንብ ያነበቡና አንደበተ ርቱዕ የሆኑ ሰዎች፣ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ዕውቀቱ ይኖራቸዋል። በቀላሉና በፍጥነት የስራ ዕድገት መሰላሉን መወጣጣት ይችላሉ። ባለጥቂት ቃላት ምስኪኖች የሆኑ፣ በሥነ-ፅኑፍ ዘርፍ ግንዛቤ አይኖራቸውም። በተመሳሳይ በሳይንስ ዘርፍ ስለተፈጠሩ አዳዲስ ግኝቶች ዕውቀቱ አይኖራቸውም።

### 5. ንባብ የማስታወስ ችሎታን ያሻሽላል፣

መጽሐፍ በምታነብበት ጊዜ፣ የገፀ ባህሪያትን ቅደም ተከተል፣ የመደብ ጀርባቸውን (የመጡበትን ማህበረሰብ)፣ ሊሆኑ የሚፈልጉትን (ምኞታቸውን)፣ በቀላል የማይታዩትን ባህሪያቶቻቸውን፣ በተጨማሪ ጥምዝምዝ መንገዶቻቸውንና ታሪኩን አራማጅ የሆኑ ዋናና ሌሎችን ሴራዎችን ማስታወስ አለብህ። እነዚህ እግዲህ በቀላሉ ሊዘነጓቸው የማይገቡ ጉዳዮች ናቸው። በሚያስገርም ሁኔታ፣ እያንዳንዱ አዲስ የፈጠርኸው ትውስታ፣ አዳዲስ የአዕምሮ ማስፋፊያዎች ማዳበሪያ መንገዶች ስለሚፈጥር፣ ቀድሞ የነበሩትን ትውስታዎች በማጠናከርና በአጭር ጊዜ የቀድሞውን በማስታወስ፣ ወደተጠናከረ መንገድ እንዲሸጋገር ያነሳሳዋል፡ ፡ የአዕምሮን ኃይል ለመጨመር፣ መማር ከተፈለገ እንዲሁም ትውስታን ለማጎልበትና አስር ጊዜ እጥፍ ብቁ እንዲሆን ለማስቻል፣ ይህ እንግዲህ መልካም አይደል?

### 6. ጠንካራ የሆነ የትንታኔ ክህሎት ማዳበር

ከዚህ ቀደም ሲል፣ በጣም አስደናቂ ወንጀል ነክ ልቦለድ መጽሐፍ አንብበህ ከመጨረስህ በፊት፣ ለወንጀሉ መፍትሄ መቋጫ አግኝተህለት ታውቃለህ? እንዲያ ከሆነ አንተ እንግዲህ፣ ታሪኩን የምር ተረድተህ፣ ዝርዝር ሁኔታዎችንና ቅደም ተከተሉን ለመተንተንና መቋጫው ምን ሊሆን እንደሚችል ግምትህን መስጠት ከቻልኽና ወንጀሉን ምን ሊሆን እንደሚችል ከተነበይኽ ወንጀሉን ማን ሊፈፅመው እንደቻለ ፍንጭ ካገኘህ፣ ልቦለዱ ደህና ተደርጎ የተፃፈ ስለመሆኑና ስለሴራው፣ እንዲሁም ገፀ ባህሪያቱ በደንብ ተደርገው ስለመሳላቸው ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስችልሃል። ስለመጽሐፉ ከሌሎች ሰዎች ጋር የመወያየት ዕድል ከገጠመህ፣ ሐሳብህን በግልፅ ማስቀመጥ ይቻልሃል።

### 7.ንባብ ትኩረትንና ማስተዋልን ማሻሻል ያስችላል

በድረ ገጽ (Internet) ዕብደት በገጠመው፣ ዓለማችን፣ ትኩረቶቻችን በየዕለቱ በተለያዩ ሥራዎች በምንጠመድባቸው ወቅቶች፣ በተለያዩ አቅጣጫዎች ይበታተናለሉ፡ ፡ በአንዲት 5 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ፣ በአንድ ተግባር መሐል ኢ.ሜይል መፈተሽ፣ ከሆኑ ሰዎች ጋር ንግግሮችን መለዋወጥ ወዘተ.... መወጣጠሮች ይኖራሉ። እዚህን የመሳሰሉ ውጥረቶች፣ አዕምሮ ላይ ጫና ይፈጥራሉ። መጽሐፍ በምታነብበት ጊዜ ግን፣ ትኩረትህ ሁሉ ታሪኩ ላይ ያርፋል። የተቀረው ዓለም ከአንተ ገለል ይላል። የመጽሐፉ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ ገብተህ ትዘፈቃለህ። መደበኛ የሆነ ሥራህን ከመጀመርኽ በፊት፣ ከአስር ወደ አስራ አምስት ደቂቃ ያህል (በታክሲ፣ አውቶብስ፣ ባቡር ውስጥ) ለማንበብ መኩራ አድርግ።

### 8. የተሻለ የጽሕፈት ክህሎት

ይህ ከቃላት ሀብታምነት ጋር፣ እጅ ለእጅ የሚጓዝ ነው። ተዘጋጅተው ለኅትመቱ ከበቁ ምርጥ መጻሕፍት ተጋላጭ መሆን፣ በራስ ጽሁፍ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። የመፃህፍትህ ደራሲ የአፃጻፍ ሥልት ወይም ዘዬ መከተል በራስ አጻጻፍና ዘዬ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡ ፡ በተመሳሳይ መንገድ አንድ ሙዚቀኛ ሌላው ላይ፣ አንድ ሠዓሊ እንዲሁ ሌላው ላይ ተፅዕኖ ያደርሳሉ። እንዲሁም አዳዲስ ደራሲያን ከሌላው ደራሲ፣ የአጻጻፍ ስልትን ይማራሉ።

### 9. ንባብ ሠላምና መረጋጋት ያመጣል

ንባብ ዘና ከማድጉም ባሻገር፣ መልካም መጽሐፍ በሚነበብበት ጊዜ፣ የምታነበው መጽሐፍ ይዘት፣ ጥልቅ የሆነ ሠላምና መረጋጋትን በውስጥህ ያሰፍናል። መንፈሳዊ ይዘት ያላቸውን መጽሐፍት ማንበብ፣ የደም ግፊትን ዝቅ ማድረግ እንደሚችል፣ አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ።

### 10. ንባብ የማይከፈልበት (ነጻ) መዝናኛ ነው

ምንም እንኳን አብዛኛዎቻችን መጻሕፍት ገዝተን፣ ለመጪ ጊዜ ማጠቃሻ ይሆኑን ዘንድ፣ እልባት አድርገንባቸው ብናስቀምጣቸውም፣ ዋጋና ጠቀሜታ አሏቸው። ብዙ ወጪ ለማያስከትሉ መዝናኛዎች፣ በአቅራቢያችን ወደሚገኝ ቤተ-መጻሕፍት ጎራ ማለት ይቻለናል። ከኮምፒውተሮቻችሁ እስቲ ትንሽ ራቅ በሉ። አንድ መጽሐፍ ይክፈቱ። እናም መንፈስዎንም ለጥቂት ጊዜ ያድሱ

*አራቱ ዋና ዋናዎቹ የንባብ ሥልቶች የሚከተሉት ናቸው።*

- የዳሰሳ ንባብ (skinning)
- አገላብጦ የመመልከት ንባብ (scanning)
- በጥንቃቄ የሚደረግ ንባብ (Intensive)
- ረዥምና ቀጣይነት ያለው ንባብ (Extensive)



ብሩክ መኮንን

# ኒኮላይ ስቴፋቪች ሊዎንቴቭ

# የአገረገዢነት ማዕረግ ያገኘው፤

# "ሩሲያዊው ደጃዝማች"

በጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ትግል ውስጥ አንፀባራቂ የሆነው የአድዋ ድል እንዲገኝ ከኢትዮጵያውያን ጎን በመሰለፍ፣ በጦር ስልት አዋቂነት፣ በጦር መሳሪያ አቅርቦትና በስልጠና ከፍተኛ አስተዋፅኦ ካደረጉ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን አጋሮች ውስጥ በግንባርቀደምነት ከሚጠቀሱ ሩሲያውያን መካከል አንዱ ነው።

ዳግማዊ አፄ ምንሊክ የደጃዝማችነት ማዕረግ ኒሻንና ሜዳሊያ ከሸለሙዋቸው፣ በዘመነመንግስታቸው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተካሄዱ የግዛት ማስፋፋት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ በመሆን በሁለቱ አገራት ዘመን ተሻጋሪ ግንኙነት ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ካደረጉ ሩሲያውያን መሀል አንዱ ነው ኒኮላይ ስቴፋኖቪች ሊዎንቴቭ።

ፌብሯሪ 25 ቀን 1862 ሩሲያ በኬርሰን ጠቅላይ ግዛት፣ ከታወቁ ባለፀጋ መሳፍንት ቤተሰብ የተወለደው ሊዎንቴቭ እድሜው ለትምህርት ሲደርስ፤ በጊዜው የሚሰጠውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ ወደ እውቁ ኒኮላቭ የጦር አካዳሚ በመግባት በእግረኛና በፈረሰኛ የጦር አመራርነት ከሰለጠነ በኋላ በእጩ መኮንነት ማዕረግ ተመርቆ በካዛክ ጦር ክፍል ውስጥ በአዛዥነት ተመድቦ ሀገሩን አገልግሏል።

በመቀጠልም በእ.ኤ.አ 1891 በኩዛክ ጦር በተጠባባቂነት ተመድቦ፣ ሙሉ ጊዜውን የሩሲያ ጦር እና የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ድጋፍ በሚያካሄድ የሀገር አሳሽነት ተልዕኮ ውስጥ መሳተፍ ጀመረ። ገና ከወጣትነት ዘመኑ አንስቶ ከሩሲያ ርቆ በጥቁሩ ዓለም ያለች ኢትዮጵያን ለመጎብኘት እንዲሁም ከአገሪቱ መንግስት ጋር አገሩ ወዳጅነት ለመመስረት እንድትችል ፍላጎት ነበረው።

ለዚህም መሳካት አስራ አንድ አባላት ያሉት የተለያዩ ባለሙያዎች የተካተቱበት፣ የሩሲያ ንጉሰ ነገስት መንግስት ልዩ መልዕክትን የያዘ የልዑካን ቡድንን በመምራት ወደ ኢትዮጵያ መጣ።

በኒኮላይ ስቴፋኖቪች ሊዎንቴቭ የተመራውና የሩሲያ ጆኦግራፊካል ሶሳይቲን በባለቤትነት ያስተባበረው የልዑካን ቡድን ወደ አቢሲኒያ ያመራው፤በውጫሌ ውል መዘዝ ምንም አይነት ዲፕሎማቲክ ግንኙነት ኢትዮጵያ ከተቀረው አለም ጋራ እንዳታደርግ ኢጣልያ በምትከራከርበት ወቅት ነበር። ሩሲያዊው በኢትዮጵያ ከዳግማዊ ምንሊክ ጋራ ተገናኝተው ስለወቅቱ የዓለም ፖለቲካ፣ እንዲሁም የአገራት ግንኙነት መጠናከር ላይሰፊ ውይይት ካደረጉ በኋላ፣ የኢትዮጵያ መንግስት በራስ መኮንን ወልደሚካኤል የሚመራ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ወደ ሴንት ፒተስበርግ፣ ሩሲያ ለመላክ ይወስናል። ይህንን ውሳኔን ተከትሎም ኮንት ሊዎንቴቭ የኢትዮጵያውያኑን የልዑካን ቡድን የሩሲያ ጉብኝት ለማመቻች ኃላፊነት በመውሰድ ወደ ሴንት ፒተርስበርግ ተመለሰ።



በራስ መኮንን የተመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን፣ በሩሲያ የተለያዩ ግዛቶች ባደረገው ጉብኝት የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ባልደረባ በመሆን የሰራው ሊዎንቴቭ፤ ራስ መኮንን የሩሲያ መንግስት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋራ የመሰረተውን ጠንካራ ወዳጅነት ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ወደ ኢትዮጵያ ከልዑኩ ጋራ በመንዝ፣ ከአፄ ሚኒልክ ጋራ ጥብቅ ጓዳዊ ወዳጅነት ለመመስረት እንዳስቻለው ከኒኮላይ ስቴፋኖቪች ሊዎንቴቭ ጋራ በአድዋ ጦርነት ዋዜማ ወደ ኢትዮጵያ ተጉዘው የነበሩ፣ ሌሎች ሩሲያውያን የጦር መኮንኖች በጻፏቸው መጽሐፍት ላይ አስቀምጠውታል።

በኢትዮጵያ ለዓመታት የኖረውና የአፄ ምንሊክ ጦር አማካሪ በመሆን የሰራው ሌላው ሩሲያዊ ሊዮኔድ አርትማኖቭ በአድዋ ጦርነት ዋዜማ፤ ሊዎኔቴቭ ከሌሎች ባልደረቦቹ ጋር በመሆን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1895 ለኢትዮጵያ ጦር 30 ሺህ ጠመንጃ ከ5 ሚሊዮን ጥይቶች፣ 42የተራራ ላይ የሚጠመዱ መድፎችና 15 የጦር አማካሪዎችን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ማምራቱን ጽፏል።

ኒኮላይ ሊዎንቴቭ በኢትዮጵያ የአድዋ ጦርነት ዝግጅት ሲካሄድ ለጥቂት ወራት በእንግድነት ከቆየ በኋላ፣ ወደ ሀገሩ በመመለስ ከዚያም ወደ ቱርክ እና ኢጣሊያን በማምራት ለዓመታት ከቆየ በኋላ፤ የአድዋ ድል በተገኘ ማግስት ኢትዮጵያ ለሶስተኛ ጊዜ ተመልሶ መጥቷል።

በአድዋ ጦርነት ወቅት የኢትዮጵያ ጦር የመድፍ ውጊያ አጠቃቀምን እንዲሁም ሌሎች ወታደራዊ ስልጠናዎችን ሲሰጡ የነበሩ ሩሲያውያን የጦር አማካሪዎች፣ በጦርነቱ የቆሰሉ ተዋጊዎችን የመጀመሪያ እርዳታ እና የሕክምና አገልግሎ ሲሰጡ ለነበሩ ሩሲያውን ዳግማዊ አፄ ምንሊክ አገልግሎታቸውን ከግምት በማስገባት የሜዳሊያና ኒሻን ሽልማት ሰጥተዋል። በዚህም መሰረት የሊዎንቴቭ የቅርብ ጓደኛ ለሆነው ባቤሮችቭ የፊታውራሪነት ማዕረግ፣ ለኒኮላይ ስቴፋቭች ሊዎንቴቭ የደጃዝማችነት ማዕረግ እና የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ባለኮከብ ኒሻን በተጨማሪም የቅዱስ ጊዮርጊስን መስቀል ሜዳሊያ ከነክብር ልብሱ ሸልመውታል።

ኒኮላይ ስቴፋኖቪች ሊዎንቴዝ ሹመት እና ሽልማቱን ካገኘ በኋላ ወደ አገሩ ሩሲያ ሲመለስ ራስ መኮንን የዘመዳቸው ልጅ የሆኑትን ተክለሐዋርያት ተክለማርያምን ወደ ሩሲያ ወስዶ እንዲያስተምርላቸው ለሊዮኔቲቭ አደራ ብለው ሰጥተውታል። በኋላ ላይ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት በሩሲያ በሊዎንቴቭ ቤተሰብ ዘንድ እየኖሩ እንዲማሩ አድርጓል።

ደጃዝማች ኒኮላይ ሊዎንቴቭ ለአራተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ በሴንት ፒተስበርግ የሩሲያ ጂኦግራፊካል ሶሳይቲ አባላት በተገኙበት ስለኢትዮጵያ መልክአ ምድር፣ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ሰፊ የሆነ ገለፃ አድርጎ፤ ሩሲያውያን መዋዕለ ነዋያቸውን በዚች አገር እንዲያፈሱ ጥሪ አድርጎም ነበር።

ከአድዋ ድል በኋላ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ወደ ኢትዮጵያ በገፍ የሚገቡ ግለሰባዊና ሀገራዊ ተልዕኮን ያነገቡ አውሮፓውያን የማዕድን ፈላጊዎችና ሀገር አሳሾች መዋዕለ ነዋይ ለማፍሰስ የሚፈልጉ ስመጥር የዓለም ባለፀጎች፣ ቅጥረኛ ደላሎች አዲስ አበባን አጨናናቀዋት ነበር። ከነዚህ አውሮፓውያን ይልቅ ደጃዝማች ሊዎንቴቭ በንጉሱና ▶

በመኳንንቱ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትና ከበሬታ ያገኝ ስለነበረ ከንጉሱ ጋራ እንዲያገናኛቸው የሚወተውቱት ብዙዎች ነበሩ።

ደጃዝማች ሊዎንቴቭ በኢትዮጵያ በነበረው ቆይታ በቤተመንግስቱ በፈለገ ሰዓት መግባትና መውጣት የሚችል፣ ተወዳጅ የንጉሱ ባለሟል በመሆኑ፤ ምንሊክ ወደ ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያን ግዛት ለማስፋፋት በጀመሩት እንቅስቃሴ ከተሳታፊዎቹ በግንባር ቀደምትነት ሊጠቀስ ቻለ። ይህንንም ተከትሎ ዳግማዊ አፄ ምንሊክ ለሩሲያዊው ወዳጃቸው በኢትዮጵያ የስልጣን መዋቅር የሌለውን ደጃዝማች ኮንት ሌዎንቴቭ፣ በንጉሰነገስቱ ግዛት "የኢኮቶሪያል አካባቢ ሀገረ ገዢ፤ ኮንትአፋ አባይ" የሚል ማዕረግ ሰጡት።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በግብፃዊው ካቭ እስማኤል ግዛት ለማስፋፋት በካሄደችው ዘመቻዎች ጎርደን ቤከርና በሂክስ በተባሉ የአሜሪካውያን የጦር መኮንኖች በቅጥረኝነት የተሳተፉበት የተለያዩ ጦርነቶች፣ እንዲሁም በ16ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ መሐመድ መሪነት ተካሄዶ በነበረ ጦርነት ከኢትዮጵያ ንጉሰነስትን ለመርዳት ከፖርቱጋል የዘመቱ ወታደሮች ከተሳተፉባቸው አውደ ውጊያዎች ቀጥሎ የመጀመሪያው ነው የተባለውን የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ ላይ፤ በደጃዝማቹ መሪነት በርካታ የሩሲያ ካዛክ ጦር አባላትና ፈረንሳውያን ወታደሮች የተካተቱበት ጦርን በራስ ተሰማ ናደው የበላይ መሪነት ወደ ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያን የግዛት ማስፋፋትና የማስገበር ዘመቻ ተካፋይም ሆነ።

በደጃዝማች ሊዎንቴቭ የሚታዘዘው ጦር አንድ ሺኅ ሁለት መቶ ዘመናዊ ጠመንጃዎች፣ ሰባት መለስተኛ መጠን ያላቸው መድፎች፣ ከአስራ ሁለት ዙር ጥይቶች ጋራ ታጥቆ ነበር ወደ ግዳጁ የተሰማራው። በደጃዝማች ሊዎንቴቭ በሚመራው ጦር ውስጥ በምክትል አመራር ሰጭነት ተሳትፈው ከነበሩ ሩሲያውያን ውስጥ በሩሲያ የንጉሰ ነገስቱ ጦር ውስጥ የድራጎን ጦር አዛዥ የነበረው ባሮን ቼንዲአቪየር እና አፄ ምንሊክ በአድዋ ጦርነት ወቅት ላይ በፈፀመው አስተዋፅኦ የታላቁን የሰለሞን ኮከብ ኒሻን የፊውራሪነት ማዕረግ የሰጡት ኢንሳይ ባቪቺቭ፣ ሩሲያዊው ዶክተር ካን ማሪዮሶቭሼ ተገኝተውበታል።

በዚሁ የምንሊክ የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ፣ በራስ ተሰማ ናደው እና በደጃዝማች ሊዎንቴቭ የተመራው ጦር እጅግ ረዥዥም የቀርከሃ ዛፎች እና ሰፊ ደን የተሸፈኑ ከፍተኛ ተራራማ አካባቢዎች፣ ወንዞች የሚፈሱባቸው ሸለቆዎችን ፣እንዲሁም የስምጥ ሸለቆን ተከትሎ የሚገኙ የሀይቆች ሠንሠለት ያለበትን ሩሲያውኑ በራሳቸው አገር ስያሜ የ"ማርጋሬታ፣ የሩስፓሊ ፣ ስቴፓኒ" ብለው የሰየሟቸው የሻላ፣ የላንጋኖና የአብያታ ጫሞ ሐይቆች፣ በስተምስራቅ ደግሞ ረባዳና ሰፊ ሜዳማ መልክአ ምድሮች ያሉባቸው ሰፊ ግዛቶችን እስከ ቱርካና ሐይቅ ድረስ በመዝለቅ በምንሊክ አስተዳደር ስር እንዲካተት ያደረገ የተሳካ ወታደራዊ ዘመቻ ነበር አካሂደዋል።

በኦገስት 8 ቀን 1899 በደጃዝማች ሊዎንቴቭ እና በራስ ተሰማ ናደው የተመራው የምንሊክ ጦር የታችኛውን የኦሞ ወንዝ ተፋሰስን ተከትሎ፣ እስከ ሩዶልፎ ሐይቅ ድረስ የዘለቀውን ዘመቻ በድል በመወጣት፣ ከወራት አድካሚ ጉዞ እንዲሁም በአሁኑ ኢትዮ ኬኒያ ድንበር ድረስ ያለውን የኢትዮጵያን ግዛት በማስገበር፣ የአስተዳደር መዋቅር ሲዘረጋ ቆይቶ ወደ አዲስ አበባ ተመልሷል።

ረዥሙና አድካሚውን ወታደራዊ ዘመቻ በድል ያጠናቀቀው ደጃዝማች ሊዎንቴቭ በንጉሰነገስቱ፣ በኢትዮጵያ ባለስልጣናት ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትና አክብሮት አግኝቷል። ምንሊክ በዘመቻው ለተሳተፉት ሩሲያውያን ወታደሮች ሊዎንቴቭን ጨምሮ የኢትዮጵያን ታላቁን የንጉስ ሰላምን፣ የኮከብ ኒሻን እና ከፍተኛ የገንዘብ ሽልማት ሸልመዋቸዋል።

ደጃዝማች ሊዎንቴቭ ከዚህ ግዳጅ በኋላ ይህንን የደቡብ ምዕራብ ምስራቅ ግዛት የማስተዳደር ስልጣን ከንጉሱ የተሰጠው መሆኑን በመግለፅ በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ግዛት የሚገኘውን እምቅና ያልተነካ የተፈጥሮ ሀብት፣ የሕዝቡን አኗኗር፣ ባህል የሚገልፅ መጽሐፉን በማዘጋጀት በሩሲያ ቋንቋ አሳተመ።

ይህንንም ዕድል በመጠቀም የተለያዩ የዓለማችን እውቅ ቱጃሮች በዚህ የንጉሰ ነገስቱ ግዛት መዋዕለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ በመቀስቀስ በተለይም በመካከለኛው አፍሪካ፣ በአሁኑ ኮንጎ አካባቢ ማዕድን በማውጣት እና በሰፋፊ የእርሻ ስራ ተሰማርተው የሚኙ ቤልጅጋውያን ባለሀብቶችን የቤልጂጉን ንጉስ ሊዎ ፓልድን ጨምሮ በኮንሴንሼን በሽርክና እንዲያለሙ ባካሄደው ዘመቻ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ለመሰባሰብ ቻለ። ይህ ከቤልጅጋውያን፣ከፈረንሳዮች፣ ከእንግሊዛውን ባለሀብቶች አፄ ሚኒልክ በደጃዝማችነት ማዕረግ እንዲያቀናቸው በተፈቀደለት ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ግዛት፣ የኢኮቶሪያል ግዛትን እንዲያስተዳድር የሾሙበትን ደብዳቤ በማሳየት የሰበሰበውን በጊዜው በመቶ ሺህዎች የሚገመት ከፍተኛ ገንዘብን ለግል ጥቅሙ አዋለ።

በተለያዩ ጊዜያት በደጃዝማች ሊዎንቴቭ ገንዘባቸው የተወሰደባቸው ሰዎች መዋዕለ ነዋይ የማፍሰሱ ሂደት ባለመጀመሩ ተበሳጭተው ለዳግማዊ አፄ ምንሊክ የአቤቱታ ደብዳቤ መፃፋቸውን ተከትሎ፣ ዳግማዊ አፄ ምንሊክ በደጃዝማ ኒኮላይ ስቴፋኖቪች ሊዎንቴቭ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ተገደዱ።

ዳግማዊ ምንሊክም ለሊዎንቴቭ ሰጥተውት የነረበውን የደጃዝማችነት ማዕረግ፣ እንዲሁም የደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ "የኢኮቶሪያል ግዛት አገረ ገዥነት" ስልጣኑን በመንጠቅ፣ ከሜይ 1902 ጀምሮ በአስቸኳይ የኢትዮጵያን ግዛት ለቆ እንዲወጣ ወሰኑ። ይህንኑ ውሳኔያቸውንም በኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ላላቸው መንግስታት ተጠሪዎች አሳወቁ።

በጊዜው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የነበረው ደጃዝማች ሊዎንቴቭ በገጠመው ውድቀት፣ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ፣ በተጨማሪም በአዲስ አበባ የሚገኙ አውሮፓውያንና የውጭ ዜጎች በመገፋቱ በፍጥነት አገሪቱን ለቆ ለመውጣት ተገደደ። ይህንን የመጨረሻ እርምጃውን ከመውሰዱ በፊት ግን ለመጨረሻ ጊዜ ዳግማዊ አፄ ምንሊክን እጅ በመንሳት ለመሰናበት ይፈቀድለት ዘንድ ጠየቀ።

ምንሊክም ፈቀደሉት። ሩሲያዊው ደጃዝ ማች ሊዎንቴቭ ምንሊክን ለመሰናበት በቤተመ ንግስታቸው በተገኘበት ወቅት ከንጉሱ፣ ከሹማ ምንቱ ጋር የነበረው ቆይታ መልካምና ኀዳዊ ስሜትን የተሞላ ነበር። ይህንንም አጋጣሚ በመጠቀም ቀደም ባሉ ዓመታት የሩሲያው ንጉስ ዳግማዊ ኒኮላስ ለምንሊክ ታላቁን የሩሲያ የቅድስት አን ሜዳሊያ ከነኒሻኑ፣ እንዲሁም አንድ ከአልማዝ የተሰራ ቀለበት አበርክተውላቸው ነበር። ይህ ከንጉስ ኒኮላስ የተሰጠ የአልማዝ ቀለበት ከተሰጣቸው ቀን ጀምሮ ከእጃቸው ላይ አልተለየም ነበር። የአልማዝ ቀለበቱ ቀደም ብሎም የልዑል ሄነሪ ደ ኦርየልስንም ቀልብ ትኩረት ስቦ የነበረ ውድ ዋጋ ያለው ቀለበት ነው።

ሊዎንቴቭ አጋጣሚውን በመጠቀም ምንሊክን ለራሱ በዚች የአልማዝ ቀለበት ተመሳሳይ ቀለበት ማሰራት እንደሚፈልግ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኘው ታዋቂ አርመኒያዊ አንጥረኛ የቀለበቱን ዲዛይን እንዲገለብጥለት ለማሳየት እንዲመልሱለት ጠየቃቸው።

አፄ ምንሊክም ለዚህ ዕድል ፊቱን ያዞረችበት፣ የተደማጭነቱ ፀሐይ የጠለቀችበት የድሮ ወዳጃቸው ያቀረበውን ጥያቄ አድምጠው ለመከልከል አልጨከን አሉና "እሺ፤ እንዳልክ ይሁና" ብለው ቀለበታቸውን አውልቀው ሰጡት። ደጃዝማች ሊዎንቴቭ ቀለበቱን ተቀብሏቸው ተመልሶ እንደሚመጣ በመጥቀስ ተሰናብቷቸው ወጣ። ከዚያ በኋላ ግን ፈፅሞ አልተመለሰም። ሊዎንቴቭ ቀለበቱን ይዞ ቀጥታ ወደ ጅቡቲ ነበር ያመራው።

ምንሊክ የሩሲያው ንጉስ የሰጧቸውን የአልማዝ ቀለበት ይዞ የተሰወረውን ሊዎንቴቭን አሳደው በቁጥጥር ስር ውሎ የማስመለስ ሰፊ ዕድል ቢኖራቸውም፣ ይህንን ዕድላቸውን ተጠቅመው የቀድሞ ወዳጃቸውን ለተጨማሪ የመንፈስ ስብራት ጉዳት እንዲጋለጥ ለማድረግ ስላልጨከኑ ጉዳዩን ለአምላካቸው ሰጥተው ተውት።

ደጃዝማች ሊዎንቴቭ በ1902 እና 1903 በጅቡቲ ነበር ያሳለፈው። በኢትዮጵያ ጀምሯቸው የነበሩ የተለያዩ የሽርክና፣ የንግድና የእርሻ ሥራዎች ስራ እንዲሁም በእቅድ ደረጃ የነበሩት ሳይጀመሩ መክነው መቅረታቸው፤ ሙሉ ለሙሉ ሙልጩን መውጣቱን በመረዳት ልቡ በሐዘን ተሰብሮ፣ ቤስቲያቤስቲን ሳይኖረው ወደ አገሩ ወደ ሩሲያ መመለስን ስላልፈቀደ በሚያዚያ 1903 ወደ ፈረንሳይ በማቅናት በዚያ በስደት ይኖር ጀመር።

ከዓመታት በኋላ በሩሲያና በጃፓን መካከል በተቀሰቀሰው ጦርነት ላይ ለእናት ሀገሩ ሩሲያ ተሰልፎ በተለያዩ ጦርነቶች በጀግንነት ተዋግቶ ምርጥ ተዋጊነቱን አስመስክሯል። ከጦርነቱ በኋላም ወደ ጅቡቲ በማቅናት በተደጋጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ለመግባትና በእርሻ ሥራና በንግድ ተግባር ላይ ለመሰማራት ቢሞክርም፣ የኢትዮጵያ መንግስት ፈቃደኛ ባመሆኑ ተበሳጭቶ ከ1906 ጀምሮ በጅቡቲ ለአመት ያህል ቆየ።

በጊዜው በነበረው ተሰሚነትና ስልጣን ያገኘውን ዕድል ማስተዋል በማጣት በፈፀመው የገንዘብ ብክነት፣ እንደ ሁለተኛ አገሩ በሚቆጥራት ኢትዮጵያ ተመልሶ ወደ ግዛትዋ እንዲገባ ፍቃድ ባለማግኘቱ ተበሳጭቶ ወደ አገሩ ሩሲያ ከመመለስ ወደ ፈረንሳይ ተሰደደ። በፈረንሳይም በስደት ለዓመታት በድህነት ውስጥ ሲኖር ከቆየ በኋላ በ1914 መዳረሻ አካባቢ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። በኢትዮጵያ ታሪክ የአገረገዥነት ማዕረግ ያገኘው፣ ምናልባት ብቸኛው የውጭ ዜጋ ሩሲያዊው ደጃዝማች ኒኮላይ ስቴፌኖቪች ሊዎንቴቭ ይሆናል።



መምሕር አሸብር ውርጌሳ

# የለውጥ ጉዞው "የልምዣት ሆነ እንዴ?"

የክቡር ዶ/ር አቶ ሀዲስ አለማየሁን "የልምዣት" የሚለውን መጽሐፍ ያነበቡ ነጭ ጀርመናዊ ተመራማሪና ፕሮፌሰር ዚመርማን ናቸው ይኸን ጥያቄ ለወዳጆቻቸው ያቀረቡት፡፡ ጀርመን Hamburg university ውስጥ ግዕዝን ከ10 ዓመት በላይ Ethiopian studies ለብዙ ዓመታት ያስተማሩና ያጠኑ የተመራመሩ አዛውንት፣ ለማርች8 ብለው ከ10 የሚበልጡ የታወቁ አውሮፓዊ ጎልማሳና ወጣት ጋዜጠኞች፣ አምስት እውቅ ምሁራን በሐምቡርግ ዩኒቨርስቲ በአነስተኛ ካፍቴሪያ እየተጨዋወቱ "የሴቶች በአል ወይም ትግል ቀዘቀዘ እንዴ?" እያሉ ሲወያዩ፤ አንዱ ከመሀከላቸው በማርች 8 ገለፃ መካከል ድንገት ዘው ብሎ ገብቶ ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ማብራራቱን ተያያዘውና ትኩረታቸውን ወሰደ፡፡ ውይይቱ ላይ አንድ ወጣት የተሰደደ ጋዜጠኛና አንድ ከሐምቡርግ ዩኒቨርስቲ በጡረታ የተገለሉ የታሪክ ተመራማሪ ነበሩ፡፡

ፕሮፌሰር ዚመርማን በድንገት ወደ ሀበሾቹ እያዩ "የባለፈው ዓመት የወርሃ መጋቢቱ የጠ/ሚ/ር ዐቢይና ጓደኞቹ ትንግርተኛው ዴሞክራሲያዊ የመሰለ ለውጥ የልምዣት ነበር እንዴ?" ብለው አፈጠጡባቸው፡፡ የለውጡ ፍሬዎች በርካታ አለምን ያስደነቁ እውነቶች ቢኖሩባቸውም፣ አሁን ግን ሊደበዝዝና ሊጨልም ያሰበ ሁኔታ ተከስቷል፡፡ ኢትዮጵያ ኮ ብዙ ጊዜ በተቃርኖ እና ሚስጥራዊ በሆኑ ነገሮች የተሞላች ነች፡፡ አንዳንድ አጋጣሚዎች እኮ ሁለተኛ እድል የላቸውም፡፡ ፖለቲካ ከሚያስገኘው ጥቅም በበለጠ ድርጅትንም ማህበረሰብንም፣ መንግስትም ዳግመኛ እንዳያንሰራሩ እንደ ጎርፍ ጥርግርግ ያደርጋቸዋል፡፡ እናም አምና በመጋቢት ወር ተጋግሎ ብዙ ያፈራው የኢትዮጵያውያን፣ በተለይም የወጣቱ የትግል ፍሬዎች በጠንካራ አመራርና ፖለቲካዊ ድርጅት ካልታገዙ አስጎምጅቶ በአፍጢሙ እንዳይደፋ፣ ወደ Dictatorship እንዳይቀየርና የልምዣት እንዳይሆን አጥብቀን በእውነተኛ መንገድ መጓዝ አለብን፡፡ በተለይም እንደኛ አገር ትልቅ ራዕይና ትልቁን ሥዕል ማየት ይኖርብናል፡፡ የእለት ተእለት ወይም ትንንሽ ግቦችን የሚያይ ማህበረሰብ ባለድል አይሆንም፡፡

በእኔ አስተያየት ከአሁኑ አጣብቂኝ ለመውጣት የሌላ አገር ተሞክሮ አያስፈልገንም ባይ ነኝ፡፡ ለምን ቢባል በአንድ ውይይት ላይ ፀሐፊ ተውኔት አያልነህ ሙላት ያሉትን አስታውሼ ነው "ጃፓኖች በነበራቸው የጥንት ሀገራዊ ባህልና እሴቶቻቸው ላይ ከየሄዱበት ሀገር ዳያስፖራ ሆነው ያገኙትን ዘመናዊ እውቀት ወደአገራቸው አምጥተው አገራቸውን የሚያሳድግ ጥበብ ፈጥረው ሰለጠኑበት፡፡" የሚለውን፡፡ እኛም ከእነሱ ብንበልጥ እንጂ አናንስም፤ ብዙ ሳይንቲስቶች፣ ምሁሮች ቢልየነሮች አሉን፡፡ ይኸንን አቅም በጥሩ አመለካከት፣ በጥሩ ተወዳዳሪ ሀሳብ ተጠቅመን፣ በዚህ የለውጥ አጋጣሚ የዶክተር ዐቢይን ኢትዮጵያዊነት ተገን አድርገን፣ በአፍ ሳይሆን በተግባር የለውጥ አካል እያደረግን ከችግር መውጣት እንችላለን፡፡ የእነ ቴዎድሮስ፣ የእምዬ ምንሊክን የአፄ ኃ/ስላሴን አዲስ የብልፅግና ራዕይ መሪ ብቻ ሳይሆን ህዝባችንም አሁን ከተጠናወተው የዘር ፖለቲካ ምንጥቅ ብሎ እንዲወጣ መጣር አለብን፡፡

በ1966ቱ አብዮት "እንደሆቺሚኒ፣ እንደቼጎቬራ" እያልን እንዘምር ነበር፡፡ ያኔ ወጣት የነበርን ልጆች 4 ኪሎ አርት ጋለሪ አካባቢ የያኔ የመኢሶን መሪዎች ከቻይና ያመጡልንን መጽሐፍት ከ10 -20 ብር ወጪ አድርገን፣ በልጅነት የኔታ ቤት የተማርኩባቸው ዳዊትና ወንጌልን፣ የአገሬን ቁርዓን የሚያካክሉ የMao መፃጎፍት ገዝተን አንብበናል፡፡ ምንም እንኳ ለአሁኑ መጥፎ ዘር ቢሆኑብንም፣ ቼጉቬራን የሚበልጠው የኮለኔል አብዲሳ አጋን መጽሐፍ ያነበብነው ስንቶቻችን ነን? ፕሬዝዳንት ማርሻል ቲቶ ለአገራቸው የመከላከያ ሚኒስትርነት ያጩት፣ እሱ ሳይጠይቅ የዩጎዝላቪያ ዜግነት በክብር የሰጡት፣ ሳያስቀይማቸው "አገሬ ሄጄ ልስራ" ያለ ጀግናችን እስኪ የጥሞና ጊዜ ወስደን እናስበው፡፡

እስኪ ጉዳዩን Critical thinking በሚለው አስተሳሰብ እንፈትሸው፡፡ ለንደን አውራጎዳና ላይ እየሄደች በሞባይልዋ "የእንግሊዝ ዜግነት አገኘሽ" ስትባል ልብዋ እንደ ከበሮ እየደለቀ፣ "ያገሬ ታቦት ምስጋናህ ይድረስህ" እያለች የእንግሊዝ ዜግነት በማግኘትዋ ብቻ መሬቱን ሳመች፡፡ ምን ታድርግ! ቢመራት፣ ቢከፋት እንጂ ሀገርዋን ጠልታ አልነበረም፡፡ በፖለቲካው ረገድ በርካታ ምሁራን ፖለቲከኞችም ተሰደዋል፤ ለአለም ሲሳይ ሆነዋል፡፡ ያውና ከብዙ ዓመታት በኋላ ወደ አገራቸው እየተመለሱ ነው፡፡ ስለዚህ የተዘራብንን የዘር ፖለቲካ ወደ ዜግነት ፖለቲካ ቀይረን፣ አንዲት ኢትዮጵያን መመስረታችን አይቀሬ ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ከዛ በፊት ምሁራኖቻችንና ፖለቲከኞቻችን በርካታ ወቅታዊ ሥራዎች ይጠብቃቸዋል፡፡ የብሔርተኝነት ፖለቲካን በትምህርት በመቀየሩ ረገድ፡፡

ሌብነት፣ ፍትህ መጓደል፣ በነፃነት አለመኖር የተከሰተው ለሆዳቸው ባደሩ ሰዎች ስለተመራን ነው፡፡ አለቅጥ ገንዘብ ያፈቀረ አረመኔ ነው፡፡ በኦጋዴንና ጅጅጋ (በሱማሌ) ያየናቸው እስርቤቶች፣ በሻሸመኔ በሽማግሌዎች ላይ የተፈጸመው ግፍ የእሴቶቻችን መሸርሸር፣ ባህላችን ከስሞ የጭካኔ ዘመን መምጣቱን ያሳያል፡፡ ጥቂት ከቆየን እርስበርሳችን እንበላለን፡፡ ይኸን በአስቸኳይ መቀልበስ ይኖርብናል፡፡ እሴት ከሌለ ሞራል የለም፡፡ ስለዚህ እንደ ንሥር አሞራ ለውጥ ፈላጊዎች መሆን አለብን፡፡ የለውጡ ኃይሎች የቀየሱት ዕውን እንዲሆን መታገል አለብን፡፡ ከሌላ ፕላኔት መሪ አንጠብቅ፤ ጠቅላይ ሚኒስትራችንን በእውነተኛውና በትክክለኛው መንገድ እየደገፍን፣ በሚታዩ ጉልህ ስህተቶች ላይ በሀቅ እየታገልን የተጀመረው ለውጥ እንዳይቀለበስ መሥራት ይኖርብናል፡፡

ኢህአዴግ በባህሪው ሲጨንቀው "የህዝቡን ጥያቄ ተረድቻለሁ፤ስህተቴን አርማለሁ፤ በስብሰናል፣ ገምተናል" እያ ወደፊት መራመድን፣ አድበስብሶ ማለፍን ይመርጣል፡፡ ሐኪሙም፣ መምህሩም፣ የፋብሪካ ወዛደሮችም ጥያቄ ሲያቀርቡ "ጥያቄአችሁ ፍትሀዊ ነው፣ ትክክል ናችሁ፣ እየሰራን ነው" እያሉ መሸንገል አያዋጣም፡፡ እውነት እንናገር፡፡ በእንግሊዞች በተፃፈው change management "አንድ መሪ ሕዝቡን ከናቀ፣ ዝቅ አድርጎ ካየ፣ ከካደ እሱ የመጨረሻ ውድቀት ምልክት መሆኑን ሊያውቀው ይገባል" ይላል፡፡ እዚህም እዚያም ያለው መፈናቀል የአመራር ድክመት ማሳያ ነው፡፡ የሁሉም ብሔረሰቦች ባህላዊ እሴቶቻችን ተመሳሳይ ናቸው፤ የእናት ፍቅር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከቋንቋ በስተቀር ልዩነት የለውም፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በዚህ ሁለትና ሦስት ዓመት የተባባሰው መፈናቀል፣ እንደ ሩዋንዳው ቱትሲ እና ሁቱ ጎሳዎች መተራረድ ውስጥ ይከተን ነበር፡፡

የዘር አስተሳሰብና የተጋነነ የገንዘብ ፍቅር (ስግብግብነት) ወደ አውሬነት ይቀይራል፡፡አሁን በቅርቡ የነበረው በደቦ የመስራት ባህላችን በ"ደቦ ወደ መግደል"፣ ወደ እንስሳነት ባህሪይ እየተቀየረ ነው፡፡ በኢትዮጵያችን በሁሉም አካባቢ ለረጅም ዘመናት አብሮ ከመኖር ያተረፍናቸው የወል ስሜቶችና ዓለምን ያስደነቁ አስተሳሰቦች በብርሃን ፍጥነት በጡንቸኛ አስተሳሰብ ተተክተው፣ ከባድ ችግር እያስከተሉብን ናቸው፡፡ ዘግናኝና አሰቃቂ ኩነቶችን እያሳዩን ነው፤ ወደ እንስሳት ልንቀየር ጫፍ ላይ ደርሰናል፡፡ በእውነትና በውሸት መሀል ያለው ልዩነት እየጠፋ ነው ፡፡ ▶

ከ50 ዓመት ጀምሮ የተዘራብን ጎሳዊ መርዝ ከዘመኑ ካንሰር የሚበልጥ በሽታ ሆኖ ጉድ እንዳይሰራን መጠንቀቅ አለብን። ኢትዮጵያችን ውስጥ አዲስ የበቀሉ፣ በዲሞክራሲያችን፣ በኢኮኖሚያችን መጥፎ ዘር ዘርተው፤ በነፃነት ስም ወደ ሥልጣን ሊጠጉ ያቆበቀቡትንም በጥንቃቄ ማስተዋል ያስፈልጋል። ሌጣቸውን መጥተው አሁን ግን ማጅር ግንዳቸው አብጦ፣ ቤታቸው ቁጭ ብለው በዘረፉት ቢልዮን ብር፣ በ27 ዓመት ባካበቱት ታክቲክ ለክፋት እየሰሩ ያሉትንም አንድ መላ ሊበጅላቸው ይገባል። ድሮ ያልነበረብን ጭካኔ አይናችን ሲያስተውል፣ እሴቶቻችን ብቻ ሳይሆኑ የኃይማኖት እምነቶችም ተሸርሽረው ሊያበቁ ትንሽ ነው የቀረን።

ለምሳሌ የእነ አቡነ ጴጥሮስ ሰማዕትነት አሁን ላይ ተረስቷል። ድሮ በቁርዓን ከተማለ፣ በህግ አምላክ ከተባለ፣ በወደቀችው ባንዲራ ከተለመነ ማን ንቅንቅ ይል ነበር? አፄ ምንሊክ "ማርያምን" ብለው ነው ያን ሁሉ ሠራዊት ያዘመቱት። እስኪ የድሮና የዘንድሮ ጳጳሶች፣ ቄሶች፣ ቃልቻዎችም ሆኑ ኡስታዞችን እንገምግማቸው። ሰሞኑን የሩሲያው አምባሳደርን የአማርኛ ንግግር እናስተውል፤ አንዳንዱ እኚህን አምባሳደር ያልተማሩ አድርጎ የሚቆጥራቸው አይጠፋም፣ "በእንግሊዘኛ አይናገሩም ኖርዋል" የሚልም አይጠፋም። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግን አማርኛችንን ስላወቁ ከልቡ ደስ ይለዋል። ይህ የማንም የአለም ማህበረሰብ ባህርይ ነው። ለምሳሌ አንድ የእኛ አገር ደራሲና ተርጓሚ ከፈረንሳይኛ ወደ አማርኛ የአገራቸውን ፅሁፍ ስለተረጎመ ብዙ ሺህ ዩሮ ሸልመውታል። የሊሴ ገ/ማርያም ተማሪዎች ወደ ፓሪስ ሄደው የተደረገላቸው መስተንግዶ፣ በተለይም በአንደኛ ደረጃ እኩያ ተማሪዎቻቸው ያገኙት ፍቅር የተለየ ነው። ወደ ሩሲያው Ambassador ስንመለስ ግን፣ ከዚህ የተለየ እውቅናና ክብር አለበት። የቀድሞዋ soviet ህበረት USSR ከኢትዮጵያ ጋር ከብዙ መቶ አመታት በላይ የጠበቀ ግንኙነት ነበራት፤ በቅድመ አያቱ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ደራሲ ፑሽኪንን ማስታወስ ብቻ በቂ ነው።

በቀድሞዋ Russia Lenin grand ውስጥ ትልልቅ የኦርቶዶክስ ገዳማት በአንድ ግቢ ውስጥ ይገኛሉ። እዚያ ውስጥ በአለም የታወቀ ዘለግ ያለ እድሜ ያስቆጠረ አንጋፋ የምርምር ዩንቨርስቲ ይገኛል። አንድ ኢትዮጵያዊ ቀሲስ ሰለሞን የተባሉ በቅድስና ትምህርት የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፣ በ1960ዎቹ ማብቅያ በአቡነ ቴዎፍሎስ ጊዜ መሀል አዲስ አበባ ላይ ራሽያኛና የግዕዝ ትምህርት ከአ.አ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለተውጣጡ ጎበዝ ተማሪዎች በክረምት በነፃ ያስተምሩ ነበር። እና Lenin grand University አንድ ትልቅ የግዕዝና የአማርኛ Department እንደነበርና ሼልፉ ሁሉ በብራና የተፃፉ የግዕዝና የአማርኛ መፅሐፍት (በብዙ መቶ የሚቆጠሩ በሳይንስ በሥነ ፈለግ (ከዋክብት)፤ በጋላክሲ በፕላኔቶች ታሪክ፣ በመድሃኒት ቅመማ የተዘጋጁ ለዘመናዊ ሳይንስ ምርምር መነሻ ሀሳብ የሚሰጡ የጥንት ብራና የግዕዝ መፃኅፍት) እንደልብ ይገኙ እንደነበር ያስተምሩም ነበር።

እንደውም ሶቭየት ሕብረት የመጀመሪያውን መንኮራኩር ወደህዋ ያመጠቀችው በዘመኑ ከደረሰችበት ቴክኖሎጂ በተጨማሪ የእነዚያ የብራና ፅሁፎች መረጃም ተጨማሪ እውቀት ሆኖላቸው ነበር። እኚህ የሩሲያ አምባሳደር የዚያ ውጤት ናቸው። በተመሳሳይ በጀርመን (Hamburg) university ከመቶ አመታት በፊት ፈረንጆች ግዕዝን ያስተምሩ ነበር። በግብፅ (Alexandria University) ወይም ከሁሉም አገሮች የበለጠ ቀረቤታ አላቸው። ምክንቱም Blue Nile ወይም የእኛ አባይ የሕይወታቸው መሰረት ስለሆነ ነበር። የግብፆች የልቡና ውቅራቸው የተመሰረተው በአባይ ስለሆነ ቀልድ አያውቁም። ድሮ ከኢትዮጵያ ነገስታት ጋር ተዋግተውበታል። አሁንም ከስብሰባ አለመገኘት አንስቶ እስከ ቦክስ መላለጥ የመሪዎቻቸው፣ የአምባሰደሮቻቸው ባህሪይ ሆኖ እያየነው ነው፡ አምባሳደሩና ዲያስፖራው ኢትዮጵያዊ ወጣት የውሃ ሳይንቲስት ስብሰባ ላይ ለቦክስ ተገባብዘዋል። ኢትዮጵያዊውም በልቡ ከተፃፈ የሀገር ስሜት ነበር ለትግል የተነሳው።

የወጣቱን አመለካከት በጥሩ አስተሳሰብ ወይንም Mind Set ለመቅረፅ አ.አ ውስጥ ዶክተር ምህረት ደበበ በስብሰባም በስልጠናም እያስተማረ እንዳለው መሰረታዊ የግብረገብነት ትምህርትን ለእዚህ ትውልድ በትክክል ማውረስ ይኖርብናል።

ስለዚህ ጉዳይ ጥንት Aristotle ‹‹ ልቡናን ትቶ አእምሮን ብቻ የሚያስተምር ትምህርት ጭርሱን ትምህርት አይደለም ይላል ›› ‹‹Educating the mind without educating the heart is no education at all. ››

ስለሆነም በተደጋጋሚ በህፃናት ልጆቻችን በወጣቶቻችን ላይ ጥሩ ዘር በእውነት ላይ ተመስርቶ የሚተገበር እንዝራባቸው። አሁን ወጣቶቻችን በዘመኑ ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሥራዎቻቸው አለምን ጉድ እያስባሉ ነው። ካናዳ ድረስ ሄደው ሽልማት ይዘው እየመጡ ነው። እንደ አትሌቶቻችን እነዚህ ሲያድጉ አይደለም ኢንዱስትሪውን በሮቦት ማጥለቅለቅ የጥንት ማረሻችንንም ለአንዴ ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚቀይሩት እርግጠኛ ነኝ። ለዚህ ሥራ የ Innovation ሚኒስትራችን ጥሩ ጅማሮ እያሳየ ነው። ከሁሉ በላይ ግን ሰሞኑን የፌደራል ኦዲተር መ/ቤት ከ3 ቢልዮን ብር በላይ ተዘርፎ፣ "በየአመቱ አልተመለሰም" እያሉ ማውራት ሳይሆን ፓርላማው እርሙን እነዚህን ገንዘቦች በአጭር ጊዜ ቢያስመልስልን የ20 ዓመቱን ሥሕተታቸውን ያካክስላቸው ነበር እላለሁ።

**የወጣቱን አመለካከት በጥሩ አስተሳሰብ ወይንም Mind Set ለመቅረፅ አ.አ ውስጥ ዶክተር ምህረት ደበበ በስብሰባም በስልጠናም እያስተማረ እንዳለው መሰረታዊ የግብረገብነት ትምህርትን ለእዚህ ትውልድ በትክክል ማውረስ ይኖርብናል።**

የእኛ ሀገር የፖለቲካ ድርጅቶች በ27 ዓመት ታሪካችን ብዙ ስለላ፣ አፈናም፣ መከፋፈልም ቢደርስባቸው እዚህ ደርሰዋል። ከእንግዲህ ከውጭም የመጡት ሆነ አገር ውስጥም ያሉት እንደጀመሩት ውስጣዊ ድርጅታዊ ትግላቸውን አጠናክረው እየተባበሩ ቢቻል ወደ ሦስት እና አራት ቁጥራቸውን አሳንሰው የመሪነት ሚናቸውን እንዲወጡ፣ ሕዝቡንም ለድል እንዲያበቁት፣ በዜግነት ላይ ተመስርተው የዘር ፖለቲካን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሕዝቡ እንዲፀየፉ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

እዚህ ላይ የፖለቲካ ልሂቃን ጥቂቶቹ ልቦናቸው ተቆልፈዋል። ስለዚህ ወደፊት በፅናት ይታገሉ። ምሁራንም አማራጮችን መርምረው በሃሳብ ልዕልና ማህበረሰቡን መምራት ይገባቸዋል። ለዚህ ሁሉ ግን መጀመሪያ ሰው እንሁን። ከማያበራ ችግርና መከራ ከጨለማ የሚያወጣ ኢትዮጵያን ማዕከል እያደረግን እናስብ። ዘርን እንርሳ፤ ትልቅ ሰው ስለሃሳብ ያወራል። ትንሽ ሰው ስለሰውየው ያወራል። በጣም የወረደ ደግሞ ስለቁስ (ስለገንዘብ) ያወራል። ይኸን መነሻ አድርገን ስለእውነት እናስብ። በፍቅርና በይቅርታ ሀይል ላይ አሁንም ተስፋ አንቁረጥ። የለውጥ ሀይሉ በቅድሚያ ለሰላም ይስራ፤ ለህግ የበላይነት ይስራ፤ የዜግነት መርዝ በአዋጅ ፈረንጆቹ እንዳጠፉት ያጥፉልን።

ይህንን የመሪነት እድል ማንም በየትም አያገኘውምና እንደጀመረው ሕዝብን አክብሮ ህዝቡ አርምልን፣ አስተካክልን የሚለውን ከልቡ ይተግብር። እንደ 66ቱ አብዮት ጉልበተኞችና ዘረኞች ለውጣችንን እንዳያኮላሹብን። መሪዎች የህዝቡን ጥቆማና ምክር ካልሰሙ ውጤቱ ወድያው ነው የሚደርሰው።

የድሮ በአሜሪካን ይሰሩ የነበሩት ታዋቂው ፖለቲከኛና ምሁር ለጃንሆይ በጽሁፍ መንግስትዎ እንዳይወድቅ ብለው የሰጡዋቸውን ምክር አልሰማ ብለው ወደቁ። ያንኑ ለደርግ ሰጡት፣ አልሰማም፤ ተገረሰሰ። የአሁኖችም ያንኑ ያንብቡት ይጠቅማቸዋል አለበዚያ ፈረንጆች እንደሚሉት

Don’t be Like a Confused traffic policeman which says beither go nor stop እናም ሕዝብን አምነን አሳትፈን ሀገራችንን ኢትዮጵያ ወደሚፈልገው ዴሞክራሲ ነፃነት የሰብዓዊ መብትንና ልማትን እያስቀደምን ከድህነት አውጥተን እናበልጽጋት። አለበለዚያ የልምዣት ይሆናል የማንተገብውን ተስፋ አንስጥ።

**ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቃት**

# ተስፋና ስጋትን . . .

*ከገጽ 2 የዞረ*

ፓምፍሌቶችን በ17ኛው ክፍለ ዘመን ጽፏል፡ ፡ በንግግር ነጻነት፣ በሀይማኖት ነጻነትና ካቶሊክ ቤተክርስትያንን ከመንግስት አስተዳደር የመነጠል ስራዎቹ በስፋት ይታወቃል፡፡ ሁልጊዜ ቮልቴርን ባስታወስን ቁጥር ካሉት ተወዳጅ አባባሎች ውስጥ አንዱ “I may not agree with what you said but I will fight to death for your right to say it” ይላል፡ ፡ ወደ አማርኛ ስንመልሰው “አንተ በምትለው/ባልከው ነገር ላልስማማ እችላለሁ፡፡ ሀሳብህን የመግለጽ መብትህ እንዲከበር ግን እስክሞት ድረስ እታገልልሀለሁ” ይላል፡፡ ይህን ሀሳብን በነጻነት መግለጽ የት ድረስ ሊሄድ እንደሚገባ ቮልቴር በ17ኛው ክፍለ ዘመን አስቀምጦልናል፡ ፡ “መሳሪያ አንስታችሁ ግደሉ” የሚል ግጭት ቀስቃሽ ንግግር ግን በየትኛውም መለኪያ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ስር በፍጹም ሊካተት አይችልም፡፡

ሆኖም መንግስት እነዚህን የጥላቻ ንግግሮችና ነጋዴዎች ለማጥቃት የሚሄድበት መንገድ በእሱ ላይ የሚቀርቡ ትችቶችንና ወቀሳዎችን ለመደፍጠጫነት እንዳይጠቀማቸው ስጋት አለኝ፡፡ ፕሬሱ አብሮ እንዳይመታም ያሰጋኛል፡፡ መንግስት መጪው ጊዜ ምርጫ እንደመሆኑ፣ በምርጫ ፉክክር ወቅት ደግሞ ከፍተኛ ሚና የሚኖረው ነጻ ፕሬስ በዚሁ አጋጣሚ ሽባ እንዳይሆን አስጊ ነው፡፡ ሚድያዎቻችን አንድ አይነት ዜማን እያስተጋቡ ባሉበት በዚህ ወቅት ጠንካራ ትችት የሚያካሂዱ ጋዜጠኞች “በጥላቻ ንግግር” ማነቆ እየታነቁ ወደ ወህኒ እንዳይጓዙ ያሰጋል፡፡ ይህም 4ኛ የመንግስት ተቋም ተብሎ የተቀመጠውን 3ቱን የመንግስት ተቋማት ለመቆጣጠር አላማ ይዞ የተቋቋመውን የሚዲያን ሚና እንዳያቀጭጨው ያሰጋል፡ ፡ ወደዚህ አቅጣጫ የሚሄድ ከሆነ ግን መንግስትን አፋኝ ስለሚያደርገው የአፋኝ መንግስታት እጣ ይጠብቀዋል፡፡

ሌላው መንግስት በሁሉም ብሔሮች ውስጥ የሚገኙ የጥላቻ ንግግሮችን የሚያሰራጩ ግለሰቦችን በህግ ተጠያቂ የማያደርግ ከሆነ ለጥላቻ ፖለቲካ አራማጆች ተጨማሪ ግብዓት እንደሚያቀርብ ከአሁኑ ሊያውቀው ይገባል፡፡

## ቅጣቱን በተመለከተ

ጀርመን በሰኔ 23፥ 2017 ባጸደቀችው ህግ በማህበራዊ ሚድያ ለሚለቀቁ የጥላቻ ንግግ ሮችና ሀሰተኛ ዜናዎች እስከ 50 ሚልዮን ዩሮ(56 ሚልዮን ዶላር ገደማ) ቅጣትን አሳል ፋለች፡፡

ዋሽንግተን ዲሲ በበኩሏ አንድ ቡድን ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ ንግግር ያደረገ ግለሰብ ከ6 ወር እስከ 3 አመት የሚደርስ ዕስር እንደሚጠብቀው ህጓ ይደነግጋል፡፡ በምን መልኩ? የትኛው አንቀጽ ነው ተግባር ላይ የሚውለው? ወዘተ የሚለውን በተለይ በአሜሪካ የሚኖሩ የህግ ባለሙያዎች ሰፊ ትንተና ቢሰጡበት ግንዛቤያችንን ያሰፋዋል፡፡

መንግስት በጀመረው መንገድ ጠንክሮ መግፋት አለበት፡፡ ውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያንም ይህንኑ ጉዳይ ጠንክረው በመግፋት ለሀገራቸው አለኝታነታቸውን ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡

**መልካም ጊዜ!**

# ዶክተር ዐቢይ . . .

*ከገጽ 7 የዞረ*

“ በማለት እቅጩን ተናግረዋል፡፡ በሃይል መንግስት ልገልብጥ ቢባል አንድም ገልባጮቹ አይተርፉም ካልሆነም በሃገሪቱ ውስጥ የርስ በርስ ጦርነት ይነሳል እንጂ ስልጣኑን አሳልፎ ለገልባጮች የሚሰጥ መንግስት የለም አይነት ነው የተናገሩት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ “ለውጡን የምናስቀጥል ሰዎች እውነት ከኛ ጋር ስለሆነ ማንም አያቆመንም” ነው ያሉት፡፡ ስለዚህ ማንም መንግስት መሆን እንዳያስብ (በህግ አግባብ ካልሆነ በቀር) አይነት ንግግር አድርገዋል፡፡ “ማን ማንን ወግቶ ነው የበላይነት ወይም ሃላፊነት ወይም ስልጣን መያዝ የሚችለው፣ መዋጋት ለሁላችንም እኩል የተሰጠን ብቃት ነው፣ አንዳንዶች የሚችሉት ሌሎቻችን የማንችለው ጉዳይ አይደለም ምክንያቱም ዘመናችንን በሙሉ ስንዋጋ ስለኖርን” በማለትም ወታደርነት ለርሳቸው ብርቅ አለመሆኑን ነው ያሳወቁት፡፡

“በዚህ አጋጣሚ ኢትዮጵያውያን እንዲገነዘቡ የምፈልገው ነገር የዋህነት ይቅርታና ደግነታችን እስከ ኢትዮጵያ አንድነት ብቻ ነው ፣ ብዙ ጊዜ ተሞክሯል ፣አንፈራም ለኢትዮጵያ አንድነት ነገም ግንባራችንን እንሰጣለን” በማለት እስከደም ጠብታ ለመዋጋት “ግንባር እስከመስጠት” የሚደርስ ሃላፊነት መውሰዳቸውንም ገልጸዋል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የወታደር አይነት ገለጻ በጦርነት እና ውጊያ ብቻ ሳይሆን በክላሽም ተገልጿል፡፡

“ለህዝባችን ይበጃል የምንለውን ለማስቀደም ካልሆነ በቀር በኢትዮጵያ ህልውና የሚመጣ ካለ እስክሪፕቶ ሳይሆን ክላሽ ተሸክመን ለመዋጋት ዝግጁ መሆናችንን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲገነዘበው እፈልጋለሁ” በማለት በግልጽ “የቁርጡ ቀን ሲመጣ ኮሎኔል ሆኜ መምጣቴ አይቀርም” ብለዋል፡፡

## ደቡብን በማስጠንቀቂያ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደቡብ ላይ ጨከን ይላሉ ይባላሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በዚያ አካባቢ ሰላም አንደመሆኑ ችግር ሲፈጠር በዚያው መጠን የመረረ እና አስነዋሪ ተግባር ጭምር የሚፈጸም መሆኑ ያሳደረባቸው ቁጣ ጭምር ነው፡፡ የሲዳማ እና ወላይታ ግጭት ላይ ሰዎች የተገደሉበት መንገድ አሳዛኝ ነበር፡፡ በሃዋሳው የቀደመ ውይይት የሲዳማን የቁጣ ቃል ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳልወደዱት እና የተለየ ብሔር ኩራት እንደማያዋጣ ለአንዲት “እኛ ለምነን አናውቅም” ላለች የሲዳማ ወጣት በሰጧት የቁጣ መልስ ማስታወስ ይቻላል፡፡ጉራጌንም “ከናንተ ይህንን አንጠብቅም” በማለት እንዲሁ ወቅሰዋል፡፡

በፓርላማው ቆይታቸውም በደቡብ ክልል የተነሳውን የክልል እንሁን ጥያቄ በተመለከተ የተናገሩት ንግግር የዚሁ ጠንካራ ስሜት ግልባጭ ነው፡፡ “ደቡብ ሰፊዋ ኢትዮጵያ ነው፡፡ በክልል ስም ቢበተን የሁሉም መበተን መነሻ ስለሚሆን ስጋት ቢገባቸው አይፈረድም” ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠንካራ እና የማያወላዳ አይነት ንግግርም ለዚሁ የተሰነዘረ ይመስላል፡፡

“በደቡብ ክልል ያለው ክልል የመሆን ጥያቄ



ህገመንግስታዊ መብት ነው… አሁን ደቡብ አካባቢ ያለውን ነገር መንግስት የህዝብን ጥያቄ በክብር ተቀብሏል፡፡ ደ.ኢ.ህ.ዴ.ን የሚባለው ክልሉን የሚያስተዳድረው ድርጅትም የቀረበለትን ጥያቄ ተቀብሎ በህግ እየመረመረ ይገኛል፡፡ ደኢህአዴን የመጨረሻ ውጤቱን እስኪያሳውቅ ምርጫ ቦርድ ዝግጅቱን እስከሚያሳውቅ በደቡብ ክልል ውስጥ ክልል ለመሆን ለመሆን የጠየቃችሁ ህዝቦች በከፍተኛ ትዕግስት እንድትጠብቁን በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡” በማለት ከተንደረደሩ በኋላ ማስጠንቀቂያቸውን በወታደራዊ ቃል ነው አንዲህ የተናገሩት፡፡

“…ከህጋዊ መንገድ ውጪ ምንም አይነት ሙከራ ቢደረግ ሱማሌ እንደሆነው ደቡብም ይሆናል፡፡ በኢትዮጵያ አንድነት የሚደራደር መንግስት የለም፡፡ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ ተቀብለናል፡፡ በትዕግስት መጠበቅ ፡፡አንቀበልም ሲባል በህጋዊ መንገድ እናስተካክለዋልለን፡፡ በዚህ መንገድ ቢታይ ጥሩ ነው፡፡ በደቦ በጩኸት የሚፈጠር ነገር ከዚህ በኋላ ማስተናገድ ትዕግስታችን አልቋል፡፡ ሁሉም ስር’ዓት ጠብቆ ይሄዳል ፡፡በስርዓት እንመልሳለን፡፡ ያን የማይጠብቅ ከሆነ በተለመደው መንገድ እናስተካክለዋለን፡፡” በማለት ሃይል የማይቀር አማራጭ መሆኑን በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡

## ለፓርቲዎች ማስጠንቀቂያ

“…ልክ ለሰላም ኑ በሰላማዊ መንገድ እንታገል…ብለን እንደጠራነው ሁሉ የኢትዮጵያን አንድነት የሚገዳደር ጉዳይ የሚሰራ ማንኛውም ሃይል በቀጥታ ጦርነት አውጆብናል ማለት ነው ፡፡መንግስት ይህንን ለመከላከል እርምጃ ይወስዳል“ ነው ያሉት፡፡ብዙዎች ከዚህ በመነሳት ኦነግ በቅርብ ጊዜ ሊመታ እንደሚችል ተንብየዋል፡፡“የኢትዮጵያ አንድነት ሰላም ብልፅግና ለዚህ ብለን ነው ትዕግስት የወሰድነው ሰላማችንን አንድነታችንን የሚገዳደር ሃይል ሲኖር የትዕግስታችንን ያህል የመረረ እርምጃ የምንወስድ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡በዚህ ጉዳይ የሚደረግ ምንም አይነት ሆደ ሰፊነት እንደማይኖር ፓርቲዎች ግለሰቦች ቡድኖች ሊገነዘቡ ይገባል” በማለት ነው የተናገሩት፡፡

ለዚህም ነው አስተያየት ሰጪዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነገሮችን በዚህ ከቀጠሉ ኮሎኔል ሆነው መምጣታቸው አይቀርም ወደሚል መደምደሚያ የመራቸው፡፡ይሆን እንደሆን አብረን የምናየው ይሁን፡፡

## ጾቼ ቬሌ

ሐረር ከተማ መብራት ኃይል ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የሚገኘዉ የገበያ ማዕከል በእሳት ጋየ። ዛሬ ጠዋት አንድ ሰዓት ተኩል ግድም የተነሳዉ ቃጠሎ ከ200 የሚደርሱ የተለያዩ የንግድ መደብሮችን አዉድሟል። መደብሮቹ በአብዛኛዉ የኤሌክትሮኒክስ፣ የልብስ፣ የቤት ቁሳቁሶችና የምግብ ሸቀጠሸቀጦች መገበያያ ነበሩ። ቃጠሎዉ በሰዉ ሕይወት እና አካል ላይ ያደረሰዉ ጉዳት የለም። ቃጠሎዉ እንደተሰማ ወደ ሐረር የተጓዘዉ የድሬዳዋዉ ወኪላችን መሳይ ተክሉ እንደዘገበዉ እሳቱን ለማጥፋት የሐረሪ መስተዳድር የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የመከላከያ የምሥራቅ ዕዝ የዉኃ ማመላለሻ ቦቴዎች፤ የሐሪሪ ፖሊስ፤ የፌደራል መከላከያ ባልደረቦች እና የሐረር ከተማ ነዋሪዎች ሲረባረቡ ነዉ ያረፈዱት። እሳቱ ከቀኑ አራት ሰዓት ግድም ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል። መብራት ኃይል ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የሚገኘዉ የገበያ ማዕከል ቃጠሎ ሲደርስበት ያሁኑ ሁለተኛዉ ነዉ። ነዋሪዎች እንደሚሉት በ2007 እዚሁ ሥፍራ የተነሳ ቃጠሎ በርካታ መደብሮችን አዉድሞ ነበር። የገበያ ማዕከሉ ሸዋበር ከሚባለዉ አካባቢ ወደ መብራት ኃይል በጊዚያዊነት የዞረዉ በ2002 ሸዋ በር ላይ በደረሰበት ቃጠሎ ምክንያት ነበር። ይሕ ማለት ማዕከሉ በእሳት ሲጋይ ያሁኑ ሶስተኛዉ ነዉ። የዛሬዉ ቃጠሎ መነሻም ሆነ በንብረት ላይ ያደረሰዉ ጉዳት ትክክለኛ መጠን በዉል አልታወቀም። ከከፖሊስ ጉዳዩን እያጣራ መሆኑን አስታዉቋል።

## ግርማ ሰይፉ

ስለ ሕገ መንግስት መቀየር አለበት። ይህ ቅየራ ከማሻሸል እሰከ ቀዶ ጥሎ አዲስ እሰከ መፃፍ ይደርሳል። እስከዚያ ድረስ ተቀብለህ ትሰራለህ። ወደ አገር ቤት የተመለሱ በመሳሪያ የታገሉ ሁሉ በሰላም ለመቀየር እየሰሩ ነው። አሁን በስልጣን ላይ ያለው ቡድን እንኳን መሻሻል እንዳለበት አምኗል። ለማሻሻል ማዋል ያለብንን ጉልበት ለጭቅጭቅ ባናውለው መልካም ነው። አንድ አማራጭ፣ ሕገ መንግስቱ ተሻሻሎ ምርጫ ይደረግ ካልን፣ ይህን ለማድረግ ቢያንስ ተጨማሪ ሁለት ዓመት ይፈልጋል፣ ይህን ለማድረግ ሁሉም ይስማማል? ባልተመረጠ መንግሰት ለተጨማሪ ጊዜ መተዳደር ማለት ነው። ሌላው አማራጭ አሁን ባለው ሕገ መንግስት ምርጫ በጊዜው ተካሂዶ በሕዝብ የተመረጠ መንግስት የማሻሻል ሃለፊነት ይውሰድ። ምን አልባትም ዋነኛ የምርጫ አጀንዳ ሊሆን ይችላል። እሰከ ህዝበ ውሳኔ የሚያደርስ። ሌሎች አማራጮች አሉ፣ አስቀያሚው አማራጭ የሽግግር መንግስት የሚለው ነው። በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ የሚኬድበት መንገድ። ይህ የሰነፍ አማራጭ ነው። ሌሎች አማራጮች አቅርቡ፣ ንገሩን እንማርበት፣ እንሰልጥን፣ በጨዋ ደንብ ሃሳብ እንለዋወጥ።

## ፕሬስ ድርጅት

ባለፉት 11 ወራት ከ50 ሺህ በላይ ለሆኑ ዜጎች ቋሚ የስራ እድል መፍጠሩን የኢዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ገለጸ። የኢዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በዛሬው እለት ባለፉት 11 ወራት የዘርፉ አፈፃጸም ላይ ውይይቱን አካሂዷል። የኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ለሊሴ ነሜ በውይይቱ ወቅት እንደተናገሩት ባለፉት 11 ወራት ለ50 ሺህ ያህል ዜጎች ቋሚ እና ከ30 ሺህ በላይ ዜጎች ጊዜአዊ የስራ እድል ተፈጥሯል። ከገቢ አንፃርም ከባለፈው ዓመት ተማሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር ከ100 ፐርሰንት በላይ ብልጫ መመዘገቡንም ዋና ስራ አስፈፃሚዋ ተናግረዋል።

እንደ ኤፍ ቢሲ ዘገባ ከሸድ ኪራይ የሊዝ ገቢና ከአገልግሎት ሽያጮች 316 ሚሊየን ብር የተመዘገበ ሲሆን ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶችም 110 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል ነው ያሉት። አዲስ ስራ በሚጀምሩ የኢንዱስሪ ፓርኮች አካባቢ ውሃና መብራት የሰራተኞች የመኖሪያ ቤት እጥረት የዘርፉ ተግዳሮቶች እንደሆኑ በውይይቱ ተነስቷል።

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ መሆኑ ነው የተገለጸው። ከመፍትሄዎቹ መካከል ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ከኤሌክተርክ ሃይል በተጨማሪ ሌሎች የሃይል አማራጮችን ለመጠቀም እንቅስቃሴዎች መጀመራቸው ተጠቁሟል። አምራች ኩባንያዎች ለሰራተኞቻቸው መኖሪያ ቤቶችን ለመገነባት በሚችሉበት ጉዳይ ዙሪያ ከኮርፖሬሽኑ ጋር መግባባት ላይ የተደረሰና መኖሪያዎችን እየገነቡ ያሉ ኩባንያዎች መኖራቸውም ነው የተገለጸው።

